አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

በ

ፍፁም ብርሃኑ ተካልኝ

ለኢትዮጵያ ስነ -ፅሁፍ እና ፎክሎር የኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ  የቀረበ ጥናት

ሰኔ 12/ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

በ

ፍፁም ብርሃኑ ተካልኝ

ለኢትዮጵያ ስነ -ፅሁፍ እና ፎክሎር የኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ  የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

ሰኔ 12/ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

በ
ፍፁም ብርሃኑ ተካልኝ

ሰኔ 12/ 2006 ዓ.ም

የተፈና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ፊርማ

--------------------- ----------------

የውስጥ ፈታኝ

-------------------- -------------------

የውጭ ፈታኝ

------------------ -------------------

## ማውጫ


ርዕስ ገፅ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

አበርክቶ ........ iii

መግለጫ ........ iv

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 2

1.2.1. ግላዊ ምክንያት ........ 2

1.2.2. አካዳሚያዊ ምክንያቶች ........ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 4

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4

1.5.1. ለባህሉ ባለቤቶች የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ........ 4

1.5.2. ለተመራማሪዎች የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ........ 5

1.5.3. በሀገር ደረጃ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ........ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.7. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 7

1.7.1. ምልከታ ........ 8

1.7.2. ቃለ-መጠይቅ ........ 10

1.7.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ........ 11

1.8. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 12

1.9. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 12

1.10. የመስክ ተሞክሮ ........ 13
1.11. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው ........ 17
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 20
2.1. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ........ 20
2.1.1. ትኩረታቸውን የሸካቾ ብሔረሰብ ላይ ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች ........ 21
2.1.2. በርዕሰ ጉዳይ የሚዛመዱ ጥናቶች እና ፅሁፎች ዳሰሳ ........ 24
2.1.2.1. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ የቢ.ኤ ዲግሪ ጥናቶች ........ 24
2.1.2.2. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቶች ........ 28
2.1.2.3. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ ሌሎች ፅሁፎች ........ 34
2.2. የፅንሰ ሀሳቦች እና ንድፈ ሀሳብ ቅኝት ........ 42
2.2.1. የፅንሰ ሀሳቦች ቅኝት ........ 42
2.2.1.1. የሞት እና የለቅሶ ምንነት ........ 42
2.2.1.2. የቀብር ምንነት እና አከዋወን ........ 43
2.2.1.3. ፆታን መሰረት ያደረገ የለቅሶ ስርዓት ........ 45
2.2.1.4. ማህበራዊ ደረጃን መሰረት ያደረገ የለቅሶ ስርዓት ........ 46
2.2.2. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት ........ 47
2.2.2.1. ከበራ (Ritual) ........ 48
2.2.2.2. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ (Performance centered approach) ........ 51
2.2.2.2.1. የክዋኔ ምንነት እና ባህሪያት ........ 51
3. የሸካቾ ብሔረሰብ  አካባቢያዊ እና ማህበረ - ባህላዊ ዳራ ........ 58
3.1. የሸካ ዞን አጠቃላይ ገፅታ ........ 58

3.2. የብሔረሰቡ አመጣጥ ታሪካዊ ዳራ እና ኃይማኖት ..... 59
3.3. የብሔረሰቡ ኢኮኖሚ መሰረት ..... 61
3.4. የብሔረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ..... 62
3.5. የብሔረሰቡ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት ..... 63
4. የመረጃ ትንተና ..... 66
4.1. የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ..... 66
4.1.1. ለህፃናት የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ..... 68
4.1.1.1. ቅድመ ቀብር ክዋኔ ..... 69
4.1.1.2. ጊዜ ቀብር ክዋኔ ..... 70
4.1.1.3. ድህረ ቀብር ክዋኔ ..... 71
4.1.2. ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ..... 72
4.1.2.1. ቅድመ ሞት ክዋኔ ..... 73
4.1.2.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ ..... 76
4.1.2.3. ቅድመ ቀብር ክዋኔ ..... 77
4.1.2.4. ጊዜ ቀብር ክዋኔ ..... 86
4.1.2.5. ድህረ ቀብር ክዋኔ ..... 97
5. ማጠቃለያ ..... 100
የተጠቀሱ ምንጮች ..... 103
አባሪዎች

አባሪ 3፡- በቃለ-መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ መነሻ ጥያቄዎች፣

የሸካቾን ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓተ-ክዋኔ ለመዳሰስ የተዘጋጀ የቃለ-መጠይቅ መነሻ ጥያቄ

- ✓ ቃለ-መጠይቁ የተደረገበት ቀን-----------------------------------
- ✓ » » የተካሄደበት ቦታ-------------------------------------
- ✓ » » የተጀመረበት ሰዓት-----------------------------------

❖ የቃለ-መጠይቁ ሰጪ አጠቃላይ መረጃ፡-

- ✓ ስም ---------------------------------------
- ✓ ፆታ ---------------------------------------
- ✓ ዕድሜ---------------------------------------
- ✓ ብሔር . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
- ✓ የአፍ መፍቻ ቋንቋ. . . . . . . . . . . .
- ✓ የትምህርት ደረጃ---------------------------
- ✓ ስራ------------------------------------------
- ✓ የአካባቢ ቆይታ ጊዜ--------------------------
- ✓ የትዳር ሁኔታ ------------------------------

❖ ለቃለ-መጠይቁ የሚረዱ መጠይቆች፡-

1. የሸካቾ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ (በአጎራባች ከሚገኙ ሌሎች ብሔሮች የተለየ) የለቅሶ ስርዓት አለው ? ካለው ስርዓቱ ምን ተብሎ ይጠራል ?
2. የለቅሶ ስርዓቱ እንዴት፣ መቼ እና የት እንደተጀመረ ይታወቃል ?
3. የለቅሶ ስርዓቱ እንዴት እና በምን አይነት ሁኔታ ይከናወናል ?

4. የለቅሶ ስርዓቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የስልጣን፣ የማህበራዊ ደረጃ፣ የእድሜ፣ የፆታ፣ የጎሳ፣. . .ወዘተ ልዩነቶች ሳቢያ ከዋኔው ይለያያል ወይስ አንድ ነው ? የሚለያይ ከሆነ ልዩነቶቹ እንደምን ያሉ ናቸው ?

5. በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ልዩ ባህላዊ ስልጣን ያላቸው (ማህበረሰቡ ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች ሲሞቱ) የሚደረግ የተለያየ የለቅሶ ስርዓት አለ ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

6. በማህበረሰቡ ውስጥ "ተራው" የማህበረሰብ አካል ሲሞት የሚፈፀሙ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች አሉ ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

7. በማህበረሰቡ ውስጥ ህፃናት ሲሞቱ የሚፈፀሙ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች አሉ ? ካለ ከቀብር በፊት፣ በቀበር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚፈፀሙት ስርዓቶች እንደምን ያሉ ናቸው ?

8. በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት ለሟች የሚገጠሙ፣ የሚዜሙ፣ የሚቅራሩ፣ የሚፎከሩ፣. . .ወዘተ ግጥምና ዜማዎች ካሉ በማን እና እንዴት ይዜማሉ ? ጠቀሜታቸውስ ምንድነው ተብሎ ይታመናል. . . ?

9. በለቅሶው ወቅት የሚለበሱ፣ የሚያዙ፣ በልዩ ልዩ አካላት ላይ የሚታሰሩ፣. .ቁሶች ካሉ አገልግሎታቸው? ማን - ምን ይረባኝ ብሎ ይይዛቸዋል ?

10. የለቅሶ ስርዓት ተዘወትሮ የሚፈፀምበት እራሱን የቻለ ቦታና ጊዜ አለው ? ካለው ለምን ?

11. የግንዘት ስርዓቱ የሚከናወነው እንዴትና በማን ነው ? ለሁሉም ሟች የሚደረገው የአገናነዝ ስርዓት አንድ ወይስ የተለያየ ነው ?

12. አንድ ሰው በሞተ በስንት ቀን ውስጥ ቀብር መፈፀም ይኖርበታል ?

13. ለሟች ወገን የሚደረግ የተለየ ነገር አለ ?

14. ብሔረሰቡ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ወይስ የለም ብሎ ያምናል ?

15. ማህበረሰቡ ሞትን እንደምን ይረዳዋል/ ለሰራው ኃጥያት የተከፈለው ዋጋ ወይስ ፈጣሪ ስለመረጠው ጠርቶት ነው ተብሎ ይታመናል/ ?

16. በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት ይህ የወንዶች፣ ያኛው ደግሞ የሴቶች ተብሎ የሚለይ የአከዋወን ስርዓት አለ ?

17. የቀብር ስፍራ የት፣ እንዴት እና በነማን ይፈፀማል ?

18. በቀብሩ ወቅት እነማን ይታደማሉ/ የቀብር ቦታው ድረስ እነማን በምን አይነት አኳኋን ይሄዳሉ ? ለምን ?

19. በብሔረሰቡ ውስጥ እድር አለ ? ካለ ሚናው እንዴት ይገለፃል ?

20. መጠየቅ ነበረብኝ ብለህ የምታምነው ሌላ ጥያቄ ካለ ብትገልፅልኝ ?

- ❖ በቃለ-መጠይቁ ወቅት የተፈጠሩ አዲስ ወይም ተያያዥ ጥያቄዎች፤
- ❖ በቃለ-መጠይቁ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ስኬቶች፤
- ❖ ቃለ-መጠይቁ የተከናወነበት አጠቃላይ ድባብ፤
- ❖ ከቃለ-መጠይቁ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከዚህ ጥናት ውጪ ላለ የትኛውም አይነት አገልግሎት ቢውል (ለምሳሌ ለልዩ ልዩ ህትመቶች፣ ለመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት፣. . .) የመረጃ አቀባዩ ፍቃደኝነት ምን ይመስላል ?
- ❖ ቃለ-መጠይቁ ያበቃበት ሰዓት፤

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም

ፊርማ

የማስረከቢያ ቀን

## ምስጋና

ጋሽ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በስራው መጀመሪያ ላይ ተመካሪዎቻቸውን በሙሉ ሰብስበው የእያንዳንዱን ክንውን ማስረከቢያ ቀናት በውይይት እንድንወስን በማድረጋቸው እና በተቆረጠው ቀን ለማስረከብ ምን ማድረግ እንዳለብን ያላቸውን ልምድ ስላካፈሉን አብዛኞቻችን በጊዜ አጠቃቀም ረገድ ያሉብንን ችግሮች አስወግደን ጥናታችንን እንድናካሂድ ረድተውናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሆሄያት ግድፈት ጀምሮ እያንዳንዱን ችግር በመንቀስ እና የሚስተካከልበትን መንገድ ያለመሰልቸት በመጠቆም ላደረጉልኝ ከፍ ያለ እገዛ ረጅም ዕድሜ ተመኝቼ የከበረ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡

ልጄ ህፃን ናታኒም፣ ሁሌም ከእናትህ ስልክ ነጥቀህ "አባባ አትመጣም እንዴ ?!" የሚለው ጉትጎታህ የማንቂያ ደወሌ ነበርና እደግልኝ እላለሁ፡፡ "አባዬ" እና "እቴቴ" በደወላችሁ ቁጥር "አላለቀም እንዴ ?!" ስትሉኝ ባያልቅ ሊሰማችሁ የሚችለው ስሜት አስፈርቶኝ የተቻለኝን ሁሉ እንዳደርግ ስለረዳኝ ፈጣሪ ዕድሜያችሁን እንዲያረዝምልኝ ስርክ እፀልያለሁ፡፡

በመረጃ ስብሰባ ወቅት በድሎት በቤታችው ተንከባክበው ያኖሩኝ ዘመዶቼ ታሪኩ እና መሰረት፣ ልጃቸው ያሬድ እና ጓደኛው "ፋጂ" የእናንተ መሰልቸት ያላየሁበት እንክብካቤ እና እገዛ ባይታከልበት ኖሮ በዚያ ቁር ውስጥ አልፌ እንዴት መረጃዎቼን ልሰበስብ እንደምችል ሳስብ የሚሰማኝ ዳገት ከሁሉ አብዝቼ እንዳመሰግናችሁ አስገድዶኛልና ቤታችሁ እንደሞላ እናንተም ሳትጎሉ ያዘልቃችሁ ዘንድ በፅኑ እመኛለሁ፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በተለይም አቶ አምባው ጮሪቶ፣ አቶ ኃይሌ መድራሻ እና አቶ ስለሺ ጫሊቶ የነበራችሁን ውድ ጊዜ እየሰዋችሁ ከቀጠሮው ቀን በተጨማሪ በተደጋጋሚ እያገኛችሁኝ ስለ ብሔረሰቡ ባህል እና ታሪክ በሰፊው ስታስረዱኝ ለወገኖቻችሁ ያላችሁን ተቆርቋሪነትና ቅንነት በሰፊው ያሳየኝ ከመሆኑም በላይ በእኔ ላይ የቤት ስራ ትቶ ያለፈ ተግባር በመሆኑ "የር ኢምቤ !" (እግዚአብሔር ይስጥልኝ) ብያለሁ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምንም እንኳ የወቅቱን የዋጋ ንረት እና ጥናቱ የሚያስፈልገውን የበጀት ዕቅድ ከግምት ውስጥ ያላስገባም ቢሆን ያመነበትን የጥናት በጀት ስለፈቀደልኝ አመስግኛለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ አቢይ ዓላማ የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜ ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት ማሳየትና መተንተን ነው፡፡ ይህንን እና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ መረጃዎች የተሰበሰቡት በሁለት ተፈጥሯዊ አውዶች ላይ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ እና ስለብሔረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው ከታመነባቸው የብሔረሰቡ አባላት ጋር ቃለ-መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማካሔድ ነው፡፡

ከእነዚህ መረጃዎች የተገኙት ውጤቶች እንደሚያሳዩት የብሔረሰቡ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በሁለት የተለያዩ መልኮች በተለያየ አግባብ እንደሚፈፀም ማወቅ ተችሏል፡፡ በብሔረሰቡ ባህል መሰረት አንድ ጥርስ ያላበቀለ ህፃን ሲሞት መሬት ውስጥ የሚቀበር ከሆነ እናትየው ዳግም ልጅ አትወልድም፤ ማህፀኗ ይደርቃል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ከእናታቸው እቅፍ ሳይወርዱ/ ጥርስ ሳያበቅሉ በሞት የሚነጠቁ ህፃናት የሚቀበሩት በሌላው የዕድሜ ክልል ከሚገኝ የህብረተሰቡ አባል በተለየ በአካባቢው በሚገኝ አንድ ትልቅ ዛፍ ውስጥ ነው፡፡ ሟች በእድሜ የገፉ፣ አንዳች ማህበራዊ ስልጣን ያለው እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙ የደረጀ ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ይበልጥ የተለያዩ ክዋኔዎች የሚስተዋሉበት እና የደመቀ ይሆናል፡፡ ሟች ከመቀበሩ በፊት ከአንድ እስከ ሦስት ወር ይቆያል፡፡ ይህም የሚደረገው በዋናነት በየአካባቢው ያሉ የብሔረሰቡ ተወላጆች በቀብሩ ዕለት እንዲገኙ ጊዜ ለመስጠት፣ ለዝግጅት ከወር በላይ የሚፈልገውን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ ለለቀስተኞች ለማዘጋጀት እና በሟች ማሳ ውስጥ መፈፀም ያለባቸውን የእርሻ ስራዎች ለማከናወን መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በብሔረሰቡ ባህላዊ የለቅሶ ክዋኔ ወቅት በዕድሜ፣ በፆታ እና በማህበራዊ ደረጃ ምክንያት የተወሰኑ ክዋኔዎች ልዩነት መኖሩን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል፡፡

በሸካቾዎች ባህል ዋንኛው ለቅሶ የሚከወነው የቀብሩ ዕለት ሲሆን በዚህን ጊዜ ሁሉም እጅጉን መሪር በሆነ ለቅሶ ሟችን የመሰናበት ማህበራዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ በጥናቱ የተደረሰበት ሌላው መሰረታዊ ነገር የሸካቾ ብሔረሰብ በቀብሩ ዕለት የሚፈፀመውን መሪር ሀዘን የሚያሳርገው "ጎሞ" በተባለ ባህላዊ ዘፈን እና ጭፈራ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ጭፈራ የሟችን እና የቤተሰቦቹን መልካም ገፅታዎች የሚያወሱ፣ ሞት ለሁሉም የቀረበ ግዴታ መሆኑን የተመለከቱ እና ሞት ዳግም የሟችን ቤተሰቦች እንዳይጎበኝ የሚመኙ ግጥሞች የሚደረደሩበት ነው፡፡

ጭፈራው በከበሮ፣ በክራር እና በጥሩንባ ታጅቦ የሚከወን ሲሆን ዓላማውም የሟች ቤተሰቦች ሀዘን እንዳይጎዳቸው ማድረግ እና "ሞት ሀዘን ሲበዛ ተደጋግሞ የሚመጣ በመሆኑ ሀዘኑ በቅቶን መደሰት ጀምረናል" የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው፡፡

ብሔረሰቡ ከሌሎች ማህበራዊ አጋጣሚዎቹ ይልቅ ለለቅሶ ስርዓቱ የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ መሆኑን እና ይህ አጋጣሚ ህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስሩን የሚያጠነክርበት፣ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን የሚገልጥበት፣ አስተሳሰቡን የሚያጎላበት፣ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶቹን እና እምነቱን የሚያፀናበትና ከትውልድ ትውልድ የሚያሸጋግርበት መድረክ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል፡፡

# አበርክቶ

እስከዛሬ በተለያዩ ጊዜያት ጥቂት የማይባሉ ጥሩም መጥፎም ነገሮች ገጥመውኛል፡፡ በህይወቴ ከገጠሙኝ ክፉ ነገሮች መካከል የማስተምርበት የጋምቤላ ኮሌጅ ተማሪዎች ፍፁም ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን "በሽፍቶች" መገደላቸው ፈፅሞ ከህሊናዬ ሊጠፋ ያልቻለ አሰቃቂ ድርጊት ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ መጋቢት 3/2004 ዓ.ም የሁለተኛ ሴሚስተር ትምህርታቸውን ለመከታተል ከጎደሬ ወደ ጋምቤላ በመጓዝ ላይ ሳሉ ጋምቤላ አካባቢ በሚገኙ "ተራ ሽፍቶች" በጥይት ተደብድበው እና በሳንጃ ተወጋግተው ለተገደሉ 17 የኮሌጃችን ተማሪዎች መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡

**መግለጫ**

በዚህ ርዕስ ስር መግለፅ የፈለኩት በጥናቱ ውስጥ የተገለገልኩባቸውን ምህፃረ ቃላት እና ዓመተ ምህረቶችን በተመለከተ ነው፡፡

ጥናቴን የተሳካ ለማድረግ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ምሁራንን ልዩ ልዩ ፅሁፎች እና ጥናቶች ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ እነዚህን ጥናቶች በምቃኝበት ወቅት በእንግሊዘኛ የተፃፉ ስራዎችን ዓመተ ምህረት የጠቀስኩት በአውሮፓውያን አቆጣጠር ሲሆን ሌሎች ሀገርኛ ስራዎችን ግን ጥናቶቹ ወይም ፅሁፎቹ የተገለገሉበትን የኢትዮያዊያን አቆጣጠርን ነው፡፡

አላስፈላጊ ድግግምን ማስወገድ ይቻለኝ ዘንድ አንዳንድ ተደጋጋሚ ጉዳዮችን በምህፃረ ቃል ጠቅሻለሁ፡፡ እነርሱም፡-

- ✓ ማ.ስ.ባ = ማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን፣
- ✓ የደ.ብ.ብ.ሕ.ፕሮፋይል = የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ፕሮፋይል፣
- ✓ ቃ.መ. = ቃለ-መጠይቅ፣
- ✓ የተ.ቡ.ው. = የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣
- ✓ ዓ.ም = ዓመተ ምህረት፣ . . .ወዘተ የሚሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም አንባቢ እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ጥናቴን ያነብልኝ ዘንድ አስቀድሜ ጠይቃለሁ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ለቅሶን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ሃዘን፡፡ ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፡፡ መጮህ፣ ማንባት፡፡ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ፡፡" (1993፣ 17) ሲል ይበይነዋል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሰዎች ከማህበሩ በሞት ሲለዩ አልቅሶ መቅበር በኢትዮጵያ በአብዛኛው የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ወገኑን አልቅሶ የሚቀብርበት ስርዓት ከብሔር - ብሔር፣ ከጎሳ - ጎሳ ሊለያይ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ አንዱ የሟቹን ልዩ ልዩ ገፅታዎች የሚያወሱ ግጥሞችን እየደረደረ ሙሾ በማውረድ ሲያለቅስ፣ ሌላው ደግሞ በለሆሳስ እንባውን ብቻ እያዘራ ቀብሮ የሚመለስ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ መልኩም ሞት የተከሰተው ምሽት ላይ ካልሆነ በስተቀር ሬሳ የማያሳድሩ እንዳሉ ሁሉ፣ ዘመድ - አዝማድ፣ ጎረቤት - ጓደኛ ከያሉበት ሰምተው በቀብሩ ዕለት እንዲገኙ ሁኔታዎችን እያመቻቹ ከወር በላይ ሬሳ የሚያቆዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም አሉ፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚገኙ ከ56 ከሚበልጡ የተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ብሔረሰብ ከሌሎቹ የሚጋራቸው የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች እንዳሉት ሁሉ፣ የብሔሩ መገለጫ የሆኑ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶችም አሉት፤ ከሚለዩት ባህላዊ መገለጫዎች መካከል የለቅሶ ስርዓት አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ማተኮር የወደደውም የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ያልተጠና ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የለቅሶ ስርዓቱን ከሞት እስከ ግበዓተ መሬት ድረስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት ተንትኖ ለማሳየት ያለመ ነው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በትምህርት ክፍሉ ከዚህ በፊት በሸካቾ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ሦስት የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቶች አሉ፡፡ እነሱም አማረ ሞላ በ1999 ዓ.ም “የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና”፣ ምህረት ካሳ በ2002 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና አመጋገብ ስርዓት" እና ስለሺ አባተ በ2002 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት" በሚል ርዕስ የሰሯቸው ጥናቶች ናቸው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የእኔ ጥናትም ቀዳሚዎቹ ጥናቶች ባተኮሩበት ብሔረሰብ ላይ አተኩሮ፤ ነገር ግን በተለየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚሰራ ጥናት ነው፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

#### 1.2.1. ግላዊ ምክንያት

ዛሬም ድረስ ለእናቴ ያለኝን መውደድ የሚገዳደረው አላገኘሁም፡፡ ይህ ስሜቴ ደግሞ በቀደሙት ዘመናት እጅጉን የላቀ ነበር ለማለት እደፍራለሁ፡፡ ምክንያቱም ከኮሌጅ ተመርቄ ወጥቼ እንኳ ስራ የያዝኩት ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ እንደመሆኑ መጠን ከእናቴ ተለይቼ ብዙ ጊዜዬን ያሳለፍኩባቸው ጊዜያት ውስን የነበሩ በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ የረጅም ጊዜ አብሮነት ውስጥ ደግሞ እናቴ ከምትሰራልኝ ምግብ ውጭ መመገብ ምርጫዬ አልነበረም፡፡ 1991 ዓ.ም ግን ይህንን ሁኔታ ለእኔ አጭር ለማይባል ጊዜ ገታው፤ የእናቴ አባት (ሽውራሻ አንገሎ ጋሜ) በእርጅና ምክንያት በማረፋቸው ሳቢያ እናቴ ከቤታችን 97 ኪሎ ሜትር ርቆ ወደሚገኘው የአባቷ ሀገር ማሻ የለቅሶውን ስርዓት በሀገሬው ደንብ መሰረት ደግሳ ልትወጣ ሳትነግረኝ ሄደች፡፡ መሄዷ ደርሶ ለመመለስ ቢሆን ባልከፋ ነበር ነገር ግን ከወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚያቆያት መሆኑን ማወቄ በእኔ እና ቤት ውስጥ አብረውኝ ካሉት ታላላቅ እህቶቼ እና አባቴ መካከል ስምምነት ሊፈጠር አልቻለም፡፡

እናቴ ባህሉ የሚፈቅደውን ሁሉ አድርጋ ስትመለስ ለምን ጥላኝ ሄዳ ይህን ያህል እንደቆየች በተከፋው ስሜቴ ስጠይቃት "የእኛ የለቅሶ ስርዓት እንደ አባትህ ዘመዶች ዘመድ አዝማድ ሳይሰበሰብ እና ተደግሶ ሳይበላ የሚፈፀም ባለመሆኑ ነው ተሎ ልመለስ ያልቻልኩት፡፡" ያለችኝ ነገር በወቅቱ ብዙም ያልገባኝ ነገር ግን እናቴን ለጊዜው ነጥቆኝ ክፉ ስሜት ውስጤ ያሳደረ በመሆኑ ምንነቱን ግልፅ ባለ ሁኔታ የማወቅ ጉጉት በውስጤ ተዳፍኖ ኖሯል፡፡ ይህን የተዳፈነ ስሜት የሚቆሰቁስ ሌላ አጋጣሚ ተፈጠረ፤ ጳጉሜ 3/2005 ዓ.ም ለበዓል በሄድኩበት ጊዜ እናቷ ታመው እሳቸውን ለማስታመም ወደ ማሻ መሄዷ ተነገረኝ፡፡ የአያቴ መታመም ሳይሆን ከ5 ወር በላይ ያላየኋት እናቴን በዘመን መለወጫ ዕለት እንኳ ላገኛት አለመቻሌ ዳግም ስለ እናቴ ዘመዶች የለቅሶ ስርዓት እንዳስብ አድርጎኛል፡፡ በዚህ ምክንያት የኤም. ኤ. ዲግሪ ልዩ ልዩ ኮርሶችን በምንወስድበት ወቅት በተለያዩ መምህራን የምናውቀው ነገር (ባህል) ላይ መስራት ጠቃሚ መሆኑን ተደጋግሞ የተነገረን ሀቅ ታስቦኛል፡፡ በመሆኑም የእናቴ ዘመዶች የለቅሶ ስርዓት ላይ የመመረቂያ ፅሁፌን መስራት ሊያዋጣኝ ይችላል ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡

### 1.2.2. አካዳሚያዊ ምክንያቶች

ከፍ ሲል የጠቀስኩት ቀዳሚ ምክንያት በውስጤ እንደተፈጠረ ያለኝን ጥቂት የረፍት ጊዜ በመጠቀም "እናቴን አይቼ፣ አያቴንም ጠይቄ እመለሳለሁ" በሚል ሰበብ መስከረም 8/2006 ዓ.ም ወደ ማሻ አቀናሁ፡፡ በዚህ ወቅት አያቴ በምትኖርበት "አበሎ" ከተባለ መንደር በአካል ተገኝቼ የለቅሶ ስርዓቱን በተመለከተ አንዳንድ መረጃዎችን ኢ-መደበኛ በሆነ ቃለ መጠይቅ ላሰባስብ ችያለሁ፡፡ መረጃውን በማሰባስብበት ወቅት እንደ ፎክሎር ተማሪ ያሳሰበኝ ነገር "አሁን ላይ ግን የተለያዩ ኃይማኖት አባቶች እየከለከሉ በመሆናቸው ሬሳ የማቆየት ስርዓቱም ሆነ ደረት እየደቁ፣ እየወደቁ እየተነሱ፣. . .ማልቀሱ እየቀረ ነው፡፡" የሚለው ምላሻቸው ነበር፡፡ በመሆኑም ይህ የለቅሶ ስርዓት ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ምን እንደሚመስል በተለያየ መንገድ ቀርሶ ለትውልድ ለማቆየት መጣር ለነገ የማይባል ተግባር መሆኑን ማመኔ ሌላኛው ምክንያቴ ነው፡፡

ይህን ርዕስ ለትምህርት ክፍሉ ከማስገባቴ በፊት "ተሰርቶበት ይሆን" የሚል ስጋት አድሮብኝ የነበረ ቢሆንም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሚገኙ ቤተ-መፅሐፍት ውስጥ ባደረኩት ዳሰሳ ያልተሰራበት ርዕስ መሆኑን አጣርቻለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃን በወረቀት ብቻም ሳይሆን በአዕምሮ በአግባቡ ሰንዶ በመያዝ ለእኔ ወደር ከማይገኝላቸው አንድ መምህሬ ዘንድም ዘልቄ በርዕሱ ያልተሰራበት መሆኑን አስረግጠውልኛል፡፡ በመሆኑም ርዕሰ ጉዳዩ ፈፅሞ ከመጥፋቱ በፊት ሊቀረስ የሚገባው መሆኑን በማመን በርዕሱ ልሰራ ወሰንኩ፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜው ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት መግለፅና መተንተን ነው፡፡ ከዚህ ዋና ዓላማ በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- ✓ የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ሂደትና አጠቃላይ ከዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት፣
- ✓ የለቅሶ ስርዓቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ደረጃዎች እና ተፈጥሯዊ ገፅታዎች ሳቢያ በተለያየ አግባብ የሚፈፀም አሊያም አንድ መሆኑን ማመላከት፣

- ✓ በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶችን እና የተለያዩ ትዕምርቶችን መተርጎም፣
- ✓ የአለቃቀስ ስርዓቱ መቼ፣ እንዴት እና በምን አይነት ከበራዎች ታጅቦ እንደሚቀርብ መግለፅ፣
- ✓ ከለቅሶ ስርዓቱ ጋር በተያያዘ ያሉትን የማህበረሰቡን እምነቶች መተንተን፣

### 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ከፍ ሲል የቀረቡትን የጥናት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- ✓ የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት አጠቃላይ ሂደት ምን ይመስላል ?
- ✓ በብሔረሰቡ ውስጥ ባሉ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ደረጃዎች እና ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ሳቢያ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔው ይለያያል ወይስ አንድ ነው ?
- ✓ የለቅሶ ስርዓቱን ተከትሎ ያሉት እምነቶች እና አስተሳሰቦች ምንድናቸው ?
- ✓ በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ከበራዎች ፋይዳ ምንድነው ?

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት መደረጉ ለተለያዩ አካላት የሚያበረክተው ጠቀሜታ አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ መካከል ለባህሉ ባለቤቶች፣ ለተመራማሪዎች እና በሀገር ደረጃ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል፡፡

#### 1.5.1. ለባህሉ ባለቤቶች የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

የሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ላይ ጥናት መደረጉ ለስርዓቱ ባለቤቶች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል የሚል እምነት አለ፡፡

- ✓ "በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል" እንዲሉ ይህንን ስርዓት ብዙም ትኩረት ባለመስጠት ቸል ብለውት የነበሩት የብሔረሰቡ አባላት ቢኖሩ "ከሞት እስከ

ግብኣተ መሬት ድረስ ያለው የለቅሶ ስርዓታቸውን" በውል እንዲያጤኑት መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል፣

- ✓ ይህን ጥናት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያነበው ሰው በመኖሩ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሸካቾን ባህል የማስተዋወቅ ረብ ይኖረዋል፣
- ✓ ጥናቱ ሲደረግ ባህሉን ከሚያውቁ የብሔረሰቡ አባላት መረጃ በአግባቡ ተሰብስቦ፣ ምልከታ ተደርጎበት እና ውይይትም ተካሂዶበት ነው፡፡ በመሆኑም በስርዓቱ ላይ የተጋረጠው የመጥፋት አደጋ እውን ቢሆን "የለቅሶ ስርዓታችን ይህን ይመስል ነበር" ብለው ማስረዳት ይችሉ ዘንድ አብነት ይሆናቸዋል፡፡

### 1.5.2. ለተመራማሪዎች የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት በተለያየ መልክ ጥናትና ምርምር ማድረግ ለሚሹ አካላት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

- ✓ በዘርፉ ወይም የጥናቱ ትኩረት በሆነው ማህበረሰብ ዙሪያ ከዚህ ሰፋ ያለም ሆነ የጠበበ ጥናት ማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች የተወሰነ መረጃ ይሰጣል፣
- ✓ በአንድ ወቅት ይከወን የነበረ አሊያም አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የፎክሎር አይነት በጊዜ ብዛት በአንዳች አስገዳጅ ምክንያት የተወሰነ መልኩ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊቀየር፣ ሊጠፋ የሚችል በመሆኑ በዘርፉ የሚካሔድ ማንኛውም ጥናት ለትውልድ የሚያተርፈው በጎ ገፅታ አለው፡፡ በመሆኑም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" በተለያዩ ምክንያቶች የመጥፋት አደጋ ቢገጥመው ይህ ጥናት መደረጉ አወንታዊ ጎን አለው፣

### 1.5.3. በሀገር ደረጃ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

- ✓ ማንኛውም አካል ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ውይይት ማድረግ ቢፈልግ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ማስፈፀም ቢሻ በተወሰነ መልኩ የህብረተሰቡን ማንነት እና አመለካከት ተረድቶ እራሱን እና መመሪያዎቹን ጥናቱ ከሚጠቁመው የማህበረሰቡ እምነት እና አመለካከት አንፃር እንዲያደራጅ የተወሰነ መረጃ ይሰጣል፣

- ✓ አካባቢው ብዙም የቱሪስት ፍሰት ጎልቶ የማይስተዋልበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህ ጥናት በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች የመሰራጨት እድሉን ካገኘ ጎብኚዎች ፊታቸውን ወደ ባህሉ ባለቤቶች እንዲያዞሩ ያነሳሳ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

**1.6. የጥናቱ ወሰን**

የሸካቾ ብሔረሰብ በተለያዩ አካባቢዎች በስፋት የሚገኝ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን የተደረገው የብሔረሰቡ ዋንኛ መገኛ በሆነው በማሻ ከተማ እና በዙሪያዋ ባሉ አጎራባች ቀበሌዎች ነው፡፡ ምክንያቱም በሌሎች አካባቢዎች የሚኖሩት የሸካቾ ብሔረሰብ አባላት ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ በመሆናቸው የለቅሶ ስርዓታቸው የተቀላቀለ ሊሆን ይችላል ከሚል ስጋት ነው፡፡ ማሻ፤ በተለይም በዙሪያዋ ያሉት ቀበሌዎች (ለምሳሌ አበሎ፣ አተሶ፣ ይና፣ ጋዳ፣ ሾበቻ፣. . .) ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍርበት አግባብ የብሔረሰቡ አባላት ብቻ የሚኖሩበት መሆኑን የሸካ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ፅ/ቤት የመረጃ አገልግሎት ባለሙያ የሆኑት አቶ አስታውሰኝ በቃሉ (ቃ.መ. 16/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ አካባቢዎቹ ሊመረጡ የቻሉት የሌሎች ባህሎች ተፅእኖ እምብዛም ያላረፈበትን ስርዓት ለማግኘት ያስችላል ከሚል ፅኑ እምነት በመነጨ ነው ፡፡ ይሁን እንጂ መረጃ ለመሰብሰብ ከየካቲት 12/06 ዓ.ም እስከ መጋቢት 17/06 ዓ.ም ድረስ በዞኑ ዋና ከተማ ማሻ በነበርኩባቸው ቀናቶች ውስጥ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ቀበሌዎች ውስጥ ለእኔ ጥናት የሚስማማ የለቅሶ ስርዓት የሚስተዋልበት ሞት የተከሰተው በአበሎ እና በይና ቀበሌዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ወሳኝ ግብዓቶች በምልከታ የተሰበሰቡት ከእነዚህ ሁለት ቀበሌዎች ነው፡፡

ይህ ጥናት የሚመለከተው ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"ን ነው፡፡ የሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት እንደአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የለቅሶ ስርዓት ሁሉ እድሜን፣ ፆታን፣ ማህበራዊ ደረጃን እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን መሰረት አድርጎ በአንዳንድ የአከዋወን ስርዓቶቹ ላይ የሚለያዩ ነጥቦች ይስተዋሉበታል፡፡ ይሁን እንጂ የሸካቾ ብሔረሰብ ሰፋ ያለ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት የሚያከናውነው አንድ አይነት ባህላዊ የስልጣን ባለቤት ለሆኑት እና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ከፍ ላለ የህብረተሰብ ክፍሎች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ጥርስ ያላበቀለ ህፃን ልጅ ሲሞት የሚኖረውም ስርዓትም የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት እነዚህ ለየት ተደርገው የሚታዩት እና ሰፋ ባለ መልኩ የሚከበሩት የለቅሶ ስርዓቶች ላይ በማተኮር የሌሎቹን የህብረተሰብ ክፍሎች የለቅሶ ስርዓቶች በአለፍ ገደም

በማንፀሪያነት በማንሳት አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓቱ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ይህ ማለት ግን በእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል የለቅሶ ስርዓት ላይ በአካል በመገኘት መረጃ ተሰብስቧል ማለት አይደለም፤ ይህን ለማድረግ ካለው ጊዜ አንፃር ተፈጥሯዊ መቼቱ ያልተገኘ በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ ይልቁንም ባለኝ ጊዜ ውስጥ በተከሰቱት ሁለት የለቅሶ ስርዓቶች ላይ በአካል ተገኝቼ ያደረኩትን ምልከታ ተመርኩዤ እና ስለባህሉ በጥልቀት ያውቃሉ ከተባሉ የብሔረሰቡ አባላት ጋር ካደረኩትን ቃለ-መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ያገኘሁትን መረጃ መሰረት በማድረግ "ከሞት እስከ ግብኣተ መሬት ፍፃሜው ድረስ" ያሉትን ልዩ ልዩ ስርዓቶች ተንትኜ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡ ይህ ጥናት ከኃይማኖት አንፃር እራሳቸውን "የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ነን" እያሉ የሚጠሩት ላይ አተኩሮ የተሰራ ነው፡፡

## 1.7. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የሚበጁት መረጃዎች የተሰበሰቡት በሁለት አይነት መንገድ ነው፡፡ ቀዳሚው ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት በቤተ መፃሕፍት ውስጥ በመገኘት በመስኩ እንዴት የተሳካ ጥናት ማድረግ እንደሚቻል የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን ከማንበብ ጀምሮ ከእዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በጥናት አካባቢ ምርጫ ዝምድና ያላቸውን ጥናቶች፣ የዚህን ጥናት ፅንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በተገቢው መንገድ ለመስራት የሚያስችሉ መረጃዎችን ከልዩ ልዩ መፃሕፍት፣ የመረጃ መረቦች እና ከተለያዩ ፅሁፎች በማሰባሰብ በመልክ በመልክ አደራጅቶ ማቅረብን የሚመለከት ነበር፡፡ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ መስክ ከመውጣቱ በፊት ምን ማድረግ እንደሚገባው ፈቃደ (1991፣ 124) ይጠቅሳል፡፡ ከዚህም በላይ እነ Sims እንደሚከተለው በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡ "Before going into the field, it is usually a good idea to conduct some preliminary research on your topic. You might talk with your instructor or someone you know has information on your topic to get some background information. You will also need to do some library research." (2004፣ 205)

ለየትኛውም የፎክሎር ተመራማሪ በተለይም ከዋኔ መር የትወራ ማዕቀፍን ተገልግሎ ጥናት ለሚያከናውን ተመራማሪ መስክ ወጥቶ ከአውዱ መረጃ ማሰባሰብ ተቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን እንደሚገባ Bauman (1992፣ 252) ይገልፃል፡፡

የመስክ ስራን ምንነት አስመልክቶ Jackson "Fieldwork done sanely is usually done in the service of some specific end; it's planned and deliberate." (1987፣ 13) በማለት የመስክ ስራ በዕቅድ እና በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚሰራ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ለአንድ የፎክሎር ተመራማሪ ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው ሲል ፈቃደ የሚጠቅሳቸው ምልከታ፣ ኢንተርቪው እና መጠይቅ ናቸው (1991፣ 90)፡፡ Kothari (2004፣ 96) በበኩሉ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን እና ሌሎች ዘዴዎችን ጭምር በሰፊው በመጥቀስ ለፎክሎር መረጃ መሰብሰቢያ እጅግ ወሳኝ መሆናቸውን ያብራራል፡፡ ለዚህ ጥናት በተመረጡት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት መረጃውም ሆነ መረጃ አቀባዮቹ የተመረጡት  በታላሚ የንሞና ስልት (Purposive sampling technique) ነው፡፡ እኔ ለዚህ ጥናት የተገለገልኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው፡፡ ስለሆነም ቀጥለን እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በዝርዝር እንመልከት፡፡

### 1.7.1. የምልከታ ዘዴ

በአውዳዊ ጥናት መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ አንዱ ነው፡፡ Gray ምልከታን አስመልክቶ ሲጽፍ ምልከታ አንድን ጉዳይ የመመልከት እና ማስታወሻ የመውሰድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጥኚውን አምስቱንም የስሜት ህዋሳቶች ቅንጅትን የሚጠይቅ ስራ ነው በማለት ያስረዳል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞም ምልከታ የሰዎችን ድርጊት በሰላ መንፈስ የመከታተልን ፣ ትእይንቱን በአግባቡ ቀርጾ የማስቀመጥን እና የተጠኚዎችን ባህሪ የመፈከርን እውቀት የሚጠይቅ መሆኑን አስፍሯል (2004፣138)፡፡

ከፍ ሲል የቀረበውን ሀሳብ Goldstein በበኩሉ እንደሚከተለው በግልፅ አስፍሯል፡፡

. . . obtaning data by direct observation, looking from the outside in and describing the situation as he sees it. The term 'observation,' as used in the context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experiance including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate. (1964፣ 77)

ከዚህም በተጨማሪ Goldstein ምልከታ ስናካሂድ በዋናነት ትኩረት ልንሰጥባቸው የሚገቡን ጉዳዮች የክዋኔው ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ፣ ከዋኝ፣ ተደራሲ፣ በሁለቱ መካከል

ያለው መስተጋብር፣ ቅርጽ፣ መቼት እና የሚከወንበት አጋጣሚ መሆናቸውን ገልጿል (1964፣ 92)፡፡

ምልከታ በሁለት አይነት መንገድ ሊከናወን እንደሚችል Kothari ይጠቅሳል፡፡ ይኸውም ተሳትፎአዊ እና ኢ-ተሳትፎአዊ በሆነ መልኩ ሊከወን የሚችል ሲሆን ተሳትፎአዊ የሚባለው አጥኚው የተጠኚው ማህበረሰብ አካል ሲሆን እና የሚጠናውን ባህል እና ቋንቋ የሚያውቅ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ኢ-ተሳትፎአዊ ምልከታ የሚባለው ደግሞ ተመራማሪው ስለሚያጠናው ማህበረሰብ ባህል የማያውቅ በመሆኑ ምክንያት ዳር ቆሞ የሚያየውን በሙሉ የሚመዘግብበት ሂደት የሚመለከት ነው (2004፣ 96)፡፡

የዚህ ጥናት ምልከታ የተካሄደው ተሳትፎአዊ በሆነ የምልከታ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም እናቴ የሽካቾ ብሔረሰብ አባል በመሆኗ ሙሉ በሙሉ ማለት ባይቻልም አብዛኛውን ባህሉን አውቃለሁ፣ ቋንቋውንም እችላለሁ፡፡ በመሆኑም Kothari አንድ ሰው የራሱን (የሚያውቀውን) ባህል ቢያጠና እጅጉን ተመራጭ ቢሆንም የብሔረሰቡ አባል እንደመሆኑ መጠን ባህሉን ከፍ ከፍ ከማድረግ፣ አንዳንዶቹን መረጃዎች ብዙም አይጠቅሙም በሚል አሊያም አደባባይ ባይወጡ ከሚል ስሜት እንዳያልፋቸው፣. . .ወዘተ ተጠንቅቆ ጥናቱን ማከናወን ይኖርበታል (2004፣ 96) የሚላቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት በተሳትፎአዊ ምልከታ ጥናቴን ላከናውን ችያለሁ፡፡

ምልከታን የተገለገልኩት የለቅሶ ስርዓቱን ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው በአግባቡ ተመልክቶ እያንዳንዱን የአከዋወን ሂደት በስርዓት ተንትኖ ለማቅረብ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ምልከታዬን ያከናወንኩት ከቀን 20 እስከ 24/06/06 ዓ.ም በአበሎ ቀበሌ በመገኘት ነው፡፡ ከውልደታቸው ጀምሮ እስከ ህልፈታቸው ድረስ በቀበሌው ይኖሩ የነበሩ ወ/ሮ አፀደ ዴግራሻ የተሰኙ የ87 ዓመት አዛውንት ያሉበት ሁኔታ በአስጊ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን የተረዱ የአካባቢው ሰዎች ደውለው ባሳወቁኝ መሰረት በቀን 20/06/06 ዓ.ም ረፋድ ላይ ህይወታቸው ከማለፉ በፊት በአካባቢው ተገኝቼ ቀብሩ እስከተፈፀመበት የካቲት 24/06 ዓ.ም ድረስ ከማሻ 35 ደቂቃ የሚፈጀውን መንገድ እየተመላለስኩ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ልሰበስብ ችያለሁ፡፡

ሁለተኛው ምልከታዬ የተካሔደው ከየካቲት 27/06 ዓ.ም እስከ መጋቢት 02/06 ዓ.ም ይና ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡ በቀበሌው ታዋቂ የሆኑ አቶ አምበሎ አደዎ የተሰኙ የ72 ዓመት አዛውንት የካቲት 26/06 ዓ.ም ምሽት ላይ ማረፋቸው ተደውሎ እንደተነገረኝ ሞተር ሳይክል ተከራይቼ

ማረፊያዬን ካደረኩበት ማሻ ከተማ ተነስቼ ከጠዋቱ 12፡45 አካባቢ በቀበሌው በመድረስ ለስድስት ቀናት ያህል የቆየውን ስርዓት በአግባቡ በመመልከት መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ቀደም ሲል በመግቢያው በሸካቾ ብሔረሰብ አንድ የኢኮኖሚያዊ አቅሙ ከፍተኛ የሆነ እና ማህበራዊ ቦታው ከፍ ያለ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የቀብር ስርዓቱ ከመፈፀሙ በፊት ከ1 አስከ 3 ወር ሊቆይ እንደሚችል ገልጫለሁ፡፡ ነገር ግን በመረጃ ስብሰባ ወቅት እኔን የገጠሙኝ ሁለቱም የለቅሶ ስርዓቶች ይህን ያህል ቆይታ ያልተደረገባቸው ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት የሚነሳው የመሰረተ ልማት አውታሮች በመስፋፋታቸው መረጃዎችን በቀላሉ ተለዋውጠው ሁሉም በለቅሶው ላይ እንዲገኙ ምቹ ሁኔታዎች ያሉ በመሆናቸው እና ፈጥነው የሚደርሱ የምግብ አይነቶች በህብረተሰቡ ዘንድ እየተለመዱ በመምጣታቸው መሆኑን መረጃ አቀባዮቼ ይጠቅሳሉ፡፡

### 1.7.2. የቃለ-መጠይቅ ዘዴ

ቃለ-መጠይቅ በአጥኚው እና በመረጃ አቀባዩ መካከል በቃል የሚካሄድ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ Gray ይህንን ሀሳብ "An interview is a conversation between people in which one person has the role of researcher. Very often, the interviewer will have on hand a set of written questions which are posed in a structured and methodical fashion." (2004፤ 213) በማለት ያጠናከረዋል፡፡

ቃለ-መጠይቅ አይነቶቹ የተለያዩ እና አጠቃቀማቸውም አንድ አይነት አለመሆኑን Gray ይጠቅሳል፡፡ አምስቱ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች ሲል Gray የሚጠቅሳቸው የተገደበ ቃለ-መጠይቅ (structured interview)፤ ከፊል የተገደበ ቃለ-መጠይቅ (semi-structured interview)፤ ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (non-directive interview)፤ ተተኳሪ ቃለ-መጠይቅ ( focus interview ) እና መደበኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (informal conversational interview ) ናቸው (2004፤ 215 -217)፡፡ ከእነዚህ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች መካከል እኔ ለዚህ ጥናት ይስማማሉ ብዬ በመምረጥ የተገለገልኩባቸው ከፊል የተገደበ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የቃለ- መጠይቅ አይነቶችን የGrayን ሀሳብ ተመርኩዤ እንደሚከተለው አብራራለሁ፡፡

✓ ከፊል የተገደበ ቃለ-መጠይቅ (semi-structured interview)፡- ይህ ዘዴ አጥኚው የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች በከፊል ተዘጋጅቶባቸው እና አስበባቸው የሚያቀርብበት ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በሚቀርቡበት ወቅት ከመረጃ አቀባዩ የሚመጡ አዳዲስ ሀሳቦች ካሉ ለመቀበል በከፊል ዝግጁ የሚሆንበት እና ተጨማሪ ጥያቄዎችንም ለመጠየቅ የሚቻልበት ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪም አጥኚው በቅደም ተከተል ያዘጋጃቸውን ጥያቄዎች አፋልሶ በሚመቸው መንገድ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

✓ ቀጥተኛ ያልሆነ ቃለ-መጠይቅ (non-directive interview)፡-ይህ የቃለ-መጠይቅ ቴክኒክ አጥኚው የሚጠይቃቸውን ሰዎች ከማግኘቱ በፊት ጥቂት ጥያቄዎችን ብቻ በመያዝ ከምልልሱ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያመነጭበት እና የሚጠይቅበት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ለአጥኚው እና ለመረጃ ሰጪው ሰፊ ነጻነት በመስጠት ጥሩ የሆነ መግባባት የሚፈጠርበት ነው፡፡ መረጃ ሰጪው የሚፈልገውን መረጃ ሰጠም አልሰጠም ሳይቋረጥ ሀሳቡን እንዲጨርስ ማድረግ ግድ የሚሆንበት ነው፡፡ ለዚህም ነው ይህንን ዘዴ የሚጠቀም አጥኚ በመጠይቁ ወቅት የተነሳበትን ርእሰ ጉዳይ እንዳይስት ጥንቃቄ እንዲያደርግ የሚመከረው (2004፣ 215-217)፡፡

እነዚህ ሁለት የቃለ-መጠይቅ ቴክኒኮች የተመረጡበት ዋንኛ ምክንያት የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሰፊ ምላሾችን ሊያስገኙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ በመሆናቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ጠያቂውም ሆነ መላሹ ዘና ባለ መንፈስ አማናዊ በሆነ ድባብ ውስጥ ሆነው ያሻቸውን መረጃ እንዲለዋወጡ ሰፊ ነፃነት የሚሰጡ ቴክኒኮች ስለሆኑ ነው፡፡

ቃለ-መጠይቅን በአብዛኛው የተጠቀምኩት ስለ ህብረተሰቡ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት፤ የአለቃቀስ ስርዓቱን ቀድሞ ለመረዳት፣ የለቅሶ ስርዓቱ እንዴት እና መቼ በዚህ መልክ መከወን እንደተጀመረ ለማወቅ፣ በማህበሩ ውስጥ በሚኖሩ ልዩነቶች ሳቢያ የአለቃቀስ ስርዓቱ የሚለያይ መሆን አለመሆኑን ለማስረገጥ፣ ስርዓቱ በዚህ መልክ መከወኑ ለማህበሩ ያስገኛል ተብሎ ስለሚታሰበው ጠቀሜታ ለመለየት፣ ስለ ሞት ያላቸውን አመለካከት ለመገንዘብ፣ ስርዓቱ በዚህ መልክ ሳይከወን ቢቀር በማህበሩ ውስጥ ምን ሊከሰት ይችላል ተብሎ እንደሚታመን ለመመርመር፣. . .ወዘተ ያሉ መረጃዎችን በአግባቡ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ሸካቾ ብሔረሰብ ባህል ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው ከሚታመንባቸው ሰባት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና ሦስት ተጨማሪ መረጃ ሰጪ አካላት ጋር ዘርዘር ያለ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ በቂ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

#### 1.7.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የተተኳሪ ቡድን ውይይት በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉ፣ ግልፅ ያልሆኑ፣ ማብራሪያ የሚፈልጉ፣. . .ወዘተ መረጃዎችን "ስለ አለቃቀስ ስርዓቱ በሚገባ ያውቃሉ" ከተባሉ ልዩ ልዩ አካላት ጋር ከተደረገ ውይይት መረጃዎችን አሟልቶ በመገኘት እርግጠኛ እና ሁሉ አቀፍ

መረጃ ለማግኘት ተገልግዬበታለሁ፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ የተደረገው ከአምስት ወንዶች እና ከአራት ሴቶች በድምሩ ከዘጠኝ ቁልፍ የባህል አዋቂዎች ጋር ነው፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይትን ተጠቅሞ በርካታ እና አስተማማኝ መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማግኘት እንደሚቻል እነ Schensul (1999፣ 52) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ይህንን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተገልግዬ የህብረተሰቡን ባህል ጠንቅቀው ከሚያውቁ የተለያዩ አካላት ጋር በመወያየት ልዩ ልዩ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡

እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በምጠቀምበት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት በፈቀዱልኝ ልክ እና አግባብ መቅረፀ ድምፅ፣ ምስል (የፎቶ ግራፍ ካሜራ) ተጠቅሜአለሁ፡፡ በተጨማሪም አጫጭር ማስታወሻ መያዝ የየዕለት ተግባሬ ነበር፡፡

### 1.8. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልክ ያገኘኋቸውን መረጃዎች በመልክ በመልክ አደራጅቼ ተንትኜ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ፡፡ መረጃዎቹን የተነተንኩት ከበራን (Ritual) መሰረት አድርጌ እና በክዋኔ መር ንድፈ ሃሳብ (Performance centered approach) በመመራት ገላጭ (Descriptive) እና የይዘት ትንተና (Content Analysis) ዘዴዎችን ተጠቅሜ ነው፡፡ ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን የመረጥኩት የለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚኖረውን ልዩ ልዩ ክዋኔ (ለቅሶውን፣ ደረት መድቃቱን፣ መውደቅ መነሳቱን፣ ፀጉር መንጩቱን፣ ፊት መቧጠጡን፣. . .) ስዕላዊ በሆነ መልኩ መግለፅ የሚያስችለኝ ስልት በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የይዘት ትንተና ስልትን አጣምሬ መጠቀምን የወደድኩት በለቅሶው ክዋኔ ወቅት የሚባሉ (የሚደረደሩ) ሙሾዎችን እና ተያያዥ ጉዳዮችን ይዘት መተንተን እንዲያስችለኝ ነው፡፡

ትንተና በማደርግበት ወቅት መረጃዎችን ያደራጀሁት ማህበረሰቡ ለዘመናት ሲጠቀምበት በኖረው የቅድመ ሞት፣ የጊዜ ሞት እና የድህረ ሞት ጊዜ ክዋኔ ተመርቼ እንዲሁም ለአንዳንድ ስርዓቶቹ የሚሰጣቸውን ባህላዊ መጠሪያዎች ተመርኩዤ ነው፡፡

### 1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ የተደራጀው በአምስት ምዕራፎች ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ "መግቢያ" በሚል አቢይ ርዕሰ ጉዳይ ስር የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ ዓላማ፣ ጥያቄዎች፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ የመረጃ

መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ፣ አደረጃጀት፣ የመስክ ተሞክሮ እና ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው የሚሉ አስራ አንድ ጉዳዮችን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ምዕራፍ ሁለት "ክለሳ ድርሳናት"ን ይዟል፡፡ "የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት" በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ስር "የለቅሶ ስርዓት ላይ" እና "ብሔረሰቡ ላይ" ያተኮሩ ከቢ.ኤ እስከ ኤም.ኤ ዲግሪ ያሉ ጥናቶች እና ልዩ ልዩ ፅሁፎች ተዳሰዋል፡፡

"ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ" በሚለው ሌላኛው ንዑስ ስር ደግሞ ከበራን፣ ከዋኔን፣ ሞትን፣ ልዩ ልዩ ስርዓቶችን፣ የማህበረሰብ ዕውቀትን፣. . . ወዘተ የተመለከቱ የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች እና ፅንሰ ሃሳቦች በአግባቡ ተቃኝተዋል፡፡

በምዕራፍ ሦስት "የሸካቾ ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ" በሚል ርዕስ የብሔረሰቡ ማንነት፣ እውቀት፣ ልማድ፣ ባህል፣ የሚተዳደርባቸው አበይት የገቢ ምንጮች እና የኑሮ መሰረቶች፣ የንግስና ስርዓት፣ የጎሳ አይነቶች፣ የጋብቻ ስርዓት፣. . .ወዘተ የአለፍ ገደም መረጃን መሰረት በማድረግ በአጭሩ ተገልፀዋል፡፡

ምዕራፍ አራት የጥናቱ ዋንኛ ክፍል "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"ን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ መረጃዎች በተለያዩ አግባቦች ተዋግነው በመቅረብ ሰፋ ባለ መልኩ ትንተና የተደረገበት ክፍል ነው፡፡

ምዕራፍ አምስት በጥናቱ የተደረሰባቸው ግኝቶች እና ማጠቃለያ የቀረበበት ነው፡፡ በመጨረሻም የተጠቀሱ ምንጮች ዝርዝር እና አባሪ በማካተት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

### 1.10. የመስክ ተሞክሮ

ይህ ጥናት አተኩሮ ወደ ሚሰራባቸው የጥናት ቦታዎች የተደረገው ጉዞ በሚከተለው መልኩ የተከናወነ ነው፡፡ ከፍ ሲል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቼን ባብራራሁበት ክፍል መግቢያ ላይ እንደገለፅኩት ለዚህ ጥናት የሚበጀኝን መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ከመውጣቴ አስቀድሜ በቤተ መፃሕፍት በመገኘት የማጠናበትን ርዕሰ ጉዳይ እና ብሔረሰብ የተመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ከአማካሪዬ ጋር በመናበብ በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከመስክ መረጃ የምሰበስብበት ጊዜ እየተቃረበ በመሆኑ ለቃለ-መጠይቅ እና ለተተኳሪ ቡድን ውይይት መነሻ የሚሆኑኝን ጥያቄዎች አስቀድሜ በማዘጋጀት ለዚሁ ተግባር አጋዥ

የሚሆኑኝን የቪዲዮ እና ፎቶ ካሜራ፣ የቴፕ ካሴት እና ልዩ ልዩ የፅህፈት መሳሪያዎችን በግዢ እንዲሁም መቅረፀ ድምፅ በውሰት በማዘጋጀት ጥር 29/2006 ዓ.ም የመስክ ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡

ጥር 29/06 ዓ.ም ዕለተ ሀሙስ ጠዋት ከአዲስ አበባ -ቴፒ በሚጭነው ሀገር አቋራጭ አውቶብስ ተሳፈሬ ጉዟችንን ጀመርን፡፡ 5፡15 ላይ ወልቂጤ ለቁርስ ከነበረን የ30 ደቂቃ ረፍት ውጪ ምንም ጊዜ ሳናባክን በርካታ ታዳጊ ከተሞችን አቋርጠን 10፡10 ሲል ጅማ ገባን፤ አዳራችንም እዚያው ሆነ፡፡

ጠዋት ልክ ከማለዳው 12፡00 ሲል አውቶብሳችን ጅማን ለቆ ጉዞ ወደ ቴፒ ሆነ፡፡ ሰቃ፣ ሸቤ እና ጊንቦን ተሻግሮ 3፡40 ላይ የከፋ ዞን ዋና ከተማ የሆነችው ቦንጋ ላይ የ30 ደቂቃ የቁርስ እረፍት ካደረግን በኋላ ጉዟችንን ተያያዝነው፡፡ የአውቶብሳችን መድረሻ ወደ ሆነችው ቴፒ ለመግባት በሚደረገው ጥድፊያ ውስጥ ውሸውሸ፣ ወሺ፣ ዲንቢራ፣ ሸሽንዳ፣ ቢጣ፣ አዳ፣ በጪ፣ ኩራ፣ ፊዴ፣ ሾሻ፣. . .ወዘተ የተሰኙ የገጠር ከተሞችን አቋርጠን ማለፍ ነበረብን፡፡ የአስፓልቱ መንገድ የሚያልቀው ሸሽንዳ ላይ በመሆኑ ከዚያ በኋላ ያለው የ 76 ኪሎ ሜትር መንገድ እጅጉን ፈታኝ የሆነ የኮረኮንች መንገድ ነው፡፡ ዝናብ በሆነ ጊዜ መኪናዎች በጭቃ እየተያዙ መንገዱን በየቦታው የቆፋፈሩት በመሆኑ ለአዲስ መንገደኛ መኪናው አቅጣጫ የሳተ ሊመስለው ሁሉ ይችላል፡፡ ይህን አስቸጋሪ መንገድ ተጉዘን ቴፒ ለመግባት ከጅማ - ሸሽንዳ ያለው በእጥፍ ኪሎ ሜትር የሚበልጠውን መንገድ ከፈጀው ጊዜ ይልቅ ወስዶብን 9፡50 ሲል ቴፒ ገባን፡፡

ከአውቶብስ እንደወረድኩ እዚያው መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በመሳፈር ጉዞዬን ያደረኩት 17 ኪሎ ሜትር ከቴፒ ርቃ የምትገኘው የቤተሰቦቼ መኖሪያ የሆነችው ሜጢ ከተማ ነው፡፡ ሜጢ ተወልጄ ያደኩበት ከመሆኑም በላይ ቤተሰቦቼ የሚገኙበት እና የተለያዩ ማህበራዊ ግዴታዎችን መወጣት የሚጠበቅብኝ በመሆኑ የተወሰኑ ቀናትን እዚያው ላሳልፍ ተገድጃለሁ፡፡

የካቲት 12/06 ዓ.ም 12፡00 ሰዓት ላይ ከሜጢ ተነስቼ ጉዞዬን መረጃ ወደምሰበስብበት ማሻ ከተማ አደረኩ፡፡ ማሻ የደረስኩት ረፋድ 4፡00 ሰዓት አካባቢ ሲሆን አስቀድሜ የደወልኩለት እዚያ የሚኖር የቤተሰቤ አባል ከመነኻሪያ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወሰደኝ፡፡ በዘመዶቼ ቤት ተዘጋጅቶ የጠበቀኝን ቁርስ በልቼ የተወሰነ ከተጨዋወትን በኋላ ከትምህርት ክፍሌ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ ይዤ ወደ ሸካ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት ሄድኩ፡፡ የሸካ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አዝመራው በትህትና ከተቀበሉኝ በኋላ የመጣሁበትን ጉዳይ እንዳስረዳ እድል ሲሰጡኝ የያዝኩትን ደብዳቤ በማቀበል የጥናቴን ርዕስ እና ዓላማ በማብራራት ለዓላማዬ ስኬት ምን አይነት መረጃ፣ ከነማን እና

እንዴት እንደምፈልግ በአግባቡ አስረድቻለሁ፡፡ አስተዳዳሪው በፅሞና ካደመጡኝ በኋላ በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል ላይ ለመስራት በመወሰኔ የተሰማቸውን ደስታ ገልፀውልኝ ከምፈልጋቸው መረጃዎች ላይፈቀድልኝ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት በመጠቆም ደብዳቤዬን ለዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ፅ/ቤት መርተውልኛል፡፡

የዞኑ ባህል እና ማስታወቂያ ፅ/ቤት ኃላፊ ደብዳቤዬን ተቀብለው ወደሚመለከተው ባለሙያ መሩልኝ፡፡ አቶ አስታውሰኝ በቃሉ የዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ባለሙያ ሲሆን ደብዳቤዬን ካሳየሁት በኋላ የጥናቴን ዓላማ እና አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦችን በዝርዝር አስረድቼው በጉዳዩ ዙሪያ መነጋገር ጀመርን፡፡ ይህን አስመልክቶ የተሻለ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉትን አካላት ዝርዝር ሰጠኝ፡፡ በዞኑ ከርእሰ ጉዳዬ ጋር እና ከአንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ መረጃዎች ካሉ እንዲያውሰኝ ስጠይቀው ምንም አይነት የተደራጀ መረጃ አለመኖሩን በመጥቀስ ትኩረታቸው ቱሪስቶችን እና ኢንቬስተሮችን መሳብ ላይ አድርገው በፅ/ቤታቸው ቀደም ሲል የተዘጋጁ ሁለት መፅሔቶችን ሰጥቶኝ እና ለማሻ ወረዳ ባህል እና ማስታወቂያ ቢሮ የትብብር ደብዳቤ ፅፎልኝ ለሌላ ቀን ቀጠሮ በመያዝ ተለያየን፡፡

የሥራ ሰዓት ተጠናቆ ስለነበር ለወረዳ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በመያዝ ወደ ዘመዶቼ ቤት አቀናሁ፡፡ ቀደም ብዬ ስለምመጣበት ርዕሰ ጉዳይ አሳውቄያቸው ስለነበር ርዕሰ ጉዳዩን አስመልክቶ የተሻለ መረጃ አላቸው የሚሏቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ከዘመዶቼም በመያዝ ከጥቂት እረፍት በኋላ ከተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች አንዱ ወደ ሆኑት አቶ አበራ በጭሮ [1] ቤት ሄድን፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አቶ አበራን ቤት ስላገኘናቸው የጠበቀ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እንድንቀመጥ ጋበዙን፡፡ ከእኔ ጋር የነበረውን ታሪኩ የተባለውን ዘመዴን ያውቁት ነበርና ስለ እኔ ማንነት በሸከኛ ሲጠይቁት የእናቴን ማንነት ስለነገራቸው እናቴን በደንብ ያውቋት ኖሯልና ዳግመኛ ከተቀመጡበት ተነስተው በደንብ ሰላም ተባባልን፡፡ አቶ አበራ የመጣሁበትን ጉዳይ ጠይቀውኝ በአጭሩ ካብራራሁላቸው በኋላ ቢረዱኝ ደስተኛ እንደሆኑ ነገር ግን በለሊት ወደ ሚዛን ዩኒቨርሲቲ ለትምህርት ለመሄድ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው እነማን በዙሪያው የተሻለ ዕውቀት እንዳላቸው ዝርዝር መረጃ በመቀበል አመስግኜ ተለያየን፡፡

ከ13/06/06 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቀን 16/06/06 ዓ.ም ድረስ በርዕሰ ጉዳዬ ዙሪያ ሰፊ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ አካላት ተብለው በተለያዩ ሰዎች የተጠቀሱልኝን የተለያዩ ሰዎች

[1] አቶ አበራ በጭሮ መምህር ሲሆኑ በብሔረሰቡ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ያዘጋጁ በመሆናቸው በዞኑ መንግስት ማበረታቻ ይሆናቸው ዘንድ ዘመናዊ የመኖሪያ ቤት እና የአምባሳደርነት ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል፡፡

እንዲያረጋግጡልኝ በማድረግ እና "በለቅሶ ላይ ቀረፃ በተኣምር አይፈቀድም !" የተባልኩ በመሆኔ በዚህ ዙሪያ ቀደም ሲል ከህብረተሰቡ ፍቃድ ውጪ የአባታቸውን ሞት አስቀርፀዋል የተባሉ ሁለት ሰዎችን አፈላልጌ በማግኘት መረጃ ስቀበል እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ሳከናውን ቆየሁ፡፡

በቀን 16/06/06 ዓ፣ም አመሻሽ ላይ የአባታቸውን ለቅሶ በከፍተኛ ውዝግብ አስቀርፀዋል ከተባሉት የቀድሞ የዞኑ አስተዳዳሪ አቶ ዘለቀ ሻጫቸው እና በአካባቢው የታወቁ ቃልቻ ("ቡለፎ" ይባላሉ፤ ዛሬም ድረስ በስማቸው ይማላል፣ ይገዘታል) የልጅ ልጅ የሆነው አቶ ስለሺ ጫሊቶ ጋር በአካል በመገናኘት በአራት የዴክ ካሴት ያስቀረፁቸውን የድምፅ እና የምስል መረጃዎች በድርድር መቀበል ችያለሁ፡፡ ይህ ካሴት የአቶ ስለሺ ጫሊቶ በ2002 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የአቶ ዘለቀ ሻጫቸው ደግሞ በ2003 ዓ.ም መጀመሪያዎቹ ወራት አካባቢ የተቀረፀ ከመሆኑም በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት የዴክ ካሴት ማጫወቻ እንደልብ የማይገኝ በመሆኑ ያገኘሁትን መረጃ ወደ ሲዲ የሚገለብጥልኝ ባለሙያ ወደሚገኝበት ቴፒ ከተማ (ቴፒ ከማሻ 86 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ በዞኑ ስር ከሚተዳደሩት ወረዳዎች አንዱ የሆነችው የኪ ወረዳ ዋና ከተማ ናት፡፡) በነጋታው ጠዋት በመሄድ አስገልብጬ ወደ ማሻ በ18/06/06 ዓ.ም ከሰዓት ተመለስኩ፡፡ ካሴቶቹ ተቀምጠው የነበሩት ቅዝቃዜ ሊያጠቃቸው ከሚችልበት ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ ቆየት በማለታቸው የድምፅ እና የምስል ጥራታቸው የተጓደለ ከመሆኑ ውጪ የያዙት መረጃ ለማንፀሪያና ለአስረጂነት በእጅጉ ጠቅሞኛል፡፡

ከቀን 20 እስከ 24/06/06 ዓ.ም በአበሎ ቀበሌ የሚገኙ አንዲት እድሜ ጠገብ አዛውንት በህመም ምክንያት ህይወታቸው በማለፉ እዚያው ተገኝቼ የመጀመሪያ ምልከታዬን ያከናወንኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ሟች ባለቤታቸው ቀደም ብለው ያለፉ በመሆኑ የሚኖሩት ከልጅ ልጆቻቸው እና ከጣውንታቸው ጋር ነበር፡፡ ምንም እንኳ ከተለያዩ ሰዎች እንዳልሞከረው የተነገረኝ ቢሆንም በዚህ ስርዓት ላይ የሚከወኑ የተለያዩ ባህላዊ ገፅታዎችን በፎቶ እና በቪዲዮ ካሜራ ማስቀረት እችል ዘንድ ፍቃዳቸውን ለማግኘት የሟችን ሴት ልጅ አግባብቼ ብጠይቅም "የእናትሽን ለቅሶ እንደነ ቡለፎ ለቅሶ አበላሺ ነው የምትለኝ ?!" ሲሉ ጉዳዩ የቱን ያህል አሉታዊ በሆነ መልኩ እየታየ መሆኑን አስገንዝበውኝ የጠየቋቸው ነገር ከቶውኑ እንደማይቻል በማስጠንቀቅ በእያንዳንዱ ስርዓት ላይ ግን ልክ እንደለቀስተኛ ተገኝቼ መመልከት እንድችል ፍቃዳቸውን ሰጥተውኛል፡፡ ስለሆነም የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ የምመለከታቸውን ልዩ ልዩ ትዕይንቶች በሚገባ በማጤን በትዕይንቶቹ ማብቂያ ላይ ሰወር ያለ ስፍራ መርጬ እና በየዕለቱ ማታ ማታ ሰፋ ያለ ማስታወሻ በመያዝ የተጋረጠብኝን ችግር በተቻለ መጠን ለመቅረፍ ችያለሁ፡፡

በቀን 25 እና 26 አስቀድሜ ያዘጋጀሁትን መነሻ ጥያቄ እና በምልከታው ወቅት የጠፈጠሩብኝን ጥያቄዎች በማከል ከሁለት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ጋር ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ከየካቲት 27/06 ዓ.ም እስከ መጋቢት 02/06 ዓ.ም ድረስ ሌላኛውን ምልከታዬን ያካሄድኩበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ምልከታ በቀደመው ምልከታዬ ያላስተዋልኩት ተጨማሪ ነገር እና በዚያን ወቅት የሳትኳቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ያገኘሁበት ነበር፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ሟች ወንድ በመሆኑም ከፆታ ስብጥር አንፃር መመልከት የሚጠበቅብኝን መሰረታዊ ነጥቦች አግኝቼበታለሁ፡፡

በሁለተኛው ምልከታዬ ወቅት ባገኘኋቸው የተወሰኑ የእረፍት ጊዜዎች እና አንዳንዴ አመሻሽ ላይ ለአዳር ወደ ማሻ ስመለስ በቀጠሮ ከያዝኳቸው ሦስት ያህል ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ጋር ቃለ-መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ሁለተኛው ምልከታዬን እንዳበቃሁ በቀን 3 እና 4/07/06 ዓ.ም እንዲሁ ከሌሎች ሁለት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ጋር ሰፋ ያለ ጊዜን አሳልፌያለሁ፡፡ መጋቢት 5/06 ዓ.ም ከምልከታ እና ከቃለ መጠይቅ ያገኘኋቸውን መሰረታዊ ነጥቦች ያረጋገጥኩበት እና ከሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቼ ያመለጡ ቁም ነገሮችን ያገኘሁበትን የተተኳሪ ቡድን ውይይት ያደረኩበት ቀን ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በነበሩኝ የተወሰኑ ቀናት በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት በድምፅ የቀረፅኳቸውን መረጃዎቼን ወደ ፅሁፍ ስገለብጥ እና ሳደራጅ ነው የቆየሁት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎቹን በትኩረት በምመረምርበት ወቅት የተፈጠሩብኝን ጥያቄዎች እና የተወሰነ ክፍተት ይስተዋልባቸዋል ያልኳቸውን የተወሰኑ መረጃዎች ከአንዳንድ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ጋር ዳግም በመገናኘት ሳሟላ ቆይቼ መጋቢት 10/06 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ቤተሰቦቼ ወደሚገኙበት ሜጢጢ ከተማ ተመለስኩ፡፡

### 1.11. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው

በዚህ ጥናት ከንውን ወቅት ያጋጠመኝ ከፍ ያለ ችግር በብሔረሰቡ ባህል መሰረት በለቅሶ ስርዓት ላይ ምንም አይነት የድምፅም ሆነ የምስል ቀረፃ እንዲደረግ የሚፈቀድ አለመሆኑ ነው፡፡ ይህ መሆኑን ትብብር እንዲደረግልኝ ከትምህርት ክፍሌ ለሸካ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት የተፃፈልኝን ደብዳቤ ይዤ የዞኑ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ አዝመራው ፊት በመቅረብ የመጣሁበትን ዓላማ እና መረጃዎቹን በምን መልኩ እንደምሰበስብ ሳስረዳ "ቀረፃውን እንኳ የሚፈቅዱልህ አይመስለኝም !" ከሚለው ጥርጣሬ ያዘለ ንግግራቸው ነው፡፡ ይህን እውነት ከተለያዩ አካላት ካጣራሁ በኋላ ቀደም ሲል ከህብረተሰቡ ፍቃድ ውጪ ቀርፀዋል ከተባሉት ሰዎች ጋር በመደራደር ያስቀረጿቸውን

ገልብጬ በመውሰድ ነው ከባዶ ልድን የቻልኩት፡፡ በእርግጥም እነዚህ ቀረፃዎችን ማግኘቴ አብዛኛውን ክዋኔዎች በአግባቡ እንድረዳ እና ለማመሳከሪያነት እንድጠቀምባቸው ረድተውኛል፡፡

አካባቢው በጋ ከክረምት የሚዘንብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተወሰኑ ምልከታዎቼን በአግባቡ እንዳልከታተል እና ለቃለ-መጠይቅ የቀጠርኳቸው ሰዎች በሰዓቱ እንዳይገኙልኝ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአየር ንብረቱ እጅጉን ቁር አዘል በመሆኑ አመሻሽ ላይ የዘመዶቼ እንክብካቤ ባይኖር ኖሮ ቁጭ ብሎ የተወሰኑ ስራዎችን ለማከናወን ያዳግት ነበር፡፡

ለጥናት የተበጀተልኝ በጀት ለጥናቱ በዋናነት ያስፈልጉኛል ብዬ ያመንኩባቸውን የተወሰኑ ቁሳቁሶች ስገዛ ገና ከአዲስ አበባ ሳልወጣ የተገባደደ በመሆኑ ለመረጃ አቀባዮቼ የምከፍለውን ተበድሬ ነበር የሄድኩት፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛው የመረጃ አቀባዮቼ ከወላጅ እናቴ ጋር የጠበቀ ትውውቅ ያላቸው በመሆኑ ከእኔ አበል ከመጠየቅ ይልቅ እነሱ በየቤታቸው ሲጋብዙኝ ነው ያመሹት፡፡ ነገር ግን ጥቂቶቹም ቢሆን የሚጠይቁት ክፍያ ዩኒቨርሲቲው ለተመራማሪው በቀን ከሚበጅተው የሚልቅ በመሆኑ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

የተወሰኑት የመረጃ አቀባዮቼ "ይሄንን እናትህ ከእኛ የተሻለ ታውቃለች፤ እሷን ጠይቃት፣ ይህ ደግሞ ምን ያደርግልሀል፣. . ." በሚል የተወሰኑ መረጃዎችን ላለመስጠት ቢያንገራግሩም ከእነሱ የፈለኩበትን ምክንያት እና እያንዳንዱ መረጃ ለእኔ ያለውን ዋጋ በማስረዳት ፍቃደኝነታቸውን አግኝቻለሁ፡፡

ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላው ችግር የምለው በየቤተመፃሕፍቱ የተፈጠረው የሰራተኞች ለውጥ እና ሽግሽግ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በዘንድሮው ዓመት በዩኒቨርሲቲው ጥቂት የማይባሉ የአስተዳደር ሰራተኞች ከነበሩበት ቦታ ተነስተው ወደ ሌላ የስራ ዘርፍ/ክፍል ተዛውረዋል፡፡ ይህ እጣ ከደረሳቸው መካከል የቤተ-መፃህፍት ሰራተኞችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለውጡ ባልከፋ ነገር ግን የገቡት ሰራተኞች ቀደም ሲል የነበሩት ሰራተኞች ይሰጡን የነበሩትን አገልግሎት ሊሰጡን ያልቻሉ ከመሆናቸው ላይ ነው ችግሩ፡፡ በተለይም የእኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አብዝተን የምንጠቀመው "IES" እና "ILS" ቤተ-መፃሕፍትን ሲሆን ቀደም ሲሉ የነበሩት ሁሉም ሰራተኞች ተነስተው በቦታቸው ስለ ቦታው የማያውቁ አዳዲስ ሰራተኞች የተመደቡ በመሆናቸው በማውጫው ላይ የተጠቀሰን አንድ ጥናት ፈልጎ ለማግኘት ከ30 ደቂቃ እስከ 1:00 ሰዓት ሊፈጅባቸው የሚችል ሲሆን ከዚያም ከባሰ "የለም" የሚል ምላሽም ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህ

ጉዳይ በእኔ ብቻ ሳይሆን አብዛኞቹ የእኔ ጓደኞችም የገጠማቸው መሆኑ ከግምት ውስጥ ገብቶ በስልጠና ወይም በሌላ መልኩ ችግሩ መፈታት ቢችል መልካም ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ርዕስ ስር ሁለት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ፡፡ እነሱም "የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት" እና "ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ" ናቸው፡፡

### 2.1. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ይህ ጥናት ከሚያተኩርበት የለቅሶ ስርዓት ጋር የተዛመዱ እና ጥናቱ የሚያተኩርበት የሸካቾ ብሔረሰብ ላይ አተኩረው የተሰሩ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ጥናታዊ ፅሁፎች እና ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይዳሰሳሉ፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ የሚመሳሰሉ የቢ.ኤ እና የኤም.ኤ ዲግሪ እንዲሁም በ"Ethnological Society Bulletin" ላይ የወጡ የተለያየ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓትን የተመለከቱ ፅሁፎች የዳሰሳው አካል ናቸው፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ፅሁፎች የሚዳሰሱበትም መንገድ ጥናቶቹ የተሰሩበትን ደረጃ እና ዘመን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህም ማለት ከዚህ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት አላቸው ተብለው የታመነባቸውን ጥናቶች ለቢ.ኤ፣ ለኤም.ኤ እና ሌሎች በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ስር በማዋገን ነው ዳሰሳው የሚደረገው፡፡ በየርዕሰ ጉዳዩ ስር የሚኖረው መቀዳደም መሰረት የሚያደርገው ጥናቶቹ የተሰሩበትን ዘመን ነው፡፡

ከፍ ባለው መልኩ የቀደሙትን ጥናቶች አዋግኖ እና በዘመን ቅደም ተከተላቸው መሰረት ለመመልከት መሞከሩ የሚኖረው ረብ አንባቢ የደረጃዎቹ ልዩነትም ሆነ የዘመን ለውጡ በጥናቶቹ ላይ ያስከተለው እድገት አሊያም ውድቀት ይኑር አይኑር በቀላሉ መመርመር ይቻለው ዘንድ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡

በቅድሚያ ይህ ጥናት የሚያተኩርበት የሸካቾ ብሔረሰብ ላይ አተኩረው የተሰሩ ጥናቶች ይዳሰሳሉ፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትም ምክንያት ብሔረሰቡን የተመለከቱ መረጃዎችን አስቀድሞ መገንዘብ ተገቢ ነው በሚል ነው፡፡ ይህ መሆኑ ብሔረሰቡ የት እና በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ አስቀድሞ መረዳት በጥናት ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን ከጅማሬው አስወግዶ ለማለፍ ይረዳል፡፡

### 2.1.1. ትኩረታቸውን የሸካቾ ብሔረሰብ ላይ ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች

በሸካቾ ብሔረሰብ ልዩ ልዩ የፎክሎር ዘውጎች ላይ ከተደረጉ ጥናቶች አማረ ሞላ (1999 ዓ.ም)፣ ምህረት ካሳ (2002 ዓ.ም) እና ስለሺ አባተ (2002 ዓ.ም) ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቧቸው ጥናቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን ጥናቶች ከቀረቡበት ዓመት አንፃር በመመደብ ቀጥለን እንመልከት፡፡

**አማረ ሞላ** (1999) "የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ዓላማ የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶችን በመሰብሰብ መድቦ ከአከዋወን ስልት እና ከይዘት አንፃር መተንተን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተረቶቹን ሰንዶ ለመጪው ትውልድ በቅርስነት ማቆየት ሌላው የጥናቱ ዓላማ እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡ እነዚህን ዓላማዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ አርቲፊሻል መቼትን ተጠቅሞ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ በማድረግ የሰበሰባቸውን ተረቶች በጥናቱ ትንተና ላይ አይነታዊ እና ይዘታዊ ትንተናን በመጠቀም መድቧቸዋል፡፡ በአይነታዊ ምደባ ስርም አካባቢያዊ ምደባን እና ፎክሎራዊ ምደባን ተጠቅሞ ተረቶቹን በተለያየ መንገድ መድቧል፡፡ አካባቢያዊ ምደባን መሰረት አድርጎ ተረቶቹን "ኬሞ" እና "ኢንጌሞ" በማለት የመደበ ሲሆን በኬሞ ስር የሚመደቡት ተረቶች ስለ ብሔረሰቡ የጎሳ መሪዎች ወይም ንጉሶች፣ ስለባህላዊ የእምነት መሪዎች፣ ብሔረሰቡ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ስላደረጋቸው ጦርነቶች ወዘተ. የሚያትቱ ናቸው ሲል ይጠቅሳል፡፡ በኢንጌሞ ስር የሚካተቱት ተረቶች ደግሞ በብሔረሰቡ እምነትና አስተሳሰብ ስለአንዳንድ ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ በአካባቢያቸው ስላሉ ልዩ ልዩ ክስተቶችና ሁኔታዎች የሚያትቱ እንደሆኑ ገልጿል፡፡

ተረቶቹን ከይዘት አንፃር በስድስት ዋና ዋና ጭብጦች መድቧቸዋል፡፡ እነሱም ብልህነት፣ መጥፎ ባህሪያት፣ ፍትሀዊነት፣ ጓደኝነት፣ ትዕግስተኝነት፣ እና ጣውንትነት ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ተረቶችም ትምህርታዊ መልዕክት የሚተላለፍባቸው ሆነው መገኘታቸውንም አማረ አመልክቷል፡፡ ፎክሎራዊ ምደባ ሲል በሚጠራው ሌላው አከፋፈሉ ደግሞ ተረቶቹን አፈ-ታሪክ፣ ገላጭ /ኬትመጣ/ ተረቶች እና ፋቡላ በማለት በሦስት ይመድባቸዋል፡፡

**ምህረት ካሳ** (2002) "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና የአመጋገብ ስርዓት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ያደረገችው ጥናት ሌላው በሸካቾ ብሔረሰብ ላይ አተኩሮ የተደረገ ጥናት ነው፡፡

ምህረት "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት፣ አቀራረብ እና አመጋገብ ስርዓት ማህበራዊ እና ባህላዊ ገፅታ ማሳየት" የሚል ዓላማን በዋናነት የያዘች ሲሆን በዝርዝር ዓላማነት ደግሞ ምግቦቹ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ በማን፣ ለማን እና ለምን እንደሚዘጋጁ ማሳየት፣ በምግብ አዘገጃጀት እና አቀራረብ እንዲሁም አመጋገብ ስርዓት ውስጥ የሚንፀባረቁ ማህበራዊ እና ፆታዊ ትዕምርቶችን ከነጠቀሜታቸው ማጥናት፣ የብሔረሰቡን ባህላዊ ምግቦች አዘገጃጀት፣ አቀራረብ እና አመጋገብ እንዲሁም ስነቃሎችን አሁን ባሉበት ደረጃ በድምፅና በምስል መሰነድ እና ከብሔረሰቡ ምግብና መጠጥ ዝግጅት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ስነቃሎችን መተንተን የሚሉትን አካታለች፡፡ አጥኚዋ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የተሳትፎ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን ተጠቅማ መረጃዎቿን ሰብስባለች፡፡

አጥኚዋ "ዋና ዋና ምግቦች" የሚባሉትን 14 የምግብ አይነቶች ከእነ አሰራር ሂደታቸው በብሔረሰቡ መጠሪያ አስፍራለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "ማባያዎች" ያለቻቸውንም ከምን ከምን እንደሚዘጋጁ ገልፃለች፡፡ እንዲሁም በብሔረሰቡ የሚዘወተሩ መጠጦችን ቀዝቃዛና ትኩስ በማለት አዘገጃጀታቸውን እና አቀራረባቸውንም አብራርታለች፡፡

ምህረት ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃና የምግብ ክልከላን ያብራራች ሲሆን በብሔረሰቡ ከምግብ እና ስርዓተ ምግብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ዳሳለች፡፡

ምህረት የብሔረሰቡ አባል መሆኗ መረጃዎችን ባሻት ጊዜና ቦታ በበቂ መጠን እንድታገኝ የረዳት መሆኑን በሰፊው ካቀረበቻቸው መረጃዎች መገመት ይቻላል፡፡ የምህረት ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚገናኝበት መስመር እኔ የማተኩርበት ብሔረሰብ ላይ ማተኮሯ ብቻ ሳይሆን እኔ በምመለከተው የለቅሶ ስርዓት ላይ ለሚገኙ ለቀስተኞች ምግብ በስፋት የሚቀርበው ቆጮ ላይ ትኩረት ሰጥታ የሰራች በመሆኗም ጭምር ነው፡፡

**ስለሺ አባተ** (2002) "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሌላው በሸካቾ ብሔረሰብ ላይ አተኩሮ የተደረገ ነው፡፡

የስለሺ ዓላማዎች "ብሔረሰቡ ግጭቶችን የሚፈታባቸውን ሾቦ እና ሾቶ ባህላዊ ተቋማት፤ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚጫወቱትን ሚና ማሳየት፣ ግጭትን በመከላከል፣ በማብረድ እና በመፍታት ረገድ የስነቃሎች ፋይዳን ማመልከት እና የብሔረሰቡን ባህላዊ የዕርቅ ክዋኔዎች

በፅሁፍ፣ በመቅረፀ ድምፅ፣ በቪዲዮ እና በፎቶ ካሜራዎች በመመዝገብ እና በመቅረፅ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ" የሚሉት ናቸው፡፡

ስለሺ መረጃ የሰበሰበው ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼትን ተጠቅሞ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የሰበሰባቸውን መረጃዎች ገላጭ እና የይዘት ትንተና ስልቶችን ተከትሎ ትንታኔውን አከናውኗል፡፡

አጥኚው ብሔረሰቡ ስለ ግጭት ያለውን አመለካከት፣ የግጭት መንስኤዎች እና አይነቶችን፣ የግጭት መፍቻ አውዶችን እና የአስታራቂ ሽማግሌዎችን ሚና ዘርዘር አድርጎ አብራርቷል፡፡ በተጨማሪም ኮዎ፣ አዶ ጮቴ፣ ማራዬማጮ፣ ሼሪቆ ሾቲዮ እና ሌሎች ባህላዊ እውቀቶች ሲል ሀገርኛ በሆነ አገላለፅ አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ተብለው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታወቁትን ተንትኖ አቅርቧል፡፡

ስለሺ የግጭት አይቀሬነትን የሚያስረዱ፣ በዘመድ መካከል የሚፈጠር ግጭት የከፋ መሆኑን የሚያስረዱ፣ መሬትን አስመልክተው የሚነገሩ፣ የእውነትን አይቀሬነት የሚገልፁ፣ ሽማግሌዎችን በተመለከተ የሚነገሩ እና ትዳርን በተመለከተ የሚነገሩ ስነ ቃሎች በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍሎ ስነ ቃሎቹን ተንትኖ አቅርቧል፡፡

የስለሺ ጥናት ለእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ በቂ የሆነ ማብራሪያ ከመስጠቱም በላይ ይዞ የተነሳቸውን ዓላማዎች ከግብ አድርሷል ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የስለሺ መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡት ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ብቻ መሰረት አድርገው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በትንተናው ወቅት ቀደም ሲል እጠቀምበታለሁ ብሎ ያስተዋወቀውን የምልከታ ዘዴን በግልፅ የተጠቀመበት ስፍራ አይስተዋልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የስለሺ ርዕስ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በእጅጉ የሚፈልግ ሆኖ ሳለ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አለመጠቀሙም እንደክፍተት የሚቆጠር ነው፡፡ ምክንያቱም የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የጎሳ መሪዎችን፣ የፖሊስ አባላትን፣ የፍትህ አካላትን፣ የሀይማኖት ተቋማትን፣ በግጭት ውስጥ ያለፉ ሰዎችን፣ የጎላ ግጭት ውስጥ ገብተው የማያውቁ ሰዎችን፣ ግጭትን ለማስወገድ የሚሰሩ ድርጅቶችን፣. . .ወዘተ በማካተት ውይይት ቢያደርግ ከዚህም የተሻለ መረጃ ሊያገኝ የሚችልበትን አማራጭ ያመቻች ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ከፍ ሲል የቀረቡት ሶስት ጥናቶች የእኔ ጥናት የሚያተኩርበት ማህበረሰብ ላይ ተመስርተው የተሰሩ በመሆናቸው የሚያመሳስለን ሲሆን ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ግን ልዩነት አለን፡፡ እነዚህን ጥናቶች ማንበቤ ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ ከምሰማቸው ጥራዝ ነጠቅ ወሬዎች ይልቅ ተጨባጭ መረጃዎችን እንዳገኝ አስችለውኛል፡፡ በተለይም የህብረተሰቡን አኗኗር እና ባህል በገለፁባቸው ክፍሎች ውስጥ የለቅሶ ስርዓቱን ጠቀስ አርገው ያለፉ ከመሆናቸው አንፃር ተገቢውን አቅጣጫ አስይዘውኛል፡፡

### 2.1.2. በርዕሰ ጉዳይ የሚዛመዱ ጥናቶች እና ፅሁፎች ዳሰሳ

በዚህ ርዕስ ስር በቢ.ኤ እና በኤም.ኤ ደረጃ የለቅሶ ስርዓት ላይ አተኩረው የተሰሩ ጥናቶችን እንዲሁም በ"Ethnological Society Bulletin" ላይ የወጡ የተለያየ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓትን የተመለከቱ ፅሁፎችን ለቢ.ኤ ዲግሪ የቀረቡ፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ እና ሌሎች በሚሉ ምድቦች ስር አካተን እንመለከታለን፡፡

#### 2.1.2.1. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን የቀረቡበትን ዓመት መሰረት በማድረግ ቀጥለን በአጭሩ እንመልከት፡፡ ጥናቶቹ የቀረቡበት ዘመን ተመሳሳይ ከሆነ የአጥኚዎችን ስም የመጀመሪያ ፊደል ለአደራደርም ቅደም ተከተሉ እገለገልበታለሁ፡፡

በዚህ ስር የማቀርባቸውን ጥናቶች ምን እና እንዴት እንደተሰሩ በአጭሩ ለማስተዋወቅ ከማደርገው ጥረት በቀር ጠለቅ ያለ አስተያየት በመሰንዘር ጥናቶቹ ያሉባቸውን ክፍተቶች ዘርዘር አድርጎ ለማቅረብ አልሞከርም፡፡ ምክንያቱም ጥናቶቹ የቀረቡበት ደረጃ ስነዳው ላይ እንዲያተኩሩ የሚጋብዝ እንጂ በንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ውስጥ አድረው ትንተና እንዲሰጡ የሚጋብዛቸው ባለመሆኑ ከዚህ አግባብ ለመመልከት አይቻልም፡፡

**ጥላሁን ኢቢዶ** (1982) ያደረገው ጥናት "የጌዴኦ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት" የሚል ነው፡፡ ጥላሁን በጌዴኦ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው ስለሚለው "የጌዴኦ ገዳ ስርዓት" ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ የገዳ ስርዓት መሰረት አድርጎም የለቅሶ ስርዓቱን በዕድሜ እና በፆታ ከፋፍሎ አጥንቷል፡፡ ዕድሜን መሰረት አድርጎ ሲያጠና ለህፃን፣ ለወጣት፣ ለጎልማሳ እና ለአረጋዊ የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት በሚል ሲሆን፤ ከፆታ አንፃርም ለወንዶች እና ለሴቶች የሚደረግ

የለቅሶ ስርዓት ሲል ገልጿል፡፡ አጥኚው ከእነዚህ ክፍልፋዮች አንፃር የሚባሉ የሙሾ ግጥሞችንም አያይዞ ተንትኗል፡፡

**አየለ መሎሬ** (1986) "የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት የለቅሶ ስርዓቱን "ቅድመ ቀብር" እና "ቀብር" በሚል ለይቶ በሁለቱም ንዑስ ርዕሶች ስር "ከልደት እስከ ሙሽርና ለደረሱ" እና "ለአዛውንት" ሲል በህብረተሰቡ ውስጥ የሚደረጉ የለቅሶ ስርዓቶችን ገልጿል፡፡ አየለ በቅድመ ቀብር ዝግጅቶች ውስጥ ከጠቀሳቸው ነገሮች ውስጥ  በቀብሩ ቀን ለለቀስተኛው የሚሆኑ የምግብ እና መጠጥ ዝግጅቶች ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙ መሆናቸውን አመልክቷል፡፡

**ጌጡ ታደሰ** (1986) ያቀረበው ጥናት "ክዋኔ በጎንደር ከተማ ለቅሶ ስነ ስርዓት" የሚል ሲሆን በለቅሶ ክዋኔው ወቅት ቃላዊ ግጥሞች በዜማ የሚባሉ መሆናቸውን ከመግለፁም በተጨማሪ የክዋኔው ታዳሚዎች በአካል እንቅስቃሴ እና በፊት ገፅታ ቅይይር የውስጥ ስሜታቸውን ሲገልፁ እንደሚስተዋሉ ያስረዳል፡፡ አጥኚው በጎንደር ከተማ የሚፈፀመው የለቅሶ ክዋኔ፣ የቀብር ስርዓት አፈፃፀም እና የለቅሶ ግጥሞች ከሟቹ ወገን ማንነት እና ማህበራዊ ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚለያይ መሆኑን ገልጿል፡፡ መንፈሳዊ በሆነ ሰው የለቅሶ ስርዓት ላይ ቀረርቶ፣ ፉከራ እና እርግዶ አይፈፀምም፡፡ ይልቁንም መንፈሳዊ ዜማ፣ ወረብና ሽብሸባ እንደሚደረግ ይገልፃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሟች ወገኖች ካባ ደርበው ለቅሶ ሊደርሳቸው የሚመጣውን ሰው ቆመው እያለቀሱ እንደሚቀበሉ አመልክቷል፡፡ ጌጡ ትኩረት ሰጥቶ የተመለከተው በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች የሚፈፀመውን የለቅሶ ስርዓት ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ለምን እንደሆነ አጥኚው የሚጠቅሰው ምክንያት የለም፡፡

**ወርቁ ማንደፍሮ** (1987) "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች" በሚለው ጥናቱ አንድ ሰው ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ግብአተ መሬት ፍፃሜው ድረስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት አስፍሯል፡፡ የሙሾ ግጥሞችን ለወጣት፣ ለሽማግሌ፣ ለእናት፣ ለእህት እና ለወንድም የሚደረደሩ በማለት አዋግኖ አቅርቧል፡፡ የሙሾ ግጥሞቹን ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ ከፋፍሎ ለማጥናት መሞከሩ እና የጥናቱን ገደብ በግልፅ ማስፈሩ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ ወርቁ የተጠኚው ማህበረሰብ አባል በመሆኑ እያንዳንዱን ነገር ሰንዶ ለመያዝ በነበረው ጉጉት በማህበረሰቡ የተከለከላቸውን ነገሮች ሁሉ በድብቅ መረጃ ይሰበስብ እንደነበር ጠቅሷል፡፡ ይህ ተግባር ከጥናት ስነ-ምግባር ውጭ በመሆኑ የሚደገፍ አይደለም፡፡ ከዚህም

በተጨማሪ በአብዛኞቹ ቦታዎች አጥኚው ለበርካታ መረጃዎች እራሱን በምንጭነት መገልገሉም የጥናቱን ተአማኒነት የሚያጎለው ተግባር ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

**ወርቃየሁ አረጋ** (1995) "የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት) እና የአዊ ዚንዚምኛ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋለች፡፡ ወርቃየሁ የአዊ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል ለማሳየት የሞከረች ሲሆን በጥናቷ የመጨረሻ ምዕራፍ ደግሞ በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት የሰበሰበቻቸውን የሙሾ ግጥሞች ለወንዶች (አባት፣ ወንድም፣ ልጅ) የሚገጠሙ፣ ለሴቶች (እናት፣ እህት) ስትሞት የሚገጠሙ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ስር በማዋገን በስፋት ተንትና አቅርባለች፡፡

**አስቴር አንጀሎ** (1997) ያቀረበችው ጥናት "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" የሚል ነው፡፡ አስቴር ይህን ጥናት ያከናወነችበት ዋንኛ ዓላማ "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል እና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን የባህል ዝምድና ለማሳየት ነው"፡፡ አጥኚዋ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት እና በስርዓቱ ላይ የሚባሉ የሙሾ ግጥሞችን ይዘት ወጣት ሲሞት፣ ጎልማሳ ሲሞት፣ አባት ሲሞት፣ እናት ስትሞት፣ ወንድም እና እህት ሲሞቱ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ስር ከፋፍላ አጥንታለች፡፡ በዚህ መልኩ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት ስታጠና "ከቀብር በፊት"፣ "በቀብር ጊዜ" እና "ከቀብር በኋላ" ባለው የከዋኔ ስርዓት አዋግና ነው፡፡ አስቴር በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት የሚባሉትን የሙሾ ግጥሞች አያይዛ ማጥናቷ ተገቢ ቢሆንም በዓላማ ያልያዘችው በመሆኑ እንደ ክፍተት ሊታይ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ድምዳሜ ለመስጠት የምታደርገው ሙከራ ("ይህኛው ጎጂ ነው፣ ያኛው ጠቃሚ ነው" ማለቷ) እንደ ፎክሎር አጥኚነቷ የሚገባ አይደለም፡፡

**ተሾመ ሙሉጌታ** (1998) "በቤንሻንጉል ጉምዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓት" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፉን አቅርቧል፡፡ በድባጢ ወረዳ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ወጣት ሲሞት፣ አዛውንት ሲሞት፣ ሰው የገደለ ሲሞት፣ አውሬ የገደለ ሰው ሲሞት እና በጥይት የተመታ ሰው ሲሞት የሚፈፅሟቸውን የተለያዩ የአከዋወን ስርዓት ልዩነቶች ተንትኗል፡፡ አጥኚው ይህ ማህበረሰብ የቀብር ጉድጓድ እንዴት እንደሚያዘጋጁ እና የአቀባበር ስርዓቱም ምን እንደሚመስል ከማመላከቱም በተጨማሪ የጉምዝ ማህበረሰብ ለሟቾች የሚገጥሟቸውን የጉምዝኛ ግጥሞች ከአቻ የአማርኛ ትርጉማቸው ጋር በማቅረብ ነው ጥናቱን ያጠናቀቀው፡፡ ተሾመ የለቅሶ ስርዓቱን የተጠኚው ማህበረሰብ ለለቅሶ ከዋኔ ልዩነት መፈጠር መሰረቶች ናቸው ብሎ ከሚጠቅሳቸው

መሰረታዊ ነጥቦች አንፃር በማዋገን ተንትኖ ለማቅረብ መሞከሩ እና በእነዚህ ክዋኔዎች ወቅት የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞችን አያይዞ ማጥናቱ ለጥናቱ የሰጠውን ትኩረት ይመሰክራል፡፡ ይሁን እንጂ ተሾመ በለቅሶ ስርዓት ክዋኔው ወቅት የተመለከታቸውን አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮች ስለምንነታቸውን በመረጃ አስደግፎ ለማስቀመጥ ከመሞከር ይልቅ "በባህሉ እንዲህ ይደረጋል" ብቻ እያለ ማለፉ እንደክፍተት የሚታይ ነው፡፡

**አቡበከር ሀሰን** (1998)"የሺናሻ ብሔረሰብ የሐዘንና የተዝካር ስርዓት ክዋኔ" ሲል ባደረገው ጥናት በሺናሻ ብሔረሰብ ሰው ሲሞት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜና ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስርዓቶች እንደምን ያሉ እንደሆኑ እና የጉዞ ፍትሐት (ሻሮ) እና የተዝካር ስርዓታቸው ምን እንደሚመስል ተንትኖ አሳይቷል፡፡ ይህ የለቅሶ ስርዓት ደግሞ ወጣት ሲሞት፣ ጎልማሳ ሲሞት፣ አዛውንት (ባልቴት) ሲሞት እና ጀግና ሲሞት ያለው አፈፃፀም ምን እንደሚመስል በትንታኔው ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በለቅሶ ስርዓቱ ወቅት የሚባሉ የሙሾ ግጥሞችንም ከይዘት አንፃር ትንታኔ በመስጠት ማጠቃለያ አቅርቦ ጥናቱን ይቋጫል፡፡ የአቡበከር ጥናት ርዕስ እና ዋንኛ ዓላማ "የሺናሻ ብሔረሰብን የሐዘን እና የተዝካር ስርዓት መግለፅ" የሚል ነው፡፡ ይህ ርዕስ እና ዓላማ ሲነደፍ ቀድሞ የሚመጣው ነገር ከሞት በኋላ እንዲያም ሲል ከቀብር በኋላ በብሔረሰቡ ዘንድ የሚፈፀሙ ተግባራት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው በህብረተሰቡ ዘንድ ሞት ከመከሰቱ በፊት ምን ምን ተግባራት እንደሚፈፀሙ በዝርዝር ያስረዳል፡፡ ይህ መሆኑ በራሱ እንደችግር የሚቆጠር ተግባር አይደለም፤ ይልቁንም የአንድን ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት አጠቃላይ ገፅታ ለማሳየት አቡበከር ከጀመረበት መጀመሩ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው የቀረፀው ርዕስ እና የነደፈው ዓላማ ያን እንዲያደርግ የሚፈቅዱለት ባለመሆናቸው ከዚህ አግባብ እንደችግር የሚታይ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

**አባተ አሰፋ** (2000) "የአሚባራ ወረዳ አፋሮች የለቅሶ ስርዓት (አርካ) እና ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንታኔ" በሚል ርዕስ የጥናቱን ተተኳሪ ብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት "ከጣዕረ ሞት እስከ ህልፈተ ህይወት"፣ "ከህልፈተ ህይወት እስከ ግብዓተ መሬት" እና "ከግብዓተ መሬት እስከ ፍፃሜ ሀዘን ድረስ" በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች በመከፋፈል ተንትኖ አቅርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ክፍል የጥናቱ ትኩረት በሆነው አካባቢ ሞትን አስመልክተው የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡ አባተ የለቅሶ ስርዓቱን ከህብረተሰቡ ያገኘውን መረጃ መሰረት አድርጎ ከቀደሙት በተለየ መልክ በማዋገን ማጥናቱ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው መረጃ የሰበሰበበት መንገድም ሆነ መረጃውን ሰጡኝ ሲል የሚጠቅሳቸው አካላት የተመረጡበትን መንገድ አልገለፀም፡፡

**ጌታመሳይ ግዛው** (2002) ያደረገው ጥናት "የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር" የሚል ነው፡፡ ጌታመሳይ የጥናቱን ዋንኛ ጉዳይ በገለፀበት ክፍል የብሔረሰቡን የቀብር ስርዓት ክዋኔዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ስር አደራጅቶ አቅርቧል፡፡ ከቀብር በፊት፣ የቀብር ስርዓት ክዋኔ፣ ድህረ ቀብር ስርዓተ ክዋኔ፣ የደም ማጥራት ስርዓተ ክዋኔ፣ የተዝካር ስርዓት ክዋኔ እና የውርስ ስርዓት በሚል ከፋፍሎ ነው ትንታኔ ያካሔደባቸው፡፡

ጌታመሳይ በጥናቱ ዋንኛ ክፍል ከቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ያገኛውን መረጃዎች ግልፅ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ስር አዋግኖ በማቅረብ ትንታኔ መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች በግልፅ ለይቶ ማስፈሩ ጥናቱ ታስቦበት የተከናወነ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ጌታመሳይ የጥናቱን ርዕስ "የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር" ያለበትን ምክንያት መግለፅ ወይም ርዕሱን ታሳቢ አድርጎ ትንታኔውን መስራት ይጠበቅበት ነበር፡፡

ከፍ ሲል የቀረቡት አስሩም ጥናቶች ያነሱት ዋንኛ ጉዳይ "የለቅሶ ስርዓት" እንደመሆኑ መጠን ከእኔው ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ አብዛኞቹ ጥናቶች (ለምሳሌ የአየለ፣ የወርቁ፣ የወርቃየሁ፣ የአቡበከር፣ የአባተ፣ የጌታመሳይ፣. . .ወዘተ) እኔ ትንታኔዬን ያቀረብኩበትን የቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ሞት የተሰኘ የአከፋፈል ስርዓት የተከተሉ መሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ በእርግጥ ጥናቶቹ በቀደመው መንገድ መደራጀታቸው እና በርዕሰ ጉዳይ ረገድ ከእኔ ጥናት ጋር የሚዛመዱ መሆናቸው የመመሳሰያችን መሰረታዊ ነጥቦች ቢሆኑም በየርዕሰ ጉዳዩ ስር ከሚነሱ ነጥቦች ስፋት እና ትኩረት አንፃር ከደረጃ መለያየቱ የሚመነጭ ልዩነቶች አሉን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቀደሙት ጥናቶች በአብዛኛው ስነዳው ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን የእኔው ጥናት ግን ከስነዳውም በተጨማሪ በንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ውስጥ አድሮ ትንታኔ እና ትርጓሜ በመስጠት የተጠኘውን ማህበረሰብ ማንነት ለመግለጥ የሚሞክር በመሆኑም እንለያያለን፡፡

#### 2.1.2.2. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች

**ሞገስ ሚካኤል** (2000) "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሔድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረገውን የጀግና የቀብር ስነ ስርዓት፣ በስርዓቱ ላይ የሚደረገውን የቀረርቶ እና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅርፅ፣ በቴፐ በመቅዳት፣ ፎቶግራፍ በማንሳት እና ጥናቱንም በፅሁፍ

በማዘጋጀት እንዲቀረስ ማድረግ" የሚል ነው፡፡ በዝርዝር ዓላማነትም የጀግኖች የቀብር ስነ ስርዓት አፈፃፀምን ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ገፅታ ማሳየት፣ በቀብር ስነ ስርዓቱ ላይ የሚደረጉ ክንውኖችን አሁንና ድሮ ምን እንደሚመስሉ በማነፃፀር ልዩነታቸውን እና ተመሳስሏቸውን ለማሳየት መጣር እና ስለ ጀግኖች የቀብር ስነ ስርዓት ክዋኔ የማህበረሰቡ አመለካከት ምንድነው ? የሚሉትን ሦስት ዓላማዎች ነድፏል፡፡ እንዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ሞገስ መረጃ የሰበሰበው ምልከታ እና ቃለ መጠይቅን ተጠቅሞ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቴፕ፣ በቪዲዮ እና በፎቶ ካሜራዎች ልዩ ልዩ መረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

ሞገስ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና የንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ዳሰሳ አድርጓል፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት "የለቅሶ ስርዓትንና ሙሾን ያጠኑ"፣ "የለቅሶ ስርዓትን፣ ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ"፣ "የለቅሶ ስርዓትን ብቻ ያጠኑ" እና "ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ" ሲል የቀደሙት ጥናቶችን ይዘት መሰረት ያደረገ አከፋፈልን ተከትሎ ዳሰሳውን አካሂዷል፡፡ ሞገስ ጥናቱ የሚካሔድበትን አካባቢያዊ ዳራ በሚገባ ዳሷል፡፡ በጥናቱ ዋንኛ ክፍል በጥናቱ አካባቢ ለጀግና የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት "የቅድመ ሞት ዝግጅት" በሚል ርዕስ ስር "የኑዛዜ ስርዓት አፈፃፀም" እና "ለዋናው ለቅሶ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች" የሚሉትን፤ በ"ጊዜ ሞት" ስር "በምሽት የሚካሔዱ ስነ ስርዓቶች"፣ "በንጋት የሚካሔዱ ስነ ስርዓቶች"፣ "በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች" እና "ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስነ ስርዓቶች" ሲል ከፋፍሎ በፎቶ ግራፍ የተደገፈ ትንታኔ አቅርቧል፡፡

የሞገስ ጥናት ያቀዳቸውን ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ ከግብ አድርሷል ለማለት ያስደፍራል፡፡ ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ለጀግና የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት ምስል ከሳች በሆነ መልኩ በተለያዩ ክፍሎች በማዋገን ዘርዘር አድርጎ ለማቅረብ መሞከሩ የጥናቱን ጥንካሬ የሚመሰክር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሞገስ ከሱ የቀደሙ ጥናቶችን የቃኘበት መንገድ ግልፅ እና እያንዳንዱን ጥናት ትኩረት ሰጥቶ ያነበበ መሆኑን የሚመሰክር ነው፡፡ በሞገስ ጥናት ውስጥ እንደ ክፍተት ከሚታዩ ነገሮች መካከል የመረጃ መሰብሰቢያን አጠቃቀም በአግባቡ ያለመግለፅ ችግሮች ናቸው፡፡ ሞገስ መረጃ ለመሰብሰብ የመረጣቸው ቃለ-መጠይቅ እና ምልከታ መሆናቸውን ከመግለፅ ባሻገር የእነዚህን መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አጠቃቀም እና ምንነት አስመልክቶ ምሁራን የሚሏቸውን ነጥቦች በመጥቀስ ለማብራራት አለመሞከሩ እንደ ድክመት ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ርዕሰ ጉዳዩ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን የሚጋብዝ ሆኖ ሳለ ለመጠቀም አለመሞከሩም ተገቢ መስሎ አይታየኝም፡፡

**ሕይወት አበሩ** (2003) "የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርባለች፡፡ ሕይወት ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከግብ ለማድረስ ዋንኛ ዓላማዋ ያደረገችው "በብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ የለቅሶ ስርዓቱን ማሳየት" የሚል ሲሆን በዝርዝር ዓላማነት ደግሞ የለቅሶ ስርዓቱ በብሔረሰቡ ውስጥ ከሚሰጥ ማህበራዊ ደረጃ አንፃር እንዴት እንደሚከወን ማጥናት፣ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚደረጉ ክንውኖችን ትርጉም ማሳየት፣ የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ በማሸጋገር በኩል የማህበረሰቡ ትጋት ምን ይመስላል የሚለውን ማጥናት፣ የለቅሶ ስርዓት ክንውኑን ከመግለፅ ባሻገር የክንውኖቹን ባህላዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት እና የለቅሶ ስርዓቱ መቼ እና የት እንደሚከወን በመግለፅ የከዋኝ እና የተሳታፊዎችን ሁኔታ ማሳየት የሚሉ አምስት ዓላማዎች ተነስታለች፡፡

አጥኚዋ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ መረጃ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተፈጥሯዊ አውዱ ላይ ተገኝታ ለጥናቷ ግብዓት የሚሆኗትን የቪዲዮ፣ የፎቶግራፍ እና የድምፅ መረጃዎችንም አሰባስባለች፡፡

ሕይወት የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ሰፋ አድርጋ ተመልክታለች፡፡ ለአቀራረብ ይመቻትም ዘንድ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት በዕድሜ እና በባህላዊ ስልጣን ከፋፍላ ተንትናለች፡፡ በዚህም "ዕድሜ" በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ስር "ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም/ ሄዋን ለደረሱ" እና "ለእድሜ ባለፀጋዎች" የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት በቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ሞት ከፋፍላ የተመለከተች ሲሆን "ባህላዊ ስልጣን" ስትል ባዋገነችው ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ "ለባለቃልቻዎች" እና "ለጎሳ መሪዎች" የሚደረግ የለቅ ስርዓት በሚል ተንትና አቅርባለች፡፡

ሕይወት ትንታኔዋን ማህበረሰቡ ለሁኔታዎች የሚሰጠውን ስያሜ መሰረት አድርጋ ለማቅረብ መሞከሯ ከፎክሎር ጥናት አንፃር በበጎ ጎኑ ሊጠቀስ የሚችል ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠኚውን ማህበረሰብ "ማህበረ ባህላዊ ዳራ" ሰፋ አድርጋ ለመመልከት መሞከሯ አካባቢውን እና ማህበረሰቡን ከማስተዋወቅም ባሻገር አካባቢው ላይ ጥናት ማድረግ ለሚሹ ሌሎች አጥኚዎች በቂ መረጃ የሚሰጥ ከመሆኑ አንፃር በጥሩ ጎኑ ሊነሳ የሚገባው ነው፡፡

ሕይወት ምንም እንኳ የለቅሶ ስርዓቱን ተከትሎ ያለውን ክዋኔ እንደምትመለከት ከመግለጿ ጋር ተያይዞ "ክዋኔ መር" የትወራ ማዕቀፍን የምትከተል መሆኑን መገመት ቢቻልም

ጥናቷ የሚታገግበትን ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በግልፅ አስፍራ ለማብራራት አለመሞከሯ የጥናቷ ክፍተት ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**ዘላለም ፋንቱ** (2004) "የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" ሲል ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሁፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፉን አቅርቧል፡፡ የዘላለም ጥናት ዋንኛ ዓላማዎች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው የብሔረሰቡን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔው ወቅት የሚስተዋሉ ችግሮችን መግለፅ ነው፡፡ አጥኚው እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ተፈጥሯዊ መቼት ላይ ተገኝቶ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አድርጓል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅሞ ያገኛቸው ግብዓቶች "ብሔረሰቡ የተለያዩ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔዎችን በሚች ማንነት እና ምንነት ላይ ተመስርቶ የሚያካሂድ መሆኑን" እንደጠቆሙት ይገልፃል፡፡ አጥኚው እዚህ ማጠቃለያ ላይ እንዲደርስ ያስቻሉትን ልዩ ልዩ መረጃዎች "የቅድመ ሞት ዝግጅት"፣ "ጊዜ ሞት"፣ "ድህረ ሞት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች"፣ "ጉዞ ወደ ቀብር"፣ "በቀብር ወቅት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች"፣ "ድህረ ቀብር ክንዋኔዎች" እና "የቀጠሮ ለቅሶ" በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍሎ ዘርዘር በማድረግ አቅርቧል፡፡

ዘላለም የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ መሳሪያዎቹን በተገቢው መንገድ አልገለፀም፡፡ ይህም ማለት ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን እንዴት እና በምን መልኩ እንደሚጠቀም ካለመግለፁም በላይ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምን ስለ መሆናቸው እና እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው የምሁራንን ሀሳብ በመጥቀስ ሊያስረግጥ አልቻለም፡፡

**ማናዬ እንግዳወርቅ** (2005) "በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ንፅፅራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ ማናዬ የሁለቱ እምነት ተከታዮች የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን እንደሚመስል አሳይቷል፡፡ በዚህም "በቅድመ ሞት" እና "ጊዜ ሞት" እንዲሁም "ድህረ ቀብር ስርዓት" የተጠቃሾቹ ኃይማኖት ተከታዮች የሚፈፅሟቸውን ልዩ ልዩ ኃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ስነ-ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ገልጿል፡፡

አጥኚው በሁለቱ ኃይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ውስጥ የታዩ አንድነቶችን እና ልዩነቶችን ተመልክቷል፡፡ ከሚታዩ ተመሳስሎዎች መካከልም የሁለቱም እምነት ተከታዮች አንድ በሽተኛ የሚሞት መስሎ ከተሰማቸው ፈጣሪ ነፍሱን ይምረው ዘንድ በዘመኑ የሰራቸውን

ሀጢያቶች ክርስቲያኑ ለካህን እንዲናዘዝ ሲደረግ፣ ሙስሊሙ ደግሞ "ከሊማን" እንዲያነብ መደረጉ፣ ኑዛዜ እንዲፈፅሙ መደረጋቸው፣ የሁለቱም እምነት ተከታዮች የሬሳውን አይን፣ ጥርስ እና አፍ የሚገጥሙ፣ እጁን ስርዓት የሚያሲዙ፣ አስከሬኑን አጥበው በጀርባው በማንጋለል ቀጥ አድርገው ማስተኛታቸው፣. . .ወዘተ፣ በሁለቱም የእምነት ተከታዮች ዘንድ አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ በሬ የሚታረድ መሆኑ፣ ከቀብሩ በኋላ ወዲያውኑ በመቃብሩ ላይ እርጥብ ቅጠል የሚተክሉ መሆናቸው፣ ከቀብር መልስ ወደ ቤት/ ድንኳን ከመግባቱ በፊት እጅን መታጠብ፣. . .ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሁለቱ እምነት ተከታዮች መካከል ካሉ የቀብር ስነ-ስርዓት አፈፃፀም ልዩነቶች መካከል በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ አስከሬን እንደሁኔታው ሁለት እና ሦስት ቀናት ሊቆይ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ሲችሉ በእስልምና እምነት ተከታዮች ግን አስከሬኑን በዕለቱ የመቅበር ግዴታ መኖሩ፣ የአገናነዝ ስርዓት ልዩነቶች መኖራቸውን፣ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ካህናት ከአስከሬን ፊት፣ የሚች ዘመዶች (ወንድም ሆነ ሴት) ከአስከሬን ኋላ ሲሆኑ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ግን አስከሬኑ ከፊት እንደሚሆን እና ሴቶች አስከሬን ተከትሎ መሄድ እንደማይፈቀድላቸው፣. . .ወዘተ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ማናዬ ያገኛቸውን መረጃዎች ከሁለቱ ተተኳሪ ኃይማኖቶች አኳያ በመልክ በመልክ አደራጅቶ ለማቅረብ መሞከሩም በበጎ ጎኑ ሊጠቀስለት ይገባል፡፡ አጥኚው መረጃ የሰበሰበበትን መንገድ በአግባቡ አለመግለፁ፣ ቃለ መጠይቅን እና ምልከታንም እንዴት እና በምን ሁኔታ ውስጥ መጠቀም እንዳለበት አለማመልከቱ፣ በሁለቱም እምነት ተከታዮች አስከሬን በጀርባው ቀጥ ተደርጎ እንዲጋደም መደረጉ፣ በመቃብር ላይ ወዲያውኑ እርጥብ ቅጠል ከእነ ቅርንጫፉ ለምን እንደሚተከል፣ ከቀብር መልስ ታዳሚዎች እጃቸውን እንዲታጠቡ የሚደረገው ለምን፣ የሙስሊም ሴቶች ለምን ሬሳ እንደማይሸኙ፣. . . በግልፅ ተተንትኖ አለማሳየቱ የጥናቱ ድክመት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

**አየሁሽ ቶማ** (2005) “የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ” በሚል ርዕስ የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቷን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርባለች፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ "የወላይታ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ያለውን ገጽታ በማሳየት ትዕምርታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ማህበረሰቡ የሚሰጠውን ባህላዊ ፍቺ መመርመር" የሚል ነው፡፡ አየሁሽ ይህንን ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ከ12 ሰዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ፣ በአንድ የዕድሜ ባለፀጋ የለቅሶ ስርዓት ላይ

በመገኘት ምልከታ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አካሂዳለች፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅማ ያገኘቻቸውን መረጃዎች በክብረ በዓላት እና በክዋኔ መር የትወራ ማዕቀፍ ቅንብብ ውስጥ ሆና ገላጭ የምርምር ዘዴን ተገልግላ ትንተናዋን አቅርባለች፡፡

አየሁሽ በጥናቷ ግኝት ማህበረሰቡ በባህላዊ የለቅሶ ግጥሞቹ ሞትን መናቁ፣ በሞት ህይወትን ማስታወሱ፣ ሟች በአካል እንጂ በመንፈስ እንደማይሞት መታሰቡ፣ ለቅሶ የማህበራዊ ትስስር መፍጠርያ ወይም ማፍረሻ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ እንዲሁም ዘመነኛው የለቅሶ ስርዓት ከነባሩ የለቅሶ ስርዓት ጋር ሲነፀር በርካታ ለውጦች እንደሚስተዋሉ ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም የለቅሶ ቃል ግጥሞቹ ተሰብስበው ቢጠኑ ከመሰነድም ባለፈ የህብረተሰቡን ማንነት እና አመለካከት የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቁማለች፡፡ አጥኚዋ በጥናቷ ሰፊና ዝርዝር ጉዳዮችን በማንሳት ትንታኔ ያቀረበች ሲሆን በጥናቱ ውስጥ በሰፊው የትዕምርቶች ትርጉም የሚታይ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የአካባቢውን ባህል እና ቋንቋ ማወቋ ሳይጠቅማት እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹን የሙሾ ግጥሞች ከሚቀርቡበት አውድ ጋር አጣምራ ማቅረብ ብትችል ኖሮ ስራው ይበልጥ የተዋጣለት ይሆን ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃዎቿን የሰበሰበችባቸውን አካባቢዎች በግልፅ አለማስቀመጧም እንደችግር ሊታይ የሚችል ነው፡፡

**ውቤ ታደገ** (2005) "የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ሲል የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቱን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አቅርቧል፡፡ ውቤ "የቤንች ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ"ን በስፋት ዳሷል፡፡ አጥኚው የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ትኩረት ሰጥቶ ተመልክቷል፡፡ በዚህም "የባለቃልቻዋች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የባላባት እና የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"፣ "የወጣቶች የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" እና "የሕፃናት የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" እንዴት እንደሚከወን የእያንዳንዱን አካላት የለቅሶ ስርዓት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ በሚል በሰፊው ተንትኖ አቅርቧል፡፡

ውቤ የጥናቱን ዘዴ እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምንነት፣ እንዴት ከጥናቱ ጋር እንደሚገናኝ እና በምን መልኩ ሊጠቀምበት እንደሚፈልግ ከምሁራን ሀሳብ አጣቅሶ በግልፅ ማሳየቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ ስለሚውሉ ቁሶች ትርጓሜ መስጠቱ እንዲሁም በስርዓቱ ወቅት የሚደረደሩትን የሙሾ ግጥሞች በስፋት ተንትኖ ማቅረቡ የጥናቱን ጥንካሬ ያሳያል፡፡

በውቤ ጥናት ውስጥ እንደ ክፍተት ከሚታዩ ነገሮች መካከል ውቤ ጥናቱ የሚታገገው በ"ከዋኔ መር" የትወራ ማዕቀፍ መሆኑን በአግባቡ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንኑ የትወራ ማዕቀፍ በሌላ መልኩ የጥናቱ ዘዴ አድርጎ ለመጥቀስ መሞከሩ አግባብ መስሎ አልታየኝም፤ ከዋኔ መር የትወራ ማዕቀፍ አንዴ እንደ ንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ዘዴ ሊሆን የሚችል አይመስለኝም፡፡

ከፍ ሲል የቀረቡት ስድስት የኤም.ኤ ዲግሪ ጥናቶች በመሆናቸው በጥናት አደረጃጀት እና አቀራረብ ረገድ ተመሳስሎዎች ይታዩብናል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን የሞገስ ጥናት በጀግና የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮረ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን እድሜን፣ ፆታን እና ማህበራዊ ደረጃን አስመልክተው የሚስተዋሉ የለቅሶ ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ የሚመለከት በመሆኑ በስፋት እንለያያለን፡፡ ሕይወት የጥናቷ አብዛኛው አደረጃጀትም ሆነ አቀራረብ እኔ ከተከተልኩት አደረጃጀት እና አቀራረብ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በየርዕሰ ጉዳዮቹ ስር ከሚነሱት መሰረታዊ ነጥቦች አንፃር እንለያያለን፡፡

የዘላለም፣ የአየሁሽ እና የውቤ ጥናት ትንታኔያቸው የተደራጀው ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር ያሉ ተጨባጭ ሁነቶችን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ የእኔም ጥናት ይሔንኑ አካሔድ የሚከተል በመሆኑ በእጅጉ እንመሳሰላለን፡፡ ይሁን እንጂ በሦስቱም አጥኚዎች ጥናት ውስጥ የሚስተዋሉትን አንዳንድ የስነ ዘዴ ክፍተቶች የእኔ ጥናት ደፍኖ ለመገኘት የሚሞክር በመሆኑ በመጠኑም ቢሆን እንለያያለን፡፡ የማናዬ ጥናት የሚያወሳው ስለ ለቅሶ ስርዓት በመሆኑ የምንመሳሰል ብንሆንም እሱ ትኩረቱን ያደረገው በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት የተለያየ የእምነት ስርዓት ተከታዮች የሚከውኑትን የለቅሶ ስርዓት በንፅፅር ማጥናት ላይ በመሆኑ እንለያያለን፡፡

### 2.1.2.3. የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮሩ ሌሎች ፅሁፎች

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ስር ቅኝት የሚደረግባቸው በ"Ethnological Society Bulletin" ላይ የተለያዩ ብሔረሰቦችን "የለቅሶ እና የሀዘን ስርዓት" አስመልክተው የወጡ የተለያዩ ፅሁፎች ናቸው፡፡ ሁሉም ፅሁፎች የወጡት በአንድ የጥናት መፅሔት ላይ በተመሳሳይ ዘመን በመሆኑ ለአደራደር ቅደም ተከተላቸው የፀሐፊዎቹ ቀዳሚ ፊደል በፊደል ተራ በማሰለፍ ነው፡፡

“THE DEATH CUSTOMS IN THE PROVINCE OF TIGRE” የሚለው **የነጋ ተሰማ** (2002) ፅሁፍ ትኩረት የትግሬ ብሔረሰብን የሀዘን ስነ-ስርዓት ማሳየት ነው፡፡

አጥኚው በቅድሚያ አንድ ሰው በፀና በሚታመምበት ወቅት የተጠኚው ማህበረሰብ በቅድመ ሞት ወቅት የሚከወናቸውን የተለያዩ ተግባራት አንስቷል፡፡ በዚህም አንድ ሰው ከሞሞቱ በፊት ቤተሰቦቹ፣ ዘመዶቹ እና ጎረቤቶቹ ተሰባስበው ታማሚው ይድን ዘንድ ጸሎት የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ የታማሚው ሁኔታ ለከፋ የሚሰጥ መሆኑን ካመኑም ነፍሱ ከመውጣቷ በፊትም ተሰባሰባስበው እንደሚሰናበቱት እና  በሁኔታው አዝነው ስሜታቸውን መቆጣጠር የተሳናቸው በዚህ ወቅት ማልቀስ እንደሚጀምሩም ገልጿል፡፡ አዛውንት ነፍሱ መውጣቷን ሲያረጋግጡ ወዲያውኑ አይኑን፣ አፍንጫውን እና አፉን በመግጠም  የግንዘት ስርዓት የሚያካሄዱ መሆናቸውን፣ የሟችን ዜና እረፍት ከደጅ ሆነው ለሚጠባበቁ ታዳሚዎች እንደሚነገርና ሀዘናቸውን እንደሚገልፁ አመልክቷል፡፡ የሟች ነፍስ አባት ወይም ሌላ ካህን ተጠርቶ ሬሳውን አጥቦ እንዲከፍነው እንደሚደረግና አቅራቢያ ላሉ ሰዎች የሟችን ዜና እረፍት፣ የቀብር ሰዓት እና ቦታውን አስመልክቶ የተመረጡ ሰዎች በተለያዩ አቅጣጫ በሚገኙ ኮረብታዎች ላይ በመውጣት በተቻላቸው መጠን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለአካባቢው በቅብብል እንዲያሰሙ እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍታት የሚደረግ መሆኑን እና ከፍታት በኋላ አራት ወንዶች ፊት እና ኋላ ሆነው አስከሬኑ በመሸከም ቀብሩ ወደሚፈፀምት  ቤተክርስቲያን ጉዞ እንደሚጀመር ጠቅሷል፡፡ ሬሳው የቀብሩ ስፍራ እስኪደርስ ድረስ በየመሀሉ ለአፍታ ረፍት እየተደረገ ጉዞ ፍታት ተደርጎ ሲያበቃ ሴቶች በአዲስ መልኩ በማልቀስ ይጓዛሉ፡፡ ቤተ-ክርስቲያን ደርሶ ልዩ ልዩ ኃይማኖታዊ ስርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ ቀብሩ ይፈፀማል፡፡

ሌሎች በማህበረሰቡ  ዘንድ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች ሲሞቱ ሁለት ጊዜ የለቅሶ ስርዓት የሚፈፀምላቸው መሆኑን ነጋ ገልጿል፡፡ ይህም ራቅ ያለ አካባቢ የሚኖሩ ለቀብር ያልደረሱ የሟች ዘመዶች ሀዘናቸውን በሰፊው እንዲገልጹ ለማድረግ እንዲሁም ከሟች ክብር የተነሳ የተቀናጀ የቀብር ስርዓት እንዲከናወን ለማድረግ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

የሟች ቤተሰቦች አንገታቸው ላይ ነጭ ክር ያስራሉ፣ የጣት እና የጆሮ ጌጣጌጦቻቸውን ያወልቃሉ፣ ልብሳቸውን አይቀይሩም፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ፀጉራቸውን ይላጯሉ፡፡  በተለይ ባሏ የሞተባት ሴት ሀዘኗ ከባድ በመሆኑ ፀጉሯን ቅቤ ሳትቀባ እስከ አንድ አመት ድረስ ልትቆይ

ትችላለች፤ በሀዘን ተቆራምዳ መጎዳቷን ያዩ የአካባቢው ሰዎች ቅቤ ይዘው በመምጣት ሀዘን ሲበዛ ጥሩ አለመሆኑን በመግለፅ ቅቤውን ይቀቧታል፡፡ ከዚህ በኋላ ራሷን መንከባከብ ትጀምራለች፣ የለቅሶ ስርዓቱም በዚሁ ያበቃል፡፡

በነጋ ፅሁፍ የጥናት አካባቢን እና ጥናቱ በዋናነት ያተኮረበትን የህብረተሰብ ክፍል ያለመግለፅ እና መረጃ ከማን እና በምን አይነት ዘዴ እንደሰበሰበ ያለማሳወቅ ችግር ይታይበታል፡፡

**አብደላ አብዱራህማን** (2002) *"The Harrari funeral customs "* በሚል ርዕስ በ"Ethnological society bulltin" በሁለት ክፍል ያቀረበው ፅሁፍ ይገኛል፡፡ የአብደላ ፅሁፍ ትኩረት በሀረር ከተማ እና አቅራቢያው በሚገኙ ገላን እና አሮባን አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የቀብር ስነ-ስርዓት እና በስነ-ስርዓቱ ወቅት ያሉ ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ መግለፅ ነው፡፡

አንድ ሰው ሲሞት የቅርብ ዘመድ ያለው ከሆነ በዘመዶቹ አማካይነት መርዶው ለሚመለከታቸው አካላት ይነገራል፡፡ ነገር ግን ሟች የቅርብ ዘመድ የሌለው ከሆነ ደግሞ በከተማ አስተዳደር በተመደበ ሰው አማካይነት ቤት ለቤት እየተዞረ ይነገራል፡፡ መርዶውን ሟች ወንድ ከሆነ ወንድ፣ ሴት ከሆነች ሴት የሚያረዱ መሆኑም ተያይዞ ተገልጿል፡፡

የቀብር ስርዓቱ የሚጀምረው ሬሳውን ከማጠብ እና ሬሳውን የተለያዩ ነገሮችን ከመቀባት ሲሆን ይህንን ከበድ ያለ ሚና የሚወጡት እድሜያቸው ገፋ ያለ ሴቶች መሆናቸው ተያይዞ ተገልጿል፡፡ የግንዘት ስርዓቱ በዚህ መልክ በሚቀጥልበት ወቅት ወንዶች ደግሞ በሌላኛው ክፍል በመሆን ቅዱስ ቁርዓንን ከፍ ባለ እና ዜማዊ በሆነ መልኩ ያነባሉ፡፡ ቁርዓኑን እያነበቡ የነበሩት አካላት የሟች ሬሳ በሚገኝበት በመቅረብ ዱኣ (ፀሎት) ካደረጉ በኋላ አራት ሰዎች ሆነው ሬሳውን በአልጋ በመሸከም ከሀረር ግንብ ውጭ ወደሚገኘው የቀብር ስፍራ እየተፈራረቁ በቅብብል ይጓዛሉ፡፡

የቀብር ስፍራ እንደደረሱ ሬሳው መቃብር ከመግባቱ በፊት ሁሉም ነብሱን ይምረው ዘንድ ፀሎት ያደርጉለታል፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ቀብሩ የሚከናወነው ዓርብ ዕለት ከሆነ ሬሳው ወደ መስጊድ ተወስዶ ጀመኣው (ለዓርብ የጋራ ፀሎት መስጊድ የተገኘ ሰው ሁሉ) ፀሎት እንዲያደርግለት ይደረጋል፤ ይህ ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ለከፍተኛ ክብር መብቃት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ከቀብር በኋላ በሀዘኑ ቤት ከሚደረጉ ነገሮች መካከል አንዱ "ከፋራ" የተሰኘውን ቂጣ መሰል ጣፋጭ ነገር ለለቀስተኛው አዘጋጅቶ ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ጣፋጭ ቂጣ የሚዘጋጀው አዋቂ ወንድም ሆነ ሴት በሚሞቱበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንዳንዶች አቅማቸው በፈቀደው መልኩ በሬ ወይም ፍየል አርደው ድሆችን የሚያበሉ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ አብደላ ከዚህ በተጨማሪ ሟች ከሞተ አራት ቀን ሲሆነው "ፋታህ" የተሰኘ ኢ-መደበኛ ከበራ በቤተሰቦቹ እና በእድሩ አባላት እርዳታ የሚዘጋጅ መሆኑን ገልጿል፡፡

የአብደላ ፅሁፍ በሀረር እና አካባቢዋ የሚገኙ የለቅሶ ስርዓቶችን በአግባቡ መግለፅ ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ፅሁፉን በቅድመ፣ በጊዜ እና በድህረ ሞት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት በሚል አደራጅቶ ቢያቀርባቸው ይበልጥ ግልፅ ይሆን ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው አብደላም በአለፍ ገደም እንደሚጠቅሰው በአንድ ማህበረሰብ የቀብር ስርዓት ላይ ልዩነት የሚያመጡትን የእድሜ፣ የፆታ እና የማህበራዊ ደረጃ ልዩነቶች ከግምት ውስጥ አስገብቶ የእሱ ፅሁፍ የትኛውን የሚመለከት እንደሆነ በግልፅ ማስቀመጥ ቢችል የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ይሰማኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጥናቱ ልዩ ልዩ ስፍራዎች ላይ ከሚጠቅሳቸው አንዳንድ ኃይማኖታዊ ገፅታዎች መረዳት ይቻላል በሚል አልፎት ሊሆን ቢችልም የጥናቱ ትኩረት የሆነው ኃይማኖት ከእነ ምክንያቱ በግልፅ ማስፈር ነበረበት፡፡

**አንዳርጋቸው ተስፋዬ** (2002) *"Funeral custom of the Kottu of Harar"* ሲል ለ"Ethnological Society Bulletin" ፅሁፉን አቅርቧል፡፡ የአንዳርጋቸው ፅሁፍ የሚያተኩረው የሀረር የቆቱ ጎሳ አባላት የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ ነው፡፡ ቆቱዎች በጋራ ከሚያከብሯቸው ልዩ ልዩ ስነ-ስርዓቶች መካከል አንዱ እና ዋንኛው የለቅሶ ስርዓት ነው፤ ማንኛውም የጎሳው አባል ሞት በማህበሩ ውስጥ ሲከሰት ተገኝቶ የድርሻውን መወጣት መቻል አለበት፡፡ ይህን ሳያደርግ ቢቀር በጎሳው አባላት ከፍ ያለ ቅጣት እንደሚደርስበት ተገልጿል፡፡

አንድ ሰው ወደ ሞት ሲቃረብ የቤተሰቡ አባላት ጎረቤቶቻቸውን ጠርተው በዙሪያው በመቀመጥ "አንድ አምላክ አለ !" ሲሉ ታማሚውም "አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው፣ መሐመድ ነብዩ ነው !" እንዲል ይጠበቃል፤ ታማሚው መናገር ወደማይችልበት ደረጃ ተሸጋግሮ ከሆነ ቤተሰቦቹ ይሉለታል፡፡ ሲቀድም የተጠቀሱት ሀረጋት አንድ የቆቱ ጎሳ በውልደቱ እና በሞቱ ሰዓት የሚሰማቸው መሰረታዊ ሀረጋት መሆናቸውን ፀሀፊው ይጠቅሳል፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት ታማሚውን ከበው ከተቀመጡት ቤተሰቦች መካከል ሴቶች በለሆሳስ ማልቀስ ይጀምራሉ፣ የሟች

ነፍስ መውጧቷ ከተረጋገጠ በአካባቢው ያሉት ሁሉም በጋራ ያለቅሳሉ፡፡ ከእነሱ መካከል በእድሜ ገፋ ያሉት ማልቀስ ተገቢ አለመሆኑን እና ፈጣሪ የመረጠውን መውሰዱን በመጥቀስ እና የሟችን ህይወት በገነት እንዲያኖራት በመፀለይ አልቃሾችን ለማፅናናት እንደሚሞክሩ ተያይዞ ተጠቅሷል፡፡

ከዚህ በኋላ ከጎረቤት ሦስት ሰዎች ተመርጠው አንዱ በአካባቢው ለሚገኙ ሰዎች ለማርዳት ሲላክ፣ ሁለተኛው ለመከፈኛ የሚሆን ነጭ ጨርቅ ገዝቶ እንዲያመጣ ይነገረዋል፣ ሦስተኛው ለመጠጫ የሚሆን ሲኒ ከአካባቢው አሰባስቦ ያመጣል፡፡ በዚሁ ሰዓት በእድሜ ገፋ ያለች ሴት ሬሳውን ለማጠብ የሚበጅ ውኃ ታፈላለች፡፡ ሟች ወንድ ከሆነ በእድሜ ገፋ ያለ ወንድ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ሴት ሬሳውን የማጠቡን ስራ በማከናወን የመከፈኑን ተግባር ይወጡታል፡፡ ሟች ሴት ከሆነች ከእነ መጋጌጫዋ እንደምትቀበር ፀሀፊው አያይዞ ገልጿል፡፡

ሟች ህይወቱ ያለፈው ከሰዓት በኋላ ከሆነ ቀብሩ በነጋታው ስለሚሆን ጎረቤቶቹ በሟች ቤት ውስጥ በመሰብሰብ ምንም እንዳልተፈጠረ አድርገው ለመታየት ሲሞክሩ ትልልቆች የመከፈኑን ስራ ይሰራሉ፣ ወጣቶች ደግሞ የቀብሩን ጉርጓድ ይቆፍራሉ፡፡ ጉርጓዱ ሲቆፈር አንድ ሰው እንደ ልብ ማንቀሳቀስ እንዲችል ተደርጎ ነው፡፡ ይህ የሚሆነውም በቆቱዎች እምነት ሟች በአንዳች መንፈስ ይጠየቃል ተብሎ ስለሚታመን ይህ መንፈስ በመቃብሩ ውስጥ እንዳሻው መሆን ይችል ዘንድ ነው ከሚል እምነት የመነጨ መሆኑን ፀሐፊው ይጠቅሳል፡፡

አንዳርጋቸው የቆቱዎችን የአቀባበር ስርዓት ሲያስረዳ በአንድ ቀን የሞቱት ሰዎች ቁጥር ሁለት ከሆነ በአንድ ጉርጓድ ውስጥ በሚሰናዱ ሁለት ክፍሎች በጋራ የሚቀበሩ መሆኑን ገልጿል፡፡ ከግብረ ስጋ ግንኙነት የራቀች በእድሜ ገፋ ያለች ሴት መቃብሩ ላይ ውኃ በማርከፍከፍ እግዜር መቃብሩን እንዲያቀዘቅዝለት ስትል ትፀልያለች፡፡ የሟች ቤተሰቦች አቅም የሚችል ከሆነ ሬሳው ከቤት ከመውጣቱ በፊት በሬ የሚታረድ መሆኑንም አያይዞ ጠቅሷል፡፡

የቀብር ስርዓቱ እንዳበቃ የሟችን ቤተሰቦች ከፊት በማስቀደም ወደ ቤት ይመለሳሉ፤ የሟች ቤት ደጅ ሲደርሱ በቡድን በቡድን ሆነው ነብሱን ይምረው ዘንድ በመፀለይ ወደ ቤት ውስጥ ገብተው ወንድ እና ሴቱ ብቻ ለብቻ ይቀመጣሉ፡፡ የሞቱ ዜና ዘግይቶ የደረሳቸው ወንዶች ሲመጡ ቀስ ብለው ወደ ለቅሶው ቤት በመግባት ትልልቆቹ ሰዎች ወደ ተቀመጡበት አካባቢ ቀርበው ነብሱን ይምረው ዘንድ ይፀልያሉ፡፡ ዘግይተው የደረሱት ሴቶች ከሆኑ ግን ራሳቸውን በፎጣ ሸፍነው በማልቀስ ሀዘንተኞችን እንደሚቀላቀሉ፣ የማስተዛዘን ስርዓቱም ለሰባት ቀን

እንደሚቆይ በመግለፅ  እና በቆይታው ወቅት የሚከወኑ ተግባራትን በዝርዝር ገልፆ አንዳርጋቸው ፅሁፉን ያጠቃልላል፡፡

አንዳርጋቸው የሀረር ቆቱ ጎሳዎች የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ያቀደውን ዕቅድ ከሞላ ጎደል አሳክቶታል ማለት ይቻላል፡፡ ከሞላ ጎደል እንዲባል ያስቻለው አንዳንድ ክዋኔዎች ትንታኔ የሚያስፈልጋቸው ሆነው ሳሉ ፀሀፊው ግን ያንን ሲያደርግ የሚስተዋል ባለመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ቀን የሞቱት ሰዎች ቁጥር ሁለት ከሆነ በአንድ ጉድጓድ የሚቀበሩ መሆኑን ከመግለፅ ባሻገር ለምን እንዲህ እንደሚደረግ የሚለው ነገር የለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአንድ ቀን የሞቱት ቁጥር ከተጠቀሰው በላይ ቢሆንስ ምን ይደረጋል የሚል ጥያቄ ለተከሰተለት ሰው የሚሆን ምላሽ በፅሁፉ ውስጥ አይገኝም፡፡

**ፋሲካ በለጠ** (2002) "THE DEATH CUSTOM AMONG THE AMHARAS OF SAWA" በሚል ርዕስ በ"Ethnological Society Bulletin" ላይ አጠር ያለ ፅሁፏን አውጥታለች፡፡ የፋሲካ ፅሁፍ ዋንኛ ትኩረት የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ የሸዋ አማራዎች የቀብር እና የሀዘን ስነ-ስርዓትን መግለፅ ነው፡፡ አጥኚዋ ይህ ስርዓት ለዘመናት የቆየ እና አብዛኛው ገፅታው ዛሬም ድረስ እየተተገበረ ያለ መሆኑን በመግለፅ ምናልባት ይህ ክዋኔ በአንዳች ሁኔታ ከመረሳቱ ወይም ከመጥፋቱ በፊት ቀርሶ ማስቀመጥ ተገቢ በመሆኑ ትኩረት መስጠቷን ትገልፃለች፡፡

ፋሲካ መረጃዎቿን የሰበሰበችው ስለ አካባቢው ጥልቅ መረጃ ካላቸው እድሜ ጠገብ አዛውንቶች እንደሆነ በመጥቀስ ይህን ማድረግ የወደደችውም መረጃ አቀባዮቿ በተለይም ሊቀ ጠበብት እና አክሊለ ብርሃን የአካባቢውን ህብረተሰብ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች በአግባቡ የሚያውቁ በመሆናቸው መመረጣቸውን ታስረዳለች፡፡ ከእነዚህ አካላት ያገኘቻቸውን መረጃዎች በሁለት ክፍል አደራጅታ አቅርባለች፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ያለውን ሂደት የተመለከተችበት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከቀብር እስከ ሁለት ዓመት (የሀዘን ስርዓቱ ምናልባትም እስከ 14 ዓመት ሊቆይ እንደሚችልም በመጥቀስ) የሚቆየውን የሀዘን ስርዓት የተመለከተችበት ነው፡፡

የቀብር ስነ-ስርዓቱን በአምስት ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍላ ነው ያቀረበችው፡፡ አንደኛው *"The making of the last will"* ያለችው ሲሆን ታማሚው አስጊ ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚፈፅመውን ኑዛዜ እና መሰል ተግባራትን የምታብራራበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል *"Breaking the news"* የሚል ሲሆን የሞቱ ዜና ለወዳጅ ዘመድ የሚነገርበትን መንገድ ያስረዳችበት ነው፡፡

ሦስተኛው ክፍል *"The service for the dead"* በሚል የቀረበ ሲሆን፡፡ በዚህ ክፍል ሟች ከመቀበሩ በፊት የሚደረጉ ሀይማኖታዊ ክዋኔዎች ተገልፀዋል፡፡ በአራተኛነት *"The funeral process"* በሚል የቀብር ስርዓቱ ምን እንደሚመስል የተገለፀበት ነው፡፡ የቀብር ስርዓቱን የመጨረሻ ሂደት የምታስረዳው "at the grave" ብላ በምትጠቅሰው ክፍል ውስጥ ነው፡፡

ሌላው የፋሲካ ጥናት ሁለተኛው አበይት ርዕሰ ጉዳይ "Mourning customs" በሚል የሀዘን ስርዓቱን የገለፀችበት ክፍል ነው፡፡ አጥኚዋ በዚህ ክፍል "weeping"፣ "decoration" እና "clothing" በሚሉ ሦስት ጉዳዮች ላይ አተኩራለች፡፡ የሀዘኑ ስርዓት እንደ ሟች ማንነት (የስጋ ዝምድና ቅርበት) ከዓመት እስከ ሁለት ዓመት ሊቀጥል የሚችል መሆኑን በመግለፅ የሟች ቤተሰቦች እና ዘመዶች በዚህ ወቅት የሚፈፅሟቸውን ተግባራት ከፍ ሲል በተጠቀሱት ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ስር ታብራራለች፡፡

"weeping" ስትል የምትገልፀው የሟች ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶች እና የለቅሶ ስርዓቱ ታዳሚዎች በግበዓተ መሬት ፍፃሜው ወቅት እና ከዚያም በኋላ እንዳላቸው ቅርበት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሟችን በጎ ገፅታዎች በመጥቀስ በቡድን አሊያም በተናጠል የሚያለቅሱበትን ሂደት ነው፡፡

አጥኚዋ "decoration" ስትል በምታብራራው ክፍል ሀዘንተኞች እስከ አርባ ወይም እስከ ሰማኒያ ቀን ድረስ ምንም አይነት ጌጣ ጌጥ እንደማይጠቀሙ፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ፀጉራቸውን እንደሚላጩ ወይም እንደሚያሳጥሩ፣ ጥፍራቸውን እንደማይቆረጡ፣ ወንዶች ፂማቸውን እንደማይላጩ፣ ቀደም ሲል ጫማ ያደርጉ ከነበር በባዶ እግራቸው እንደሚሄዱ፣ አጎዛ መሰል ነገር በማንጠፍ ባዶ መሬት ላይ የሚተኙ ስለመሆናቸው፣. . .ወዘተ ትገልፃለች፡፡ ይህም የሚሆነው በሟች ሀዘን መጎዳታቸውን ይገልፅላቸው ዘንድ ነው ስትል ምክንያቱንም ታስቀምጣለች፡፡

ፋሲካ የጥናቷ መጨረሻ ባደረገችው "clothing" በሚለው ክፍል በሀዘን ወቅት ተግባራዊ የሚደረገውን የአለባበስ ስነ-ስርዓት የቃኘችበት ነው፡፡ የሸዋ አማራዎች በሀዘናቸው ወቅት ጥቁር ወይም ሴቶች ነጠላቸውን ጉሎ ነክረው ለ12 ቀን ገልብጠው እንደሚለብሱ ትጠቅሳለች፡፡ በተጨማሪም ሟች ከሞተ በ3ኛ፣ በ7ኛ፣ በ12ኛ፣ በ40ኛ፣ በ80ኛቀኖች እንዲሁም በ6ኛ ወር እና በ1ኛ ዓመት ላይ ከወትሮው በተለየ የሚለቀስለት መሆኑን ታስረዳለች፡፡

ፋሲካ በጥናቷ በለቅሶ እና በሀዘን ስርዓቱ ወቅት የሚከወኑ መሰረታዊ ነገሮችን በአግባቡ መግለፅ መቻሏ በጠንካራ ጎኑ ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፋሲካ ጥናት ውስጥ አንዳንድ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ ከእነዚህም የጥናቷን ተተኳሪ ማህበረሰብ እና አካባቢ በአግባቡ አለመጥቀሷ የመጀመሪያው ነው፡፡ ይህም ማለት ፋሲካ ". . .I have set out to describe the funeral and mourning customs commonly observed by the christian Amharas of sawa." (2002፣ 204) በሚል አንድ አረፍተ ነገር ነው የጥናቷን ተተኳሪ ማህበረሰብ እና አካባቢ የገለፀችው፡፡ ችግሩ ያለው በአጭር መገለፁ ላይ ሳይሆን ስለሚጠናው ማህበረሰብ ግልፅ ያለ መረጃ የሚሰጥ ካለመሆኑ ላይ ነው፡፡ ሸዋ ውስጥ እንደሆነ ከመጥቀስ ባሻገር  በየትኞቹ ቀበሌዎች ላይ እንደሚያተኩር በግልፅ መቀመጥ ነበረበት፡፡ ምንም እንኳ በጥናቱ ውስጥ ከሚተገበሩ አንዳንድ ጉዳዮች በመነሳት የጥናቱ ትኩረት "የኦርቶዶክስ" ክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ መሆኑን ለማወቅ እንችል እንደሆነ እንጂ "ክርስቲያን" ብቻ ብላ ማለፏ አሻሚ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥኚዋ መረጃ የሰበሰበችባቸውን መንገዶችም በግልፅ አላስቀመጠችም፡፡ በጥናቱ ውስጥ ሲከወኑ የሚታዩ አንዳንድ ተግባራት ለምንነታቸው በግልፅ መብራራት ሲኖርበት ይህ እንዲሆን አልተደረገም፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር የተመለከትናቸው አራት ፅሁፎች ለጥናት መፅሔት እንዲስማሙ ተደርገው የተሰናዱ በመሆናቸው በተጠኚው ማህበረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚስተዋሉ ዝርዝር ጉዳዮችን መዳሰስ ላይ ትኩረት ባያደርጉም እነዚህን የጥናት ውጤቶች ማንበቤ ተጨማሪ ግንዛቤ ፈጥሮልኛል፡፡

## 2.2. የፅንሰ ሀሳቦች እና ንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ክፍል ጥናቱ የሚያተኩርበትን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከቱ "ፅንሰ ሀሳቦች" እና ጥናቱ የሚመሰረትባቸው "ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች" ይቃኛሉ፡፡ በቅድሚያ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ማዕከል ያደረጉት ፅንሰ ሀሳቦች ቀጥሎም ጥናቱ የሚታገግባቸው ንድፈ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ የመቀዳደማቸው ምክንያት በቅድሚያ ጥናቱ የሚያተኩርበትን ርዕሰ ጉዳይ አብራርቶ ጥናቱ ወደሚመራበት ንድፈ ሀሳብ ማለፍ የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥራል ከሚል እምነት ነው፡፡

### 2.2.1. የፅንሰ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ስር ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ቁልፍ ርዕሰ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ፡፡

#### 2.2.1.1. የሞት እና የለቅሶ ምንነት

ሞት እና ህይወት ፍጥረታት ሁሉ የሚጋሩት የጋራ ገፅታ ነው፡፡ በተለያዩ ማህበረሰቦች እምነት የሚፈጥረው እና የሚገለው አካል ማንነት በተለያየ መልኩ የሚገለፅ ቢሆንም ሞት የመኖሩ ሀቅ አብዛኛውን (ሁሉም ማለት ካልተቻለ) የሚያስማማ ነው፡፡ የሞትን ምንነት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት "የነፍስ ከስጋ መለየት፣ የህይወት ፍፃሜ፣ እልፈት፡፡" (1993፣ 85) ሲል ይገልፀዋል፡፡ በዚህ አገላለፅ መሰረት አንድ ሰው (ማንኛውም ፍጡር) ሞተ ሊባል የሚችለው እስትንፋሱ ከስጋው ስትለይ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር በተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ደግሞ ሞት የሚለው ቃል "የነፍስና የስጋ መለየት ወይም ህይወትን ማጣት፡፡ ይህም በስጋዊም በመንፈሳዊም ሊሆን ይችላል፡፡" (1972፣ 62) የሚል ብያኔ ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህኛው ብያኔ ከቀደመው ብያኔ ጋር የሚመሳሰል ነገር ቢኖረውም መዝገበ ቃላቱን እንዳዘጋጀው ተቋም አስተምህሮ የሚለይ ነገርም አለው፡፡ ይኸውም በዚህኛው አገላለፅ ሞት የሚከሰተው በስጋም በነፍስም ላይ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ማለት በክርስትናው እምነት መሰረት "የመንፈስ ሞት" የሚባለው አንድ ሰው የኃይማኖቱ ቀኖና እና ዶግማ ከሚፈቅደው ውጪ በመሆን ልዩ ልዩ ተግባራትን ፈፅሞ ሲገኝ ነው፤ ከመንፈሳዊ ህይወቱ ተገልሏል፣ ነፍስ የዘራለት ፈጣሪውን አስቀይሟል፣ በመሆኑም እሱ ያለው በአካል እንጂ በመንፈሱ ሞቷል እንዲል፡፡ "የስጋ ሞት" የሚባለው ደግሞ አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ተለይታ "ሰው" ከሚለው መጠሪያው ተፋቶ "ሬሳ" ተብሎ ሲጠራ ነው፡፡

Untiedt የተባለ ፀሀፊ የሞትን ምንነት "Death is a mystery, and it will remain so forever." (2008፣ vii) በማለት ገልጿል፡፡ ከዚህ ፀሀፊ አገላለፅ አንፃር ሞት ብዙ ያልተፈቱ እንቆቅልሾች ያሉት እና ሁሌም የሚከሰት መሆኑን እንረዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ለቅሶ" የሚለውን ቃል "ሀዘን፡፡ ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፡፡ መጮህ፣ ማንባት፡፡ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ፡፡" (1993፣ 17) ሲል ይበይነዋል፡፡ ይህ ጥቅስ እንደሚነግረን አንድ ሰው ሲሞት ህብረተሰቡ ሀዘኑን በተለያዩ መንገዶች የሚገልፅ መሆኑን ነው፡፡ ሀዘንተኛው ሀዘኔን ያስታግስልኛል ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውንም አይነት ተግባራት በሰዓቱ የሚፈፅም መሆኑንም እንረዳለን፡፡

በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በለቅሶ ክዋኔ ወቅት የሚቀር የለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ወቅት የሟች ወገን ወዳጅ እና ጠላቱን የሚለይበት ወቅት በመሆኑ ነው፤ ግጭት ውስጥ የገቡ ሰዎች እጅግ የተካረረ ሁኔታ ውስጥ መግባታቸው የሚታወቀውም አብዛኛውን ጊዜ "ቀብሬ ላይ አትድረስ፤ ቀብርህም ላይ አልደርስም !" ሲባባሉ ነው፡፡ በመሆኑም ከሞት በኋላ እንኳ ቂሙን የማይዘነጋ ህብረተሰብ ውስጥ ተወልዶ ላደገ የለቅሶ ክዋኔ ላይ መቅረት እጅግ እማይታሰብ ነው የሚሆንበት፡፡

የለቅሶ ስርዓት ተሳታፊዎችን ማንነት እና የቀብር ስርዓቱን አከዋወን በተመለከተ Kohen "In all societies, when a person dies, family, friends, and neighbors respond in structured, patterned ways to the death." (1980፣ 1) በማለት ይገልፃል፡፡

እንደ Kohen አገላለፅ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ሞት በሚከሰትበት ጊዜ ቤተሰብ፣ ጓደኞች እና ጎረቤቶች ስርዓት ባለው እና በተቀናጀ ሁኔታ ሀዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ኢትዮጵያዊ በሆነ ባህል ውስጥ ያደገ ሰው ደግሞ ፀበኛም ቢሆን የቀብር ዕለት ተገኝቶ "እኔ ይቅር ብዬሀለሁ፤ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ" ሲል የሚስተዋልባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ስለሆነም የለቅሶ ስርዓት በሚኖርበት ወቅት ወንዱ እርሻውን ጥሎ፤ ሴቷም ማድቤቷን ዘግታ ሞት በተከሰተበት ስፍራ ተገኝተው ሀዘናቸውን መግለፅ የተለመደ ተግባር ነው፡፡

### 2.2.1.2. የቀብር ምንነት እና አከዋወን

በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ሞት በሚከሰትበት ጊዜ ቅድመ ቀብር ክንውኖቹ አስቀድሞ በመፈፀም የሞተን መቅበር የነበረ ስርዓት ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ

እንደየባህሉ ወግ እና ልማድ መደረግ ያለባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ተከናውነው ግብዓተ መሬቱ የሚፈፀምበትን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ግብዓተ መሬቱ የሚፈፀምበት ወይም የተፈፀመበት ስፍራ ደግሞ "መቃብር" ተብሎ ይጠራል፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "ቀብር" ለሚለው ቃል "ቀበራ፣ አቀባበር፣ ግንዘት፣ አገናነዝ፣ የሬሳ ህግ፣ ሽቱ መቅባት፣ ማጠን፣ ማጤስ፣ መፍታት፣ ማልቀስ፣ ርግዶ ሙሾ፣ የመሰለው ኹሉ" (1948፣ 781) የሚል ብያኔ ሰጥተውት እናገኛለን፡፡ ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ቀብር ኃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓቶች በጋራ የሚስተዋሉበት መሆኑን ነው፡፡ ይህም ማለት የቀብር ስርዓት አፈፃፀም እንደየባህሉ እና ወጉ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ እንደሚከተለው የእምነት ስርዓትም የሚለያይ መሆኑንም ይጠቁመናል፡፡ በሀገራችን የክርስትና እምነት ተከታይ የሆነ ሰው ሲሞት ሟች እንዳለው የእምነት ደረጃ የሚደረግለት የግንዘት እና የፍታት ስርዓት ስርዓት የተለያየ ነው፡፡ የቀብር ጉርጓድ አቆፋፈር እና አቀባበር ስርዓቱ ግን በአብዛኛው ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በክርስትናው የቀብር ስርዓት ወቅት የተመለከትነውን በእስልምና እምነት ተከታዮች የቀብር ስርዓት ወቅት ላናገኘው እንችላለን፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ የቀብር ስርዓት አፈፃፀም እንደ ሟች ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ዕድሜ እና ባህላዊ ስልጣን የሚወሰንበት አጋጣሚ መኖሩን Linton (1964፣ 113) ያስረዳል፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የቀብር ስርዓት ሞት እንደተከሰተበት ብሔረሰብ ባህል እና ደንብ ይለያያል፡፡ ይህ ልዩነት ከሚስተዋሉባቸው ልዩ ልዩ ገፅታዎች መካከል በቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብር እና ድህረ ቀብር ወቅት የሚፈፀሙት ተግባራት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በተጠቀሱት እርከኖች ስር ሊፈፀሙ የሚችሉ ክንውኖችን በአጭሩ እንመልከት፡፡

በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ አንድ ሰው ያለበት ሁኔታ ወደ ሞት የሚያደርሰው ሆኖ ከታሰበ ተጠርጣሪው ሰው ነፍሱ ከስጋው ከመለየቱ በፊት የሚፈፀሙ በርካታ ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ታማሚው ህይወቱ ከማለፉ በፊት በህይወት ዘመኑ የሰራቸውን ሀጢያቶች ለሚመለከታቸው አካላት እንዲናዘዝ በማድረግ ፈጣሪ ነፍሱን እንዲምራት መፀለይ፣ ታማሚው ሀብት ንብረት ያፈራ ከሆነ ይህን የተመለከተ ኑዛዜ እንዲፈፅም ማድረግ፣. . .ወዘተ የሚሉት ናቸው፡፡ የታማሚው ህይወት ካለፈ በኋላ ደግሞ በዚሁ እርከን ከሚፈፀሙ ተግባራት መካከል የሬሳ አጠባ፣ ግንዘት እና የፀሎት ስርዓት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሟች

ቤተሰቦች እና እድርተኞች አማካይነት ለወዳጅ ዘመድ የቀብሩ ዜና እንዲደርስ ማድረግ እና ከቀበር መልስ እና ለሀዘን ወቅት የሚሆን ምግብ እና መጠጥ ማዘጋጀትን፣. . .ወዘተ ይጨምራል፡፡ የቀብር ቦታ ዝግጅትም የዚሁ የቅድመ ቀብር ክንውን አካል ነው፡፡

በጊዜ ቀብር የክንውን ደረጃ የማህበረሰቡን እምነት እና ፍልስፍና እንዲሁም ኃይማኖት መሰረት ባደረገ መልኩ የሟች ግብዓተ መሬት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ እንደ አብዛኛው ማህበረሰብ እምነት በዚህ ወቅት የሚኖረው ለቅሶ መሪር ነው፡፡ ምክንያቱም ከሟች ጋር የሚኖራቸው የመጨረሻዋ የስንብት መድረክ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ አብዝቶ ማንባቱ፣ ደረት መምታቱ፣ ፀጉር መንጨቱ፣ መውደቁ፣ መነሳቱ፣ ሙሾ ማውረዱ፣ የሟችን ፎቶ እና ልብስ ይዞ መንሰቅሰቁ፣. . .ወዘተ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በዚህ ወቅት  የሚከናወኑ ናቸው፡፡

ቀብሩ በሚሸኝበት ወቅት ያለው የዖታ እና እድሜ ጉዳይ፣ የቀብር ሾኚዎች ቅደም ተከተል፣ በቀብሩ ወቅት የሚፈፀሙ የፀሎት፣ የቀብር እና የአቀባበር አቅጣጫ፣ በሬሳው ላይ በተዋረድ አፈር መርጨት፣ በቀብሩ ላይ እርጥብ ነገር መትከል፣. . .ወዘተ በዚህ እርከን ተግባራዊ ከሚደረጉት ክንውኖች በዋናነት የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

ድህረ ቀብር ክንውን የሟች ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚመለከት ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል ከቀብር መልስ ቤት ከመገባቱ በፊት እጅን ታጥቦ ውኃ ወደ ኋላ መርጨት፣ በሀዘኑ ቤት የተዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥ መመገብ፣ ማስተዛዘን፣ ሀዘንተኞችን መሰናበት፣. . .ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሟች የሞተበትን 3ኛ፣ 7ኛ፣ 12ኛ፣ 40ኛ፣ 80ኛ፣ የመንፈቅ እና ሙት ዓመት፣ 7ኛ እና 14ኛ ዓመት መታሰቢያ ስርዓቶችም እዚሁ እርከን ስር ተካተው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በተጠቀሱት እርከኖች ስር የሚፈፀሙት ክንውኖች እንደየማህበረሰቡ ባህል እና እምነት የሚለያዩ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

### 2.2.1.3. *ፆታን መሰረት ያደረገ የለቅሶ ስርዓት*

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሞት በተከሰተባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ለቅሶ የሚሰናዳበት ስርዓት አንድ ሆኖ አይታይም፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ከሚከሰቱባቸው በርካታ ምክንያቶች አንዱ ፆታ

ነው፡፡ በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ወንድ ሲሞት እና ሴት ስትሞት የሚኖረው የለቅሶ ስርዓት ከስርዓተ ግንዘት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜው ድረስ የሚለያዩባቸው ነጥቦች አሉ፡፡

ይህን ጉዳይ Kottack የተባለ የተባለ ፀሀፊ "Gender refers to the cultural construction of sexual differences. Male and Female are biological sexes that differ in their x and y chromosomes. Culture takes that biological difference and associates it with certain activities: beehavior, and ideas. (2002: 460) በማለት በተፈጥሮ ሳቢያ የመጣውን የፆታ ልዩነት ባህል ወስዶ ልዩ ልዩ ክፍፍሎችን እና ተግባራትን ለመፈፀም እንደሚገለገልበት ያስረዳል፡፡

በተለይም ብዙም ባልሰለጠኑ ህዝቦች መካከል ከፆታ ረገድ የሚኖረው ልዩነት በስራ ክፍፍል፣ በአዋዋል፣ በአስተዳደር እና በአመጋገብ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ሞት በማህበሩ ውስጥ በሚከሰትበት ጊዜም አልፎ አልፎ የሚስተዋል ነው፡፡

ከኃይማኖት አንፃርም በግንዘት ስርዓቱ ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ወንድ ሲሞት የሚኖረው ዝግጅት እና ሀዘን ሰፋ ያለ ሆኖ ሲታይ ለሴቶች የሚደረገው ግን በአንፃሩ ጠበብ ያለ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ካስቻሉት ምክንያቶች መካከል "ሞት የመጣው በሴት ነው" ከሚል እና ወንድ የቤቱ ጋሻ/ መከታ ተደርጎ የሚታሰብ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከፆታ አንፃር የሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚኖሩ ልዩነቶችን በተወሰነ መልኩ ዳሷል፡፡

#### 2.2.1.4. ማህበራዊ ደረጃን መሰረት ያደረገ የለቅሶ ስርዓት

ሀብታም - ደሃ፣ ጀግና - ፈሪ፣ ጌታ - ሎሌ፣. . .ወዘተ የሚሉ መንትያ ተቃርኖዎችን መመልከት በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ለተለያዩ ሰዎች ሲሰጥ መመልከት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይህ በህብረተሰቡ የተሰጠው ደረጃ ሰውየው ከዚህ ዓለም በሞት ሲሰናበትም በሚደረግለት ስርዓት ወቅት ሲንፀባረቅ ይስተዋላል፡፡ Brown ይህንን ሀሳብ ". . .Societies mark the individual's progression from role to role by changing his name or by giving him designations that indicate each particular role." (1963፣ 49) በማለት ይገልፀዋል፡፡

ማህበረሰቡ ሰውየው በህይወት ሳለ ከሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ተግባራት በመነሳት የተለያዩ መጠሪያዎችን እና ማህበራዊ ደረጃዎችን እንዲጎናፀፍ ያስችለዋል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ለሰውየው ባበጀው ማንነት ልክ በተለያዩ መድረኮች ላይ ቅደም ተከተሉን ያበጅለታል፡፡ ከእነዚህ መድረኮች አንዱ ደግሞ "የለቅሶ ስርዓት" ነው፡፡ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ መመዘኛዎች ከፍ ያለ ቦታ የተሰጠው ሰው ሲሞት እና መደዴው ሲሞት የሚኖረው የለቅሶ ስርዓት ዝግጅት አንድ አይደለም፡፡

ከፍ ሲል የጠቀስነውን ሀሳብ አስመልክቶ Brown "when death takes. . .some important member of the group the whole comunity becomes involved every where poeple the fact of grief and almost every where there are patterns of murning." (1963፣ 60) ሲል ያብራራል፡፡ እንደ Brown ሀሳብ በማህበረሰቡ ውስጥ ጠቃሚ ተደርጎ የሚታሰብ አንድ ሰው ሲሞት የሚኖረው ሀዘን ከዳር ዳር የሚዘልቅ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖርን የለቅሶ ስርዓት የተለያየ እንዲሆን ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ማህበራዊ ደረጃ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እድሜ ሌላው የለቅሶ ስርዓት ልዩነት መፍጠሪያ መድረክ መሆኑንም ግልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ከፍ ሲል የቀረቡት የልዩነት መፍጠሪያ መድረኮችን ከግምት ውስጥ በማስገባ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

### 2.2.2. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

ይህ ጥናት በፎክሎር ዘርፍ ከሚጠኑ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱ በሆነው "የለቅሶ ስርዓት" ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓት ደግሞ ከአራቱ አበይት የፎክሎር ዘውጎች ውስጥ በ"ሀገረሰባዊ ልማድ" እንደሚመደብ ፈቃደ (1991፣ 14) ያስረዳል፡፡ በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ ሰው ሲሞት አልቅሶ መቅበር የተለመደ ተግባር ነው፡፡ የአለቃቀስ ስርዓቱ በሁሉም ብሔረሰቦች ዘንድ አንድ አይነት እና ወጥ አካሔድን ተከትሎ የሚፈፀም ባይሆንም የትኛውም የማህበረሰብ ክፍል ሰው ሲሞትበት የሚያከናውናቸው የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች አሉት፡፡ ይህን በተመለከተ ዘሪሁን "በአንዱ የለቅሶ ስነስርዓት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል፣ ይዘለላል፡፡ በሌላው ደግሞ የሟች ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ፣ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፡፡ በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የለቅሶ ክዋኔ ይደረጋል፡፡ በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ፡፡" (1992፣ 22) በማለት ያብራሩታል፡፡

Cohen የተባለ የስነ ሰብ ተመራማሪ በበኩሉ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሞት ሲከሰት የቀብር፣ የአለቃቀስም ሆነ የሀዘን ስርዓቱ ማህበረሰቡ በጋራ እንዳደራጃቸው ደንብ እና መመሪያዎች የሚወሰኑ መሆናቸውን "Cultural guidelines determine the treatment and disposal of the body and prescribe a period of mourning for close relatives." (1980፣ 1) በማለት ይገልፃል፡፡

ከተጠቀሱት ሀሳቦች በግልፅ የምንረዳው የትኛውም ማህበረሰብ ወገኑን በሞት ሲነጠቅ የሚቀብርበት የራሱ የሆነ ስነ-ስርዓት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሞት ሲከሰት ሀዘን አለ፣ ሀዘን ሲያጋጥም ደግሞ ሀዘን መግለጫ መንገዶች ተያይዘው ይነሳሉ፡፡ ከእነዚህ ሀዘን ከሚገለጥባቸው መንገዶች ደግሞ ዋንኛውን ስፍራ የሚይዘው ለቅሶ ነው፡፡ አስቀድመን ለመጥቀስ እንደሞከርነው ለቅሶ ደግሞ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ በተለያየ መልኩ የሚከወን ነው፡፡ ስለዚህ ይነስም ይብዛ፣ ይስፋም ይጥበብም ይኼን ስርዓት ለማስኬድ በየማህበረሰቡ የሚዘጋጅ ከበራ[2] (Ritual) አለ:: ከበራው ደግሞ እንዲሁ በደረቁ የሚቀርብ ሳይሆን ከክዋኔ ጋር ነፍስ እና ስጋ ሆነው ነው የሚቀርቡት፡፡ በመሆንም ይህ ጥናት በከበራ እና በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ላይ እንዲመሰረት ሆኗል፡፡ ከዚህ በማስከተል እነዚህ ጥናቱ የሚመራባቸውን ንድፈ ሀሳቦች በዝርዝር እንመልከት፡፡

#### 2.2.2.1. ከበራ (Ritual)

አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ውስጣዊ ስሜቱን ከፍ ባለ መንገድ ለመግለፅ የሚሻው (የሚገደደው) በማህበሩ ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶች ሲፈጠሩ ነው፡፡ ከዝግጅቶቹ አንዱ የሞተን ሰው ለመቅበር የሚሰናዳው ከበራ ነው፡፡ በከበራው ወቅት ገሚሱ ሲወድቅ - ሲነሳ፣ ሌላው ፀጉሩን ሲነጭ - ፊቱን ሲቧጥጥ፣ እኩሉ ጦር ጎራዴ (አንዳች አይነት ባህላዊ መሳሪያ) ይዞ ሲፎክር - ሲያቅራራ፣ የቀረው በለሆሳስ በማንባት፣. . .ወዘተ ሀዘኑን ሲገልፅ መመልከት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በከበራው ወቅት ከሚቀነቀኑ - ከሚዜሙት፣ ከሚለበሱ - ከሚጫሙት፣ ከሚጠለቁ - ከሚነገቱት፣ ከሚወድቁ -ከሚነሱት፣. . .ወዘተ ልዩ ልዩ ክንውኖች በመነሳት የአንድን ማህበረሰብ ውስጣዊ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ኢኮኖሚያዊ አቅም፣ እምነት እና ፍልስፍና በውል የምንረዳበት አጋጣሚ ይፈጠርልናል፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ እነ Sims "Groups frequently devise ceremonies or performances that enact deeply held beliefs or values. These

[2] "Ritual" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል አብዛኞቹ እኔ የተመለከትኳቸው ፅሁፎች "ክብረ በዓላት" የሚል ትርጉም ሰጥተውታል አግኝቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ከምሰራበት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚሰምር መስሎ ስላልተሰማኝ ነው "ከበራ" እያልኩ ለመጠቀም የወደድኩት፤ በአጭሩ "ክብረ በዓል" ደስታን እንጂ ሀዘንን የሚጠራ መስሎ ስላልተሰማኝ ነው፡፡

are rituals, and they make our inner experiences of traditions visible and observable to members of the group and often to outsiders." (2005፣ 94) በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ከፍ ሲል በእነ Sims የተገለፀውን ሀሳብ Dorson "ከበራዎች በስርዓት የተቀናጁ እና የተሳታፊ አካላቱን አስተሳሰብ ትዕምርታዊ በሆነ መልኩ የሚገልጡ ናቸው፡፡" (1972፣ 160) በማለት ያጠናክረዋል፡፡ አስቀድመን እንደጠቀስነው ከፍ ሲል የተጠቀሱት ሁለት የፎክሎር ተመራማሪዎች ሀሳብ የሚነግረን በከበራ ወቅት የሚታዩት ልዩ ልዩ ክዋኔዎች በዘፈቀደ የሚሆኑ ሳይሆን ማህበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ የሚፈፅማቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን አመለካከት እና ፍልስፍና የመግለጥ አቅማቸው ከፍ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በአንዳች ምክንያት ከበራ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ እንዲሁ በደረቁ የሚቀርብ ሳይሆን በልዩ ልዩ የፎክሎር ዘውጎች ህብር አምሮና ደምቆ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ እነ Sims እንደሚከተለው በትባት ይገልፁታል፡፡ "Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and costumes." (2005፣ 95)፡፡ በመሆኑም በአንድ ከበራ ላይ፤ ለምሳሌ በለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ የሙሾ ግጥምን ሳይወዱ በግድ እንዲያለቅሱ የማድረግ አቅም ባለው ዜማ እና ቅላፄ የሚያወርዱ፣ የአራዊት ቆዳ ለብሰው ጦር እና ጋሻ በመያዝ የሚፎክሩ እና የሚሸልሉ፣ ደረታቸውን የሚደቁ፣ እየወደቁ የሚነሱ፣ ፊታቸውን የሚቧጥጡ፣ ፀጉራቸውን የሚነጩ፣. . .ወዘተ ሰዎችን መመልከት ሰርካዊ ክንውን ነው፡፡ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ በአንድ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ ስነ-ቃሉንም፣ ቁሳዊ ባህሉንም፣ ትውን ጥበባቱን እና ሀገረሰባዊ ልማዱን መመልከት የሚቻለን መሆኑን ያሳያል፡፡

ከበራዎች "መንፈሳዊ (sacred)" እና "አለማዊ(secular)" ተብለው ለሁለት እንደሚከፈሉ እነ Sims ያስረዳሉ፡፡ መንፈሳዊ ከበራዎች በዋናነት ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች በተለይ ከቅድስና እና ከመንፈሳዊ ነገሮች ጋር የሚገናኙ ሲሆን በአብዛኛው ትዕምርታዊነት እና ዜማዊነት የሚያጠላባቸው ናቸው፡፡ ይህ የከበራ አይነት የከዋኞቹን እምነት ተጨባጭ በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን እና ተሳታፊዎቹ በእምነታቸው ስለአለም ያላቸውን አተያይ፣ ስለሰዎች ያላቸው አመለካከት፣ እሴቶቻቸውን፣ የህይወት ፍልስፍናቸውን...ማስተላለፍ እንደሚችሉ እነ Sims (2005፣102) ያብራራሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዓለማዊ ከበራዎች የሚሰኙት ከኃይማኖት ስርዓት ውጭ ያሉት ከበራዎች ናቸው ሲሉ እነ Sims (2005፣ 103) ፅፈዋል፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል ከተገለፁት

ከበራዎች አንፃር ይህ ጥናት የሚያተኩርበትን ርዕሰ ጉዳይ መመደብ ቢያስፈልግ ሁለቱም የከበራ አይነቶች ተዛንቀው የሚታዩበት መሆኑን መመስከር ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በሀገራችን ሙስሊሙም ክርስቲያኑም አልቅሰው የሚቀብሩ ከመሆናቸው አንፃር የሚመሳሰሉ ቢሆኑም ከአገናነዝ እና ከአቀባበር ስርዓት አኳያ ግን ሰፊ ልዩነቶች መኖራቸውን ነቅሶ ማውጣት ይቻላል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው እነ Sims ዓለማዊ ከበራ ኃይማኖታዊ ስርዓት የሚስተዋልበት እንዳልሆነ አድርገው ቢጠቅሱም በተለይም በሀገራችን በአንዳንድ ከበራዎች ላይ (ለምሳሌ በለቅሶ እና በጥምቀት) በእጅጉ ተዛንቀው ይገኛሉ፡፡

ከበራዎች ለማህበረሰቡ የሚያስገኙትን ጠቀሜታ አስመልክቶ Dorson ከበራዎች ማህበራዊ ትስስርን ከማጠናከር በተጨማሪ ግለሰባዊ ማንነትን ከማህበረሰቡ አመለካከት አኳያ የመቅረፅ እና የማፅናት ፋይዳ ያላቸው መሆኑን እና ከዚህ በተጨማሪም ከበራዎች ከበሽታ የመፈወስ፣ ዘርን የማብዛት፣ ሀጢያትን የማንፃት፣ ማህበራዊ ደረጃን የመለወጥ፣ ረጅም እድሜን የማስገኘት ፋይዳ ያላቸው መሆንን ይጠቅሳል (1972፣ 167)፡፡

ይህንን ሀሳብ እነ Sims "That's one reason rituals are so important to groups and to folklorists: they make intangible values, beliefs and attitudes—which are frequently hidden—concrete and visible." (2005፣ 96) በሚል ገልፀውታል፡፡ እንደ እነ Sims ገለፃ በከበራው ወቅት ከሚኖረው መገለጥ ተጠቃሚ የሚሆነው ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን የፎክሎር ባለ ሙያውም ጭምር ነው፡፡ የከበራን ፋይዳ አስመልክቶ Jin Pire "the role of the ritual was to promote social integration and cohesion." (1990፣ 31) በማለት ከቀደሙት ሁለት ምሁራን የጠቀስነውን ሀሳብ ያጠናክረዋል፡፡

የከበራን ምንነት እና ተግባር የዚህን ያህል ለመመልከት ከሞከርን Bauman ከበራን በምናጠናበት ወቅት ከበራው የት እና እንዴት ተከወነ ? ከበራውን በዋናነት የሚመሩት እነማን ናቸው ? ተሳታፊዎቹ እነማን ናቸው ? የተሳታፊዎቹ ምላሽ ምን ይመስላል ? ከበራውን ለማድመቅ አገልግሎት ላይ የዋሉት የፎክሎር ገፅታዎች እንደምን ያሉ ናቸው ? የታሪኩ መዋቅር ምን ይመስላል ? በከበራው ወቅት የሚከውኑት ነገር በሰርካዊ ህይወታቸው ከሚከውኑት በምን ይለያል ? እንዴት ጀምረው እንዴትስ ነው የሚቋጩት ?. . .ወዘተ (1975፣ 312) የሚሉት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ማተኮር እንዳለብን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱት መሰረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ለመተንተን፤ ከዚህም በላይ ከበራ ካለ አውድ እና ክዋኔ ተሳስረው መገኘታቸው የግድ በመሆኑ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን ለመተንተኛነት መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

"በእርግጥ የለቅሶ ስርዓት ከበራ ነው ?" የሚል ጥያቄ ከተለያዩ ወገኖች ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የተለያዩ ምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደቻልነው "ከበራ በራሱ ጊዜና ቦታ በቀጠሮ የሚከወን ነው"፡፡ በመሆኑም ቀጠሮ ከሌለው (ጊዜ ቆርጦ ከማይመጣው) ሞት ጋር ምን አገናኘው ሊባል ይችላል፡፡ ወደፊት በትንተናው ክፍል በስፋት እንደምንመለከተው የሸካቾ ብሔረሰብ ሞት በማህበሩ ውስጥ ሲከሰት እንዳብዛኞቹ የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ልማድ ሞት የተከሰተ ዕለት፣ ወይም በንጋታው ግፋ ካለም በሰልስት ቀብሮ ሀዘን የሚቀመጥ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሟችን ማንነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የወር፣ የሁለት ወር አሊያም የሦስት ወር ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ነው ቀብሩ የሚፈፀመው፡፡ ይህ እሚሆነውም በዋናነት የብሔረሰቡን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ በብዛት እና በጥራት ለማሰናዳት፣ ዘመድ አዝማድ ሁሉ ለለቅሶው ቀን ከያለበት እስኪሰባበሰብ፣ በቀብሩ እለት የሚቀርቡ ባህላዊ የማፅናኛ ስነ-ስርዓቶች እስኪሰናዱ፣. . .ወዘተ ነው፡፡ በመሆኑም የሸካቾ ብሔረሰብ እንደማንኛውም የሰው ዘር ሁሉ ሞትን በአጋጣሚ የሚጋፈጠው ቢሆንም ሙቱን የሚሰናበተው ባጋጣሚ ሳይሆን ይሁነኝ ብሎ፣ አቅዶበት እና አስቦበት ነው፡፡ ለዚህ ነው "ከበራን" የንድፈ-ሀሳብ ማዕቀፌ ማድረግን የወደድኩት፡፡

#### 2.2.2.2. ከዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ (Performance centered approach)

ይህ ንድፈ ሀሳብ በከበራ ወቅት የሚታዩ መሰረታዊ ጉዳዮችን ነቅሶ በማውጣት በአግባቡ ለመተንተን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያሉት በመሆኑ እያንዳንዱን ነጥቦች በዝርዝር ለመመልከት ይሞከራል፡፡

##### 2.2.2.2.1. የከዋኔ ምንነት እና ባህሪያት

"Performance is in a sense perhaps an element in every action." (Finnegan፣ 1992፣ 86)

ይህ ጥቅስ ከዋኔ የማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ አላባ (መሰረታዊ ነገር) መሆኑን ይነግረናል፡፡ የከዋኔን ምንነት አስመልክቶ እነ Sims ም "ከዋኔ እየተካሄደ መሆኑን ታዳሚያኑ በግልፅ የሚያውቁት መቼት እና ቀመር ያለው ነው" (2005፣ 128) በማለት ከዋኔ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚቀርብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

> performances are aesthetic practices -patterns of behavior, ways of speaking, manners of bodily comportment - whose repetitions situate actors

in time and space, structuring individual and group identities. Insofar as performances are based upon repetitions, whether lines learned, gestures imitated, or discourses reiterated, they are the generic means of tradition making. (Diborah A. Kapchan፣ 1995፣ 379)

ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ረጅም ጥቅስ የምንረዳውም ክዋኔ ተውህቦ ያለው፣ የተቀናጀ፣ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ በድምፅ ቅላፄ እና በአካል እንቅስቃሴ ታጅቦ ተደጋግሞ በመቅረብ የግለሰብን ብሎም የቡድንን ማንነት መገንባት የሚቻለው መሆኑን ነው፡፡ የክዋኔን ምንነት በዚህ መልኩ ከተረዳን በማስከተል ደግሞ ስለ ባህሪያቱ በዝርዝር እንመልከት፡፡

የክዋኔ ባህሪያት የሚባሉት ደግሞ ክዋኔው ምሉዕ እንዲሆን የበኩላቸውን ድርሻ የሚወጡና የማይነጣጠሉ አሀዶች ናቸው፡፡ እነዚህም የክዋኔ አጋጣሚ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ቴክስት፣ አውድ፣ መቼት እና ቅርፅ መሆናቸውን Finnegan (1992፣ 91) Bauman (1975፣ 290)ን ጠቅሳ ክዋኔን መሰረት አድርጎ የሚያጠና የፎክሎር ተመራማሪ ከፍ ያለ ትኩረቱን በእነዚህ ላይ ሊያሳርፍ እንደሚገባው ታስገነዝባለች፡፡ ስለሆነም እንደሚከተለው በዝርዝር እንዲቀርቡ ሆነዋል፡፡

**የክዋኔ አጋጣሚ፡-** ማንኛውም የፎክሎር ዘውግ የሚከወንበትን አንድ አይነት አጋጣሚ የግድ ይፈልጋል፡፡ የክዋኔ አጋጣሚው ጉዳዩ በተገቢው መንገድ ይቀርብ ዘንድ ተገቢውን ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ የክዋኔውን አጠቃላይ ቅርጽ የመከሰት እና የመምራትም ሚና አለው፡፡ ለምሳሌ የሙሾ ግጥም ለመደርደር የለቅሶ ስርዓት ይኖር ዘንድ ግድ ይላል፡፡ ሙሾው በዚህ ጊዜና ሰዓት ተቀናጅቶ የሚቀርብ ሲሆን ሙሾ አውራጁም ሆነ ታዳሚው እውናዊ በሆነ ስሜት ውስጥ ተገኝተው የሀዘን ስሜታቸውን እንዲወጡት ይሆናል፡፡

የክዋኔ አጋጣሚን አስመልክቶ እነ Sims "Many rituals, for example, begin at a predetermined time and place, and an announcement or other signal opens and closes the performance." (2005፣ 128) በማለት ከበራዎች የሚቀርቡት አንድ በውል በሚታወቅ ጊዜ እና ቦታ ውስጥ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ እንደማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ሁሉ በሸካቾ ብሔረሰብም ሞት የሚከሰተው በጋጣሚ ቢሆንም ከበራው የሚከናወነው ግን ታስቦበት እና ታቅዶበት ነው፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የክዋኔ አጋጣሚ ብለን ልንጠራው የምንችለው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚከሰተውን ሞት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

**ከዋኝ፡-** ከዋኝ የአንድ ድርጊት አድራጊ ፈጣሪ ማለት ነው፡፡ ከወነ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "አዘጋጀ፣

አሰናዳ፣ አስጌጠ፣ አሳመረ፣ ፈፀመ፣ ጨረሰ፡፡" (1993፣ 380) ሲል ያብራራዋል፡፡ ይህ የከዋኙን ድርጊት እንዲያመለክት ተደርጎ የተሰናዳው ትርጓሜ አንድ ከዋኝ የቱን ያህል ጉልህ ሚና ያለው መሆኑን ያሳየናል፡፡ በመሆኑም ክዋኔው አምሮ እና ደምቆ አሊያም ፍዝ ሆኖ እንዲቀርብ የማድረጉ ሚና በዋናነት የሚወድቀው እከዋኙ ላይ ነው፡፡ የአከዋወን ሂደቱም በግል፣ በጥንድ እና በቡድን ሊሆን እንደሚችልም በ Finnegan (1992፣ 90) ተጠቅሷል፡፡

የከዋኝን ሚና አስመልክታ Finnegan "performers carry out their role(s): relying mainly on words and gestures, or also exploiting music or dance; purporting to deliver works by others (human or supernatural); creative or otherwise in the sense of composing during or before performance; and so on." (1992፣ 90) በማለት ከዋኝ ምን ማድረግ እንዳለበት ከክዋኔው ቀደም ብሎ ወይም በክዋኔው ሰዓት ለአውዱ የሚስማሙ ነገሮችን በመፍጠር አብዛኛውን ጊዜ ድምፁን እና አካላዊ እንቅስቃሴውን ተጠቅሞ አሊያም በመጨፈር ሚናውን እንደሚወጣ ትገልፃለች፡፡ ከዋኙ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ወቅት ተመራማሪው የከዋኙ እድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ክሂል፣ ድግግሙን እና የሌሎቹን ቀልብ ለመግዛት የሚጠቀምባቸውን ጥበቦች፣. . .ወዘተ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ መሆኑን Finnegan (1992፣ 90) አበክራ ትገልፃለች፡፡

በአንድ የክዋኔ አጋጣሚ ውስጥ የከዋኝ ሚና ከፍ ያለ መሆኑን እነ Sims "The point is that you (as a part of the audience) and the performers created a kind of event together in which you all became part of the others' experience." (2005፣ 127) ሲሉ ይገልፁታል፡፡ በሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ወገኑን አልቅሶ እንዲቀብር እና "ኀሞ" በመጨፈር ሞትን ሊያሳፍር የሚገባው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የለቅሶ ስርዓቱ የደመቀ ይሆን ዘንድ አስለቃሾች የሚመረጡት ሀዘኑ እጅጉን ከጎዳቸው የቤተሰቡ አባላት ሲሆን፣ የ"ኀሞ" ጭፈራውም ያማረ ይሆን ዘንድ ዋንኛ ከዋኞች የሚመረጡት አስቀድሞ የተሸለ ክሂል ያላቸው ተለይተው ነው፡፡

**ታዳሚ፡-** Finnegan "*Audience is really parts of the performance itself*" (1977፣ 216) በማለት ታዳሚ የክዋኔው አካል እና ክዋኔው እንደ ክዋኔ እንዲቀጥል ወሳኝ መሆኑን ትገልፃለች፡፡

በየትኛውም ክዋኔ ውስጥ የታዳምያኑ ሚና ከከዋኙ ባልተናነሰ መጠን እጅጉን ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት ክዋኔውን በማጀብ (እጀባው በድምፅ፣ በጭብጨባ፣ በከበሮ፣ በድልቂያ፣. .

.ሊሆን ይችላል)፣ ከዋኙን በማበረታታት፣ በከዋኔው ላይ ያላቸውን አመለካከት በመግለጽ በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ የከዋኝን ምንነት እና ድርሻ አስመልክቶ Bauman "From the point of view of the oudience, the act of expression on the part of the performer is thus marked as subject to evaluation for the way it is done, for the relative skill and effectiveness of the performer`s display of competence." (1975፣ 293) በማለት ያብራራል፡፡

አንድ ከዋኝ ወደ መድረክ የሚወጣው በዙሪያው ያሉት ታዳሚያኑ በብቃቱ የሚተማመኑበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ከዋኙ ከታዳሚያኑ ጋር ያለው መስተጋብር እንደ አንድ መሰረታዊ የመገምገሚያ ነጥብ የሚወሰድ ነው፤ ታዳሚያኑ ከዋኙ ክዋኔውን በጥሩ ሁኔታ ካስኬደው በአከዋወኑ መደሰታቸውን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ክዋኔውን በማድመቅ፣ በማጨብጨብ፣ በከበሮ በማጀብ፣ በመጨፈር፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ እና በፊት ገጽታ ልውጥውጥ ከዋኙን በማበረታታት፣ በመሸለም፣. . .ወዘተ ለመግለፅ ይሞክራሉ፡፡ በሌላ መልኩም በከዋኙ የአከዋወን ብቃት ደስተኛ ካልሆኑ በክዋኔው ሂደት ከእነሱ የሚጠበቀውን ምላሽ በመንፈግ፣ ከክዋኔው ስፍራ እራሳቸውን በማግለል፣ ጮኸው ክዋኔውን በመረበሽ፣ ሚና በመንጠቅ ወይም ከከዋኙ በመራቅ ሌላ የተሻለ የክዋኔ መድረክ ፈጥረው ተቃውሟቸውን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ የለቅሶ አጋጣሚ ላይ ሙሾ የምታወርድ አንዲት ሴት ብትኖር የድምጿ ቅላፄ የማይስብ ወይም የግጥም አደራደር ስርዓቷ የተፋለሰ ሆኖ ቢገኝ ሰዉ "ምናል እንባ አድርቅ !" ናት በሚል ከአጠገቧ የሚሸሽ የመሆኑን ያህል የድምጿ ቅላፄም ሆነ የግጥም አደራደር ስርዓቷ የሰመረ ሆኖ የተገኘች ሙሾ አውራጅ ስትገጥመው ደግሞ "አስለቀሰችኝ እኮ ጃል !" ሲል አድናቆቱን የሚገልፅ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በአንድ የክዋኔ አጋጣሚ ውስጥ የከዋኝ ሚና እጅጉን ከፍ ያለ ቢሆንም ያለ ታዳሚያን ንቁ ተሳትፎ ግቡን ሊመታ እንደማይችል ልብ ይሏል፡፡

በብሔረሰቡ እምነት መሰረት ማንኛውም ሞት በማህበሩ ውስጥ መከሰቱን የሰማ የብሔረሰቡ አባል በዕለቱ ተገኝቶ የለቅሶ ክዋኔው ታዳሚ ይሆን ዘንድ ባህሉ ግድ ይለዋል፡፡

**"ቴክስት"፡-** እነ Sims ለአብዛኞቻችን "ቴክስት" የሚለው ቃል ቤተኛ የሚሆነው ከፅሁፍ ጋር የተገናኘ ሆኖ ሲቀርብ መሆኑን በመጥቀስ "ቴክስት" የሚለው ቃል ፎክሎራዊ ትርጓሜ ግን የማያካትተው ነገር እንደሌለ ". . .So in its most encompassing sense, *text* can refer to words, objects, ideas, and behaviors." (2005፣ 19) በማለት ይገልፃሉ፡፡ ይህም ማለት በፎክሎር እይታ ስናጤነው እያንዳንዱ ነገር "ቴክስት" ነው ወደሚል ድምዳሜ ያዘልቀናል፡፡

ለምሳሌ የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት የሆነው የለቅሶ ስርዓት ከፎክሎር አኳያ የሚጠኑ በርካታ ነገሮችን አስተሳስሮ የያዘ እንደ መሆኑ መጠን ቴክስት ነው ልንለው እንችላለን፡፡

የለቅሶ ስርዓቱን አጠቃላይ ገፅታ ያየን እንደሆነ በተለያየ አግባብ ሊታይ እና ሊጠና የሚችል "ቴክስት" መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

**አውድ፡-** Ben-Amos አውድ ለፎክሎር መሰረታዊ ነገር መሆኑን የሚገልፀው "Folklore exists in the contextulal state." (1993፣ 209) በማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይኸው የፎክሎር ተመራማሪ አውድ ፎክሎር የሚተረጎምበት ወይም የሚገለፅበት መሰረታዊ ነገር መሆኑን ያስረዳል (1993፣ 212)፡፡ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ በመካሄድ ላይ ያለውን ፎክሎራዊ ክንዋኔ በግልፅ ለመረዳት እና ቁም ነገሩን ጨብጦ በክዋኔው አጋጣሚ ላልተገኘ ሰው ክዋኔውን አስመልክቶ ሙሉ መረጃ ለማስተላለፍ የመከወኛ ስፍራው ምን እንደሚመስል በውል ከመረዳት ጀምሮ ከዋኙም ሆነ ታዳሚያኑ ምን እንደለበሱ፣ በእጃቸው ምን እንደያዙ፣ እግር እና እጃቸው ላይ ምን እንዳጠለቁ፣ እንዴት ይወድቁ ይነሱ እንደነበር፣ ምን አይነት አካላዊ እንቅስቃሴ እንደሚስተዋልባቸው፣ የፊት ገፅታቸው ምን እንደሚመስል፣. . .ወዘተ በአጠቃላይ ክዋኔው የሚቀርብበትን ድባብ በትኩረት ተከታትሎ መመዝገብ መዝግቦ ማስቀረት ይኖርበታል፡፡

ከፍ ሲል የጠቀስነውን ሀሳብ Bauman በአውድ ጥናት ውስጥ መሰረታዊው የፅንሰ ሀሳብ እና የስነ-ዘዴ ማጠንጠኛ ነጥብ በክዋኔው ክስተት ውስጥ የምናገኛቸው መዋቅር እና ተለዋዋጭነት ናቸው፡፡ እነዚህ ቁም ነገሮችም የከዋኙን እና የተሳታፊዎቹን ሚና የማሳወቅ ተግባር አላቸው (1990፣ 70) ሲል ያጠናክረዋል፡፡

እነ Sims በክዋኔ ውስጥ ሁለት አበይት አውዶች መኖራቸውን በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡ እነርሱም ተጨባጭ አውድ እና ማህበራዊ አውድ ናቸው፡፡ ተጨባጭ አውድ የምንለው በክዋኔ ወቅት የሚስተዋለውን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የድምጽ ቅላጼ፣ ዜማ አወጣጥ፣ የፊት ገጽታ መለዋወጥ ...ወዘተ የሚይዝ ሲሆን፤ ማህበራዊው አውድ ደግሞ በክዋኔው ላይ የታደሙትን ተሳታፊዎች ሁለንተናዊና ማህበራዊ ገጽታ ይመለከታል፡፡ እነዚህም የታዳምያኑን ብሔር፣ ኃይማኖት፣ ባህል፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ስራ፣... ወዘተ መሆናቸው (2005፣ 138) ተብራርቷል ፡፡ ይንን ሀሳብ Ben-Amos (1990፣ 77) በሌላ መንገድ ግን ተመሳሳይ ይዘት ባለው አገላለፅ ያጠናክረዋል፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሁለት አውዶች አንፃር የሸካቾ ብሔረሰብን የለቅሶ ስርዓት ስንፈርጀው በሁለቱም አውዶች ውስጥ የሚወድቅ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ማንባቱን፣ ደረት መድቃቱን፣ ፀጉር መንጨቱን፣ ፊት መቧጠጡን፣ መውደቅ መነሳቱን፣. . .ማህበራዊ አውድ በሚለው ስር መመደብ የሚቻል ሲሆን፣ ተጨባጭ አወድ በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ስር ደግሞ በለቅሶው ወቅት በእጅ የሚየዙ፣ በአንገት የሚጠለቁ እና የሚለበሱ፣. . .ጉዳዮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**መቼት፡-** ክዋኔው መቼ እና የት እንደሚከወን የመታወቁ ነገር በክዋኔው ውስጥ አብይ ገጽታ እንደመሆኑ መጠን መቼት ከክዋኔ አይነቶች አንዱ ነው፡፡ Bauman ይህንን ሀሳብ "ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜ የሚታወቅ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ በመሆኑም ክዋኔውን ለመከወን ቅድመ ዝግጅት ይደረግበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክዋኔው መጀመሪያው እና መጨረሻው የሚታወቅ ወይም መነሻ እና መድረሻ ያለው ሊሆን ይገባል" (1992፣ 46) በማለት በክዋኔው ውስጥ ጊዜ እና ቦታ ያላቸውን ጉልህ ሚና ይጠቅሳል፡፡

**ቅርፅ፡-** ማንኛውም የፎክሎር ዘውግ የሚቀርብበት የራሱ የሆነ ቅርፅ አለው፡፡ ይህ ቅርፅ የሚፈጠረው ማህበረሰቡ በወደደው እና በፈቀደው መልኩ ነው፡፡ አንድ የለቅሶ ስርዓት የራሱ የሆነ ቅርፅ ያለው በመሆኑ በምንም አይነት መልኩ በሰርግ ስርዓት ቅርፅ ውስጥ ሊያልፍ (ሊቀርብ) አይችልም፡፡ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በለቅሶ ወቅት ሙቱን አልቅሶ እና አዝኖ ከመሸኘት ውጭ ዘፍኖ እና ጨፍሮ ሊሰናበተው አይፈቅድም፤ በሞቱ የተደሰተ ቢኖር እንኳ ያዘነ መስሎ ለመሰናበት ከመሞከር ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖረውም - አሻፈረኝ ቢል እንኳ ከማህበሩ የመገለል እጣ ይገጥመዋልና፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት የሚያተኩርበት የሸካቾ ብሔረሰብ በለቅሶው ወቅት የሚቀርብ ህብረተሰቡ አምኖ እና ወዶ የተቀበለው የማፅናኛ ዘፈን (ጎሞ) እና ጭፈራ አለው፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ "የጥናቱ አደረጃጀት" ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የሚደራጀው ማህበረሰቡ በቅድመ፣ በጊዜ እና ድህረ ሞት ወቅት ሟችን ለመሰናበት ምን ምን አይነት ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ለማሳየት በሚረዳ መልኩ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገውም አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ቀደም ሲል በተጠቀሱት ቅርፆች ውስጥ የሚያከናውናቸው ልዩ ልዩ ተግባራት ያሉት በመሆኑ ነው፡፡

እነ Sims እያንዳንዱ የፎክሎር ዘውግ የሚከወንበት የራሱ የሆነ ቅርፅ ያለው መሆኑን እና ይህ ቅርፁ የከዋኔውን አጀማመር፣ ሂደት እና አጨራረስ ያመላክታል ሲሉ (2005፣ 95) ላይ ያብራራሉ፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር የቀረቡት ሰባት የከዋኔ ባህሪያት ከዋኔውን ነፍስ እና ስጋ አላብሰውት ወደ ፊት እንዲጓዝ የሚያስችሉት መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች በዚህ ጥናት ግዘፍ ነስተው የሚገኙት ይህ ጥናት በሚያተኩርበት "የለቅሶ ስርዓት" ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በከበራው ወቅት ነፍስ ዘርቶ የሚገኘውን ከዋኔ የትኞቹ ባህሪያቱ እንደምን እንደቀረቡ በትንታኔ ለማሳየት ይሞከራል፡፡ ከበራና ከዋኔ የደም እና ስጋ ያህል የተዋሀዱ መሆናቸውን Rappaport "ከዋኔ ከሌለ ከበራ የለም" (1992፣ 250) በማለት አፅህኖት ሰጥቶ ይገልፃል፡፡ ምክንያቱም ከበራው ያለ ከዋኔ ብቻውን ሊቆም የማይችል ከመሆኑ አንፃር እና የከበራው መልዕክት ሳይሸራረፍ እና ትርጉሙን ሳይለቅ ሊተላለፍ የሚችለው በከበራው በመሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የለቅሶ ስርዓቱን ምክንያት በማድረግ የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ ክንውኖችን በአግባቡ መዝኖ መተንተን ይቻለው ዘንድ ከዋኔ ተኮር አቀራረብን ምርጫው አድርጓል፡፡ በመሆኑም የከዋኔን መሰረታዊ ባህሪያት ከግምት ውስጥ በማስገባት ትንታኔው ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የሸካቾ ብሔረሰብ  አካባቢያዊ እና ማህበረ - ባህላዊ ዳራ

### 3.1. የሸካ ዞን አጠቃላይ ገፅታ፤

የሸካ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚተዳደሩ 13 ዞኖች እና 8 ልዩ ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ዞኑ ከሀገራችን ደቡብ ምዕራብ በኩል ከክልሉ ርዕሰ ከተማ አዋሳ በ951 ኪሎ ሜትር፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ  በ676 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

የሸካ ዞንን በሰሜን የኢሉባቦር ዞን፣ በምስራቅ የከፋ ዞን፣ በምዕራብ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በደቡብ የቤንች ማጂ ዞን ያዋስኑታል፡፡ የሸካ ዞን ማሻ፣ አንድራቻ እና የኪ የተሰኙ ሦስት ወረዳዎችን በውስጡ ያቀፈ ሲሆን 56 የገጠር እና 7 የከተማ ቀበሌዎች እንዲሁም 2 የከተማ አስተዳደሮች ይገኙበታል፡፡  በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን የ1999 ዓ.ም ህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤትና የህዝብ ዕድገት መካከለኛ ግምት መሰረት በ2002 ዓ.ም የዞኑ ህዝብ ብዛት ወንድ 111,136፣ ሴት 108,021 በድምሩ 219,157 እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከዚህም ውስጥ 81.8% በገጠር የሚኖር ሲሆን 18.2%  ደግሞ በከተማ የሚኖር ነው፡፡

የዞኑ የቆዳ ስፋት 238,755 ሄክታር ነው፡፡ ከእዚህ ውስጥ ለእርሻ የዋለ 644,2558 ሄክታር፣ በደን የተሸፈነ 111,192 ሄክታር፣ ሊለማ የሚችል 20,958 ሄክታር፣ ሊለማ የማችል 3,032.42፣ በሌሎች የተያዘ 30760 ሄክታር መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ዞኑ ከ900 - 2700 ከባሀር ጠለል በላይ ከፍታ ሲኖረው የአየር ንብረት ቀጠናዎቹም ደጋ 17.65%፣ ወይና ደጋ 59.85% እና ቆላ 22.58% ናቸው፡፡ የዞኑ አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ1800 - 2200 ሚ.ሊትር ሲደርስ የሙቀት መጠኑ ከ24°C - 29°C እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ (ማ.ስ.ባ. 2000 ዓ.ም)

ዞኑ ከፍተኛ የሆነ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ሀብት ክምችት እንዳለው የባለሙያዎች ጥናት ያስረዳል፡፡ ከ32 በላይ በጋ ከክረምት የማይነጥፉ ትላልቅ ወንዞች ባለቤት፣ በአገራችን ከፍተኛ የሆነ የደን ሽፋን ከሚገኝባቸው አካባቢዎች አንዱ የሸካ ዞን ሲሆን ከዞኑ አጠቃላይ የመሬት ቆዳ ስፋት 23.14% በጥብቅ ደን የተሸፈነ፣ 32% ያህሉ ደግሞ በአዋሳኝ የደን ክፍል የተሸፈነ ነው፡፡ በዞኑ 2 የደጋ ሀይቆች፣ 39 ፏፏቴዎች፣ 14 ዋሻዎች እና 37 ሆራዎች ይገኛሉ፡፡ በዞኑ በዋናነት የሸካቾ፣ የመጃንጊይር እና የሸኮ ብሔረሰቦች የሚኖሩ ሲሆን ሌሎች በርካታ ብሔረሰቦችም በመፈቃቀድ እና በመከባበር አብረው ይኖራሉ፡፡ (ኮቦ፣ ቅፅ 1፣ ቁ. 1፣ 2005 ዓ.ም)

### 3.2. የብሔረሰቡ አመጣጥ ታሪካዊ ዳራ እና ኃይማኖት

የሸካቾ ብሔረሰብ ከ1983 ዓ.ም በፊት በነበረው አስተዳደራዊ መዋቅር "ሞቻ አውራጃ" ተብሎ በሚጠራው ግዛት ውስጥ ይኖር የነበረ ሲሆን በወቅቱ የብሔረሰቡ መጠሪያም "ሞቻ"፣ ቋንቋቸው ደግሞ "ሞችኛ" ይባል ነበር፡፡ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ግን አካባቢው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ስር ከሚተዳደሩ 13 ዞኖች መካከል አንዱ በመሆን የሸካ ዞን ተብሎ ይጠራል፡፡ ህዝቡ "ሸካቾ"፣ ቋንቋው ደግሞ "ሸክኛ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ አምባው ጮሪቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> ሞቻ የሚለው መጠሪያ ለብዙ ዘመናት የህብረተሰቡ መጠሪያ ሆኖ ያገለገለ ቢሆንም ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ግን የአካባቢው ሽማግሌዎች እና ታሪክ አዋቂዎች ተሰብስበው 'ሸካቾ' የሚለው መጠሪያ ይበልጥ ከህብረተሰቡ ማንነት ጋር የተያያዘ ነው በሚል ሊሰጡት ችለዋል፡፡ 'ሸካቾ' ማለት በጥምር ግብርና ህይወቱን የሚመራ፣ ከጓሮው ብዙ ምርት የሚይዝ ጎተራ ያለው፣ እሸት ከጓሮው የማይጠፋ፣. . .የሚለውን ትርጉም የሚይዝ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ መጠሪያ ከቀድሞው ይልቅ ህብረተሰቡ የሚስማማበት ነው፡፡ (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

ከፍ ሲል በአቶ አምባው የተጠቀሰውን ሀሳብ አቶ ኃይሌ መድራሻም "የእኛን ማህበረሰብ 'ሞቻ' ከሚለው ይልቅ 'ሸካቾ' የሚለው መጠሪያ ነው በደንብ የሚገልፀው፡፡ ጥንትም ቢሆን 'ሞቻ' የሚለውን መጠሪያ ብሔረሰቡ ለራሱ የሰጠው ሳይሆን በአጎራባች የሚገኙ ሌሎች ብሔሮች ናቸው ያወጡለት፡፡ ስለሆነም በእኔ እምነት ዛሬ ላይ የብሔረሰቡ ታሪክ አዋቂዎች ተማክረው ያወጡለት 'ሸካቾ' የሚለው መጠሪያ ነው ትክክል፡፡" (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ያጠናክሩታል፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ቋንቋ የሆነው "ሸክኛ" በኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ ስር የሚመደብ ሲሆን ቋንቋው ከከፊኛ እና ከሺናሺኛ ቋንቋዎች ጋር በዘዬ ብቻ ነው የሚለያየው፡፡ የእነዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎችም እርስ በእርሳቸው በየቋንቋቸው ያለ አስተርጓሚ ይግባባሉ፡፡ ይህን ቋንቋ በጥቂቱም ቢሆን መግለፅ ያስፈለገው የለቅሶ ስርዓቱ የሚከወንበት በመሆኑ ነው፡፡

የህዝቡን አመጣጥ ታሪካዊ ዳራ በሚመለከት ብዙም በፅሁፍ ሰፍረው የሚገኙ የታሪክ ማስረጃዎችን ማግኘት ባይቻልም ቃለ- መጠይቅ የተደረገላቸውም ሆነ የተተኳሪ ቡድን ውይይት

አባላት በሙሉ የሚጠቅሱት "የሽካቾ ብሔረሰብ ከእስራኤል የመጣ መሆኑን ነው"፡፡ አቶ ኃይሌ መድራሻ የህብረተሰቡን ጥንተ አመጣጥ እና ኃይማኖት በተመለከተ እንደሚከተለው በሰፊው ያብራራሉ፡፡

> አባቶቻችን የነገሩን የእኛ ህዝብ ከእስራኤል ሀገር የፈለሰ መሆኑን ነው፡፡ አባቶቻችን በእስራኤል ይኖሩ በነበሩበት ወቅት ይደርስባቸው የነበረውን መገለል በመቃወም ከአካባቢው በመሰደድ በግብፅ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገቡ እና ወደ ኢትዮጵያ ከገቡም በኋላ በአባይ ወንዝ ዳርቻ ሰፍረው ይኖሩ እንደነበረ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚያም ሰፍረው የነበሩበት አካባቢ የአየር ንብረቱ ብዙም ስላልተስማማቸው በሊሙ አድርገው ዛሬ ሰፍረው ወደሚገኙበት አካባቢ መምጣታቸውን ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ወቅት ከእነሱ መካከል ተነጥለው የቀሩት 80 ሰዎች (ሺና አሾ) በአሁኑ ሰዓት በቤንሻንጉል ጉምዝ ውስጥ የ"ሽናሻ" ብሔረሰብ በሚል የሚጠሩ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ አባቶቻችን ከእስራኤል መምጣታቸውን አስመልክቶ ከሚያቀርቡልን ማስረጃዎች መካከል የመጀመሪያው የሽካቾ ብሔረሰብ በሙሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ መሆኑን እና 40 ፅላቶችን ከእስራኤል ሀገር ይዞ መምጣቱን ነው፡፡ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግራኝ መሐመድ ወረራ ድረስ ሁሉም የህብረተሰቡ አካል ከእስራኤል ይዞ የመጣውን ታቦታት በየአካባቢው ቤተ-ክርስቲያን ሰርቶ በማቆም የሚፆም፣ የሚፀልይ፣ በስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን የሚመራ፣. . . ወዘተ ነበረ፡፡ ነገር ግን የግራኝ መሐመድ ወረራ ተፋፍሞ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ቤተ-ክርስቲያኖችን፣ ፅላቶችን እና የክርስትና እምነት ተከታዮችን ማውደም መጀመሩን አባቶች ሲሰሙ በየአካባቢው የገነቧቸውን ቤተ-ክርስቲያናት በማፍረስ በውስጣቸው የነበሩ ፅላቶችን እና ንዋየ ቅድሳትን 16 ቱን ፅላቶች አንድ ቦታ፣ 13ቱን ደግሞ ሌላ ቦታ በመቅበር እና ድንገት የቀበሯቸውን አግኝቶ የሚያቃጥልባቸው ከሆነ ደግሞ ያለ አንድ ፅላት እንዳይቀሩ በመስጋት አንዷን ፅላት ከእነሱ በፊት አቃጥሎ ወደ ነበረው የከፋ ግዛት በድብቅ በመውሰድ ለወቅቱ የከፋ ንጉስ አደራ በመስጠት ፅላቶቻቸውን ሁሉ ከመቃጠል እንደታደጓቸው ይናገራሉ፡፡ 39ም ፅላቶች የተቀበሩበትን የሚያውቁ እና ለከፋ በአደራ መሰጠቱን በተዋረድ እየሰሙ የመጡ አዛውንቶች ቢኖሩም ዛሬም ድረስ ሁሉም ከያሉበት ወጥተው ለህብረተሰቡ ግልጋሎት በመስጠት ላይ አይደሉም፡፡ ይህን ተከትሎም ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ የተወሰነው የህብረተሰቡ ክፍል በአካባቢው በሚገኙ ቃልቻዎች

ማምለክ ጀመረ፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬም ድረስ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው፡፡ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ መካከል አንዱ የሆኑት አቶ ስለሺ ጫሊቶ "የጎንጋ ህዝቦች ታሪካዊ አመጣጥ" ሲሉ እያዘጋጁ ባሉት ያልታተመ ፅሁፍ ውስጥ ከፍ ሲል በአቶ ኃይሌ በዝርዝር የቀረበውን ሀሳብ እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፡፡

> የጎንጋ ህዝቦች የሚባሉት ከ14 ኛው መቶ ክ.ዘመን እስከ 19 መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ድረስ የራሳቸው የሆነ አስታዳደራዊ መዋቅር የነበራቸው ነገር ግን የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑት "የሂናሮ መንግስት"፣ "የከፋ መንግስት"፣ "የሸካ መንግስት"፣ "የቦሾ/ጎሮ መንግስት" እና "የአንፊሎ ቡሻሼ መንግስት" የተሰኙት ናቸው፡፡ የእነዚህ ህዝቦች ግንድ ከእስራኤል ሲሆን በጥንት ጊዜ በእስራኤላዊያን ላይ ይደርስ የነበረውን ግፍ እና በደል በመሸሽ በወቅቱ ሰላም ወደ ነበረችው ጥንታዊት ግብፅ በመሰደድ ልዩ ስሙ አሌክሳንደሪያ በሚባል አካባቢ ሰፍረው ይኖሩ ነበር፡፡ የተወሰነ ጊዜ በዚህ አካባቢ ሰፍረው ከቆዩ በኋላ በአካባቢው በተፈጠረው ርሀብ እና ብጥብጥ ሳቢያ አካባቢውን ለቆ የአባይን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ምዕራብ ጎጃም ወንበራ አካባቢ ሰፍረው ይኖሩ እንደነበር እና ኋላ ላይ ዛሬ ወደሚገኙበት ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ሰፍረው መኖር እንደጀመሩ የአፈ ታሪክ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ (ያልታተመ፣ ከገፅ 1-2)

ከአቶ ኃይሌ ሀሳብም ሆነ ከስለሺ ያልታተመ ፅሁፍ በሰፊው የምንረዳው "የሸካቾ ብሔረሰብ" ከሌሎች ወንድሞቹ፤ በተለይም ከከፋ እና ከሺናሻ ብሔረሰቦች ጋር በታሪክ አጋጣሚ ከእስራኤል ተነስቶ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት አሁን የሚገኝባቸው ስፍራዎች ላይ መኖር መጀመሩን ነው፡፡ ይህ ሀሳብ ምንም እንኳ ሰፋ ያለ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል አምኖ የተቀበለው "ታሪኩ" መሆኑን ከሁሉም መረጃ አቀባዮች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 3.3. የብሔረሰቡ ኢኮኖሚ መሰረት

ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የሸካቾ ብሔረሰብ ዋንኛ መተዳደሪያው ጥምር ግብርና ነው፡፡ አካባቢው ቆጮ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ቀይ ጤፍ፣ ድንች እና ጥቅል ጎመን በስፋት ይመረትበታል፡፡ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ከሚያከናውነው የእርሻ ስራ ጎን ለጎን

የንብ ማነብ ስራውን በሰፊው የሚሰራ በመሆኑ  ከዓመት እስከ ዓመት የማይነጥፍ ነጭ ማር በአካባቢው ይገኛል፡፡

በዞኑ የጋማ እና የቀንድ ከብቶች በስፋት የሚገኙ ሲሆን አካባቢው ለቡና፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ቅመማ ቅመም ምርቶች በእጅጉ የተመቸ ነው፡፡ (ኮቦ፣ ቅፅ 1፣ ቁ. 1፣ 2005 ዓ.ም)

ኢኮኖሚያዊ መሰረቱን በአጭሩም ቢሆን መጥቀስ ያስፈለገው የሸካቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ላይ ለለቀስተኞች የሚሆን በርከት ያለ ምግብ እና መጠጥ የሚቀርብ በመሆኑ በጥቂቱም ቢሆን ተያያዥነት አለው ከሚል እምነት ነው፡፡

### 3.4. የብሔረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር

የሸካቾ ብሔረሰብ የራሱ በሆነ የንግስና ስርዓት እና አስተዳደራዊ መዋቅር ይተዳደር የነበረ ነው፡፡ ቀዳሚው የሸካቾ ንጉስ (ንጉስ በሸከኛ ታቶ ይባላል) "ጋሆቺ"  ሲሆኑ ተጠሪነታቸው ለንጉሱ ሆኖ የራሳቸው የሆነ አስተዳደራዊ መዋቅር እና ስልጣን ያላቸው ከትራሻ [3]፣ ወላሻ [4] ፣ ፋራሻ [5] ፣ አካክራሻ [6] ፣ ጪተራሻ [7] ፣. . .ወዘተ የተሰኙ የስልጣን እርከኖች አሉ፡፡ እነዚህ ባለ ስልጣናት በብሔረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን አበሎ፣ አተሶ፣ አዶ፣ ቡሻሾ፣ አደሎ፣ ሚጀ፣ ባቶ፣ ከጮ፣ ደመዎ፣ ሁማቾ፣ አባኮ፣ ሸውነአ፣ ፋአ፣ ኪጦ፣ ዳቦ፣ ኒበዎ፣ ኒጦ፣ አካኮ፣ ሾዶ፣ ሺአ፣ ጋቲሞ፣ ጉቶ፣ ጉቾ፣ ሂኒውሶ፣ ሂኒበሮ፣ ዋሆ፣ ማሶ፣ ሂኒማዎ፣ ፈሎ፣ የሀሎ፣ ሺሮ፣ ፈጥሮ፣ አውሶ፣ ዮፎ፣ ጫጎ፣ መንጆ፣ ማነቾ፣ ሜቾ፣ ሚጆቾ፣ ገላሞ፣ ሺሾ፣ ወሎ[8]፣ አዲሞ፣ አሲአ፣ ሺቦ፣. . . .ወዘተ የተሰኙ ከ50 በላይ የሚሆኑ የጎሳ አባላትን በክፍፍል የሚያስተዳድሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የአስተዳደር አካላት

---

[3] . "ከትራሻ" ተጠሪነቱ ለንጉሱ ሆኖ ከንጉሱ በመጣ ትዕዛዝ ወይም በተገኘ ፈቃድ ሌሎች የምክር ቤቱን አባላት ሰብስቦ የሚያወያይ የጠቅላይ ሚኒስቴርነት ማዕረግ ያለው ባህላዊ ስልጣን፡፡

[4] . "ወላሻ" ተጠሪነቱ ለከትራሻ ሲሆን ስልጣኑም በአካባቢው ሰላም እና ደህንነት ማስጠበቅ ነው፤ የጦሪ መሪ እንደማለት፡፡

[5] . "ፋራሻ" ተጠሪነቱ ለከትራሻ ሆኖ ከንጉሱ እና ከከትራሻ የሚቀርቡ የመወያያ አጀንዳዎችን በፅሞና አድምጦ ለቤቱ በቃል የሚያቀርብ ነው፤ አፈ ጉባኤ የሚለውን ይተካ ይሆናል፡፡

[6] . "አካክራሻ" የምክር ቤቱ አባል፡፡

[7] . "ጪተራሻ" የምክር ቤቱ አባል፡፡

[8] . "ወሎ" የሸካቾ ብሔረሰብ አንድ ጎሳ ሲሆን ከአማራው ብሔር የሚመደበው የ"ወሎ"ን ጎሳ የሚመለከት አይደለም፡፡

የማስተዳደር ተግባራቸውን የሚወጡት ለአገዛዝ ይመቻቸው ዘንድ ተጠሪነታቸው ለእነርሱ የሆነ ከያንዳንዱ ጎሳ በልዩ ልዩ ዘርፎች ኃላፊዎችን በመሰየም ነበር፡፡

ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሩን በጥቂቱም ቢሆን መጥቀስ ያስፈለገውበሸካቾ ብሔረሰብ ለእነዚ አካላት የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት "ለተራው" ህዝብ ከሚደረገው በተወሰነ መልኩ የሚለያይ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.5. የብሔረሰቡ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት

ሰርግ በሸከኛ "ጋሮ" የሚባል ሲሆን ብሔረሰቡ ሰባት የጋብቻ አፈፃፀም አይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም "ማኮ" (በቤተሰብ ምርጫ የሚፈፀም ጋብቻ)፣ "ኤችዮ" (በሁለቱ ተጋቢዎች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጋብቻ)፣ "ሾሶ" (የጠለፋ ጋብቻ) ይህ የጋብቻ ስርዓት በሁለት የሚከፈል ነው፤ "ሾቶ" ከመንገድ አስገድዶ መጥለፍ ሲሆን፣ "ጋፖ" ደግሞ የራስን እጮኛ በውግዝ መያዝን የሚመለከት ነው፡፡ ሌሎቹ የጋብቻ አይነቶች "ፉሶ" (የማባበል ጋብቻ)፣ "የቾ" (የውርስ ጋብቻ)፣ "ሽፖ" (ልጅህን ለልጄ በመባባል የሚፈጠር ጋብቻ) እና "ኢሞ" (የስጦታ ጋብቻ) የተሰኙት መሆናቸውን ወ/ሮ በላይነሽ አርጀፎ (ቃ.መ. 26/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ) እና አቶ ኃይሌ መድራሻ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) ያስረዳሉ፡፡

"ማኮ" የወንዱ ቤተሰብ አይተው ለልጃቸው የፈቀዷትን ልጅ ማንኛውንም ባህላዊ ስርዓት አልፈው የልጃቸው ሚስት እንድትሆን የሚያደርጉበትን ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ይሆን ዘንድ የልጁ ቤተሰቦች በአካባቢው ተቀባይነት ያላቸውን ሦስት ሽማግሌዎች መርጠው በመላክ አስፈላጊው ማጣራት እና ስነ-ስርዓት ታልፎ የሚፈፀም የጋብቻ ስነ-ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ሂደት የሴቷ ወገኖች ልጃቸውን ለትዳር የፈለገውን ወጣት እና ቤተሰቦች ማንነት፣ በጎሳ ወይም በሌላ በማንኛውም አይነት መንገድ የደም ትስስር አለመኖሩን በማጣራት ከተደጋጋሚ ደጅ ማስጠናት በኋላ የሚፈፀም የጋብቻ ስነ-ስርዓት ነው፡፡

"ኤችዮ" ይህ የጋብቻ አይነት በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚፈፀም ነው፡፡ አንድ ወንድ የወደዳትን ሴት አብዛኛውን ጊዜ ጎረቤቷ ከሆነች ጓደኛዋ ጋር በመሆን ከሚኖሩበት ቦታ በመሰወር ከፍቅረኛዋ ጋር ቀድመው ወደተነጋገሩበት አካባቢ በመኮብለል ለተወሰነ ጊዜ ተሰውረው ከቆዩ በኋላ በወንድ ወገን ቤተሰቦች አመቻችነት ለሴቷ ወገን ቤተሰቦች ሽማግሌ ተልኮ እርቅ በመፈፀም ጥሎሽ ከብት እና መደገሻ በመስጠት በመልስ ስነ-ስርዓት የሚፈፀም የጋብቻ ስነ-ስርዓት ነው፡፡

"ሾሶ" ጠለፋ ማለት ሲሆን በሸካቾ ብሔረሰብ ዘንድ በሁለት አይነት መልኩ የሚፈፀም ነው፡፡ አንደኛው "ጋፖ" ሲሆን አንድ ወንድ ላጫት ሴት ቤተሰቦች የሚከፍለው ጥሎሽ በማጣቱ ሳቢያ እጮኛውን በወቅቱ ሳያገባት ይቆይና በአንድ አሳቻ ወቅት ቤተሰቦቿ በአካባቢው ያለሞኖራቸውን አረጋግጦ እጮኛውን ወደቤቱ በማስገባት ትዳር የሚመሰረትበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ወንዱ ሴቷን ይዞ በሚጓዝበት ወቅት የአካባቢው ሰዎች ወይም ዘመዶቿ ደርሰው ሊያስጥሉ ቢሞክሩ "በፈጠራችሁ ማንም እንዳይነካኝ፣ የገዛ እጮኛዬን ነው እየወሰድኩ ያለሁት" በማለት ይማፀናል፤ በመሆኑም በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ማንም ሰው ተማፅኖውን ጥሶ ሰውየውን መንካት የተወገዘ በመሆኑ እጮኛውን በሰላም ይዞ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ ከዚህ በኋላ ሽማግሌዎች ተመርጠው ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ይላኩና ቅሬታው ተፈቶ ተጋቢዎቹ በሰላም እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ በሸካቾዎች ባህል ጋብቻ በዚህ አይነት መልኩ እንዲፈፀም መፈቀዱ አንድ ሰው በአቅም ማነስ የተነሳ የሚፈልጋትን ሳያገባ እንዳይቀር ከሚል አመለካከት የመነጨ ሲሆን አሁን አሁን ግን ሰዎች "ጥሎሽ የሚከፍለው ገንዘብ አጣ" መባልን ስለማይፈልጉ በዚህ መልክ የሚፈፀም ጋብቻ እየቀረ መጥቷል፡፡

ሌላኛው በጠለፋ የሚፈፀም የጋብቻ አይነት "ሾቶ" ነው፡፡ ይህ የጋብቻ አይነት አንድ ወንድ የወደዳትን ሴት ጓደኞቹን አስተባብሮ ጠልፎ የሚያገባበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ በሸካቾዎች ዘንድ የጠለፋ ጋብቻ ሰፋ ያለ ውዝግብ እና ጭቅጭቅን በሴቷ እና በወንዱ ቤተሰቦች መካከል የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ጠላፊውን ከፍ ላለ ቅጣት የሚዳርግ በመሆኑ አብዛኞቹ የማህበረሰቡ አባላት ጋብቻቸው በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፍ አይፈቅዱም፡፡

"ፋሶ" የማባበል ጋብቻ ማለት ሲሆን አንድ ወንድ የወደዳትን ሴት እሷን በሚቀርቡ አካላት አማካኝነት አግባብቶ የሚያገባበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ልጅቷን የሚቀርቡ ተብለው የተመረጡት አካላት በተደጋጋሚ ስለልጁ መልካም ገፅታዎች በተለያየ መንገድ በመንገር የልጅቷ ቀልብ ልጁ ላይ እንዲያርፍ ካደረጉ በኋላ ሊያገባት ከሚፈልጋት ልጅ ጋር በቀጥሮ ያስተዋውቋታል፡፡ በዚህ መልክ የተጀመረው ቅርርብ ለጋብቻ እንዲበቃ ይሆናል፡፡

"የቾ" አንድ ሰው የሚች ወንድሙን ወይም ዘመዱን ሚስት በውርስ የሚያገባበትን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ጋብቻ ዋንኛ ዓላማው የሟች ልጆች በባዕዳን እጅ ወድቀው መጎሳቆል እንዳይደርስባቸው እና የሟች ሀብት እና ንብረት ባክኖ እንዳይቀር በሚል እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በባህሉ መሰረት ሟች ወንድም ኖሮት ሌላ ጋብቻ ያለው ቢሆን እንኳ በተጨማሪነት የሟች ወንድሙን ሚስት እንዲያገባ ይገደዳል፡፡

"ሽፖ" ምንም አይነት የደም ትስስር የሌላቸው ሁለት ጓደኞሞች ያላቸውን መቀራረብ ይበልጥ በጋብቻ ማጠንከር ሲፈልጉ ልጅህን ለልጄ በተባባሉት መሰረት የሚፈፀመውን የጋብቻ ስነ-ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡

"ኢሞ" የስጦታ ጋብቻ ማለት ሲሆን ይህ የጋብቻ አይነት ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የጋብቻ ስርዓት ጋር የሚመሳሰልባቸው ነጥቦች ቢኖሩትም ይህኛው የጋብቻ አይነት በአንደኛው አካል ፍቃድ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚጀመር ነው፡፡ አንድ ሰው በምግባሩ አሊያም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ከሌላኛው ሰው ጋር መዛመድ በሚፈልግበት ወቅት "ልጄን ለልጁ" ሰጥቻለሁ ሲል ለአካባቢው ሽማግሌዎች ይገልፃል፡፡ ይህን የሰሙት ሽማግሌዎም ቃል ለተገባለት ልጅ አባት ስለሁኔታው በማስረዳት በሂደት ጋብቻው እንዲፈፀም የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡

በአጠቃላይ በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት ቀደም ሲል የተጠቀሱት የጋብቻ አይነቶች በዋናነት ሊፈፀሙ የሚችሉት ተጋቢዎች የአንድ ጎሳ አባል ያልሆኑ እንደሆነ ብቻ ነው፤ ዛሬም ድረስ ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ከጎሳው አባል እንዲያገባ አይፈቀድለትም፡፡ ምክንያቱም የአንድ ጎሳ አባል ማለት የአንድ እናት እና አባት ልጆች ተደርገው የሚቆጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡

ሰርግን አስመልክቶ የተወሰነ ዳሰሳ ማድረግ የተፈለገው "ሰርግና ሞት አንድ ነው" እንዲሉ ለሰርግ ስነ-ስርዓቱ የሚሰጠውን ትኩረት መመልከት ለለቅሶ ስነ-ስርዓቱ የሚኖረውን አመለካከት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሊያሳይ ይችላል ከሚል እምነት በመነጨ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተና

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ አቢይ ጉዳይ የሆነው "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ከተለያዩ ገፅታዎች አንፃር ተተንትኖ ይቀርባል፡፡ ትንተናው የሚካሔደው ከቃለ-መጠይቅ፣ ከምልከታ እና ከተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

### 4.1. የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ

"የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ" ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያሉት እና ማህበረሰቡ ከየትኛውም ባህላዊ ክዋኔዎቹ ይልቅ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አቶ ኃይሌ መድራሻ እንደሚከተለው በስፋት ያብራሩታል፡፡

*እንደ እኛ ማህበረሰብ እምነት አንድ ሰው ሲሞት ሟቹን ወይም የሟቹን ቤተሰብ የሚያውቅ ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል በአካባቢ በመገኘት አልቅሶ የመቅበር ማህበራዊ ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም በተለያየ አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰቡ አባላት በማህበሩ ውስጥ ሞት መከሰቱን ሊሰሙ የሚችሉባቸውን የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም መልዕክት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡ መልዕክቱ የደረሰው ላልደረሰው በማዳረስ ቀብሩ እንዲፈፀም በተቆረጠለት ቀን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከገጠመው የብሔረሰቡ አባል ውጭ ያሉት በቦታው ተገኝተው የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊ ግዴታ ይወጣሉ፡፡ በመሆኑም አንዳንድ ሰዎች ተቀባይነት በሌላቸው ምክንያቶች አሳበው የሟችን ቤተሰብ ቀርበው ያላፅናኑ እንደሆነ አብዛኛው የህብረተሰቡ አባላት ያገሏቸዋል፤ የደስታቸውም ይሁን የኃዘናቸው ተካፋይ ቁጥር ይቀንሳል፡፡ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)*

ከፍ ሲል በአቶ ኃይሌ በረጅሙ የተሰነዘረውን ሀሳብ ወ/ሮ ዘውዲቱ አንገሎም በተመሳሳይ ሁኔታ ነገር ግን በተለየ አገላለፅ ያጠናክሩታል፡፡ ወ/ሮ ዘውዲቱ መገለሉ በምን በምን ተግባራዊ እንደሚሆን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ወንድየው እርሻ ለማረስ የሚያቀናጀው በሬ ቢፈልግ ለቅሶ አለመድረሱን የሚያውቁ የአካባቢው ሰዎች አያውሱትም፣ ለቀፎ መስቀያ የሚሆን ገመድም ማንም አይሰጠውም፣ በአካባቢው በሚኖሩ የህብረት ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆን አይጋበዝም፣. . .ወዘተ፡፡ ሴቷን

በተመለከተም ማንም ሰው ቆጮ አያፋፍቃትም፣ ለቆጮ የሚሆን እርሾ (ኤኮ) ማንም አይሰጣትም፣ ቡና/ጨሞ እንድትጠጣ አትጋበዝም፣ ሴቶች ተሰባስበው የሚወጡት ማህበራዊ ግዴታዎች በሚኖሩ ጊዜ ተካፋይ እንድትሆን አይደረግም፣. . .ወዘተ፡፡ (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ)

ከፍ ሲል የጠቀስኳቸው መረጃ አቀባዬ መገለሉ እስከምን ድረስ እንደሚቀጥል እና ይቅር የሚባለው መቼ እንደሆነም "አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ለቅሶ ሳይደርስ ቀርቶ የደረሰበትን መገለል ይቅር ሊባል የሚችለው በአካባቢው ባሉ ታዋቂ ሽማግሌዎች ፊት ቀርቦ የሰራው ነገር ጥፋት መሆኑንና በስራውም መፀፀቱን በሚገባ አምኖ የሟችን ቤተሰቦች አቅሙ በፈቀደ ልክ አርዶ በማብላት ሲክስ ብቻ ነው፡፡" (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ) በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ለቅሶ መቅረት የሚያስከትለውን ጣጣ በውል ስለሚያውቅ ያለበቂ ምክንያት ከለቅሶ አይቀርም፡፡ ስለሆነም የሸካቾ ብሔረሰብ አባላት ከሰርግና ከልዩ ልዩ በዓላት ይበልጥ ቀጠሮ ተይዞለት በሚፈፀም ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ወቅት ከወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር በስፋት ይገናኛሉ፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን (በሸክኛ "ሼኪ ኤፎ" ይባላል) ማህበረሰቡ ከሚያስቀምጣቸው የልዩነት ነጥቦች አንፃር ከፋፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ እንደ ተተኳሪ ቡድን ተወያዮቼ እምነት ከሌሎቹ የብሔረሰቡ አባላት የተለየ የሚባለው የለቅሶ ስርዓት የሚፈፀመው ጥርስ ሳያበቅሉ በሞት ለሚነጠቁ ህፃናት የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ለንጉስ፣ ለጎሳ መሪዎች እና ለቃልቻዎች የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት አንድ ባለፀጋ ሲሞት በሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ላይ የተወሰነ የሚጨምረው ነገር ቢኖረውም አብዛኛው ገፅታው ተመሳሳይ ነው፡፡ እንዲሁም ከፆታ አንፃር ለሴቶቹም ሆነ ለወንዶች የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት አብዛኛው ገፅታው ተመሳሳይ ሆኖ በተወሰኑ ክዋኔዎች ላይ ግን ልዩነት ይስተዋልበታል፡፡ ለእያንዳንዱ አካላት የሚደረገው ለቅሶ እንዲደምቅ አሊያም እንዲደበዝዝ ዋንኛውን ሚና የሚጫወተው ሟች ወይም የሟች ቤተሰቦች ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም መሆኑንም ተወያዮቹ አያይዘው ይጠቅሳሉ፡፡ (የተ.ቡ. ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በመሆኑም የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት የአከዋወን ሂደት "ለህፃናት የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት" እና "ለአዋቀቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ሁለት አበይት ጎራ ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ሲሆን የአዋቂዎችን የለቅሶ ስርዓት ለመግለፅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከፍ ሲል የተጠቀሱ ልዩነቶችን እንደሚከሰቱበት አግባብ ይገለፃሉ፡፡

#### 4.1.1. ለህፃናት የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት

በሸካቾ ብሔረሰብ ልጅ ሲወለድ የሚኖረው ደስታ እና ፈንጠዚያ ከፍ ያለ ነው፤ በተለይም የተወለደው ወንድ ከሆነ አባት ከማንም በላይ ደስ ይለዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ አምባው ጮሪቶ "አባት ወንድ ልጅ ሲወለድለት 'ወራሼን አገኘሁ፣ ጦሬን የሚይዝ ተወለደልኝ' እያለ ደስታውን ይገልፃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወንድ የወለደለችለትን ባለቤቱን ከወትሮውም በተለየ ላቅ ያለ እንክብካቤ ያደርግላታል፡፡ የተወለደችው ሴት ከሆነች ደግሞ ይበልጥ የምትደሰተው እናት ነች፡፡ ምክንያቱም የቤት ውስጡን ስራ የምታግዛት ረዳት በማግኘቷ ነው፡፡" (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ በደስታ የተቀበሏቸው የአብራካቸውን ክፋዮች በአንዳች ምክንያት በሞት ከተነጠቁ ሀዘናቸውን የሚገልፁበት መንገድ ከአዋቂዎቹ የተለየ ነው፡፡

የተወለደው ልጅ የሞተው ጥርስ ሳያበቅል ከሆነ ነፍሱ ባለፈችበት ቅፅበት ቤተሰብ እና ጎረቤት ብቻ እርምን ለማውጣት ያህል ብዙም ከፍ ባላለ ድምፅ አልቅሰው ሟችን ይሰናበታሉ፡፡ የቀብር ስርዓቱም በሌላው የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች ፈፅሞ ይለያል፡፡ ሟች እየተውተረተረም ቢሆን ከቤተሰቡ አልፎ ለጎረቤት መላላክ፣ በግና ፍየሎችን ማሰማራት፣ ከብት መንዳት፣ ቀንበር መሸከም፣. . .ወዘተ በአጠቃላይ ለአቅመ አዳም/ ሔዋን እየደረሰ ባለበት ወቅት ከሆነ የሞተው በቤተሰቡም ሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እጅግ መረር ያለ ለቅሶ ነው እሚሆነው ሲሉ አቶ አምባው ያስረዳሉ (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)፡፡

ወ/ሮ በላይነሽ አርጀፎ የቀደመውን ሀሳብ "እናት ልጇ ጥርስ ሳያበቅል ከሞተባት የሚሰማት ሀዘን ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ ልጇን የሰጣትን ፈጣሪ አስቀይማ ቀጣይ ልጅ እንዳይከለክላት ስትል የሆዷን በሆዷ ውጣ ትንሽ አልቅሳ ነው ዝም የምትለው፡፡" (ቃ.መ. 26/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ያጠነክሩታል፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሁለት የህፃናት ሞት ውስጥ እዚህ ትኩረት ሰጥቶ ማቅረብ የተፈለገው ማህበረሰቡ ጥርስ ሳያበቅል ለሞተ ህፃን የሚያከናውነውን የለቅሶ ስርዓት የተመለከተ ነው፡፡ ይህም እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት አስቀድሞ ለመጠቆም እንደተሞከረው በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ (ከ0 እስከ 1 ዓመት) ያለ አንድ ህፃን ሲሞት በሌሎች የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚሆነው የለቅሶ ስርዓት የተለየ በመሆኑ ነው፡፡ ለአቅመ አዳም/ ሔዋን በመድረስ ላይ እያለ ለሞተ ወጣት የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት በዝርዝር ለማቅረብ ያልተፈለገበት ምክንያት ስርዓቱ

በሌሎቹ የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ከሚከወነው ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል በመሆኑ ነው፡፡ ይልቁንም የትልልቆቹ ለቅሶ ከወጣቶቹ ለቅሶ የሚጨምረው ያለ በመሆኑ አንዱን በሌላው ውስጥ ማሳየት ይቻላል በሚል እምነት ነው፡፡ ስለሆነም ጥርስ ሳያበቅሉ ለሞቱት ህፃናት  ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚከወኑ ስርዓቶችን ቀጥለን እንመልከት፡፡

#### 4.1.1.1. ቅድመ ቀብር ክዋኔ

አንድ ህፃን የእናቱን ጡት እየጠባ፣ ከእናቱ እቅፍ ሳይወርድ በተለየያ ምክንያቶች ቢሞት በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት ቀብሩ የሚፈፀመው መሬት ውስጥ ሳይሆን በዛፍ ላይ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትን ምክንያት አቶ ኃይሌ ሲገልፁ "እንደ ብሔረሰቡ እምነት ጥርስ ሳያበቅል የሞተው ህፃን ልጅ መሬት ውስጥ ከተቀበረ እናትየው ዳግም አትወልድም ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ነው፡፡" (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሆነ አንድ ህፃን ልጅ ሲሞት ቀብሩ ከመፈፀሙ በፊት የሚከናወኑ ባህላዊ ስርዓቶች አሉ፡፡

ህፃን ልጃቸውን በሞት የተነጠቁት ሴት ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች በጋራ በመሆን በለሆሳስ አጠር ያለ ለቅሶ በማልቀስ እርማቸውን ያወጣሉ፡፡ ከዚህን በኋላ ከቤተሰቡ ወይም ከጎረቤቱ መካከል በዕድሜ ጠና ያሉ አዛውንቶች ወደ አልቃሾቹ በመጠጋት "ማልቀስ ተገቢ አለመሆኑን፣ ፈጣሪን ማስቀየም እንደሆነ" በመግለፅ ከለቅሶው እንዲታቀቡ ይገስጿቸዋል፡፡ ልጇ የሞተባትንም ሴት ነጠል በማድረግ ካፅናኗት በኋላ መሀል አናቷን ቅቤ በመቀባት "ፈጣሪ ከዚህ የተሻለ፤ የሚያድግ ልጅ" በቅርብ እንደሚሰጣት በማግባባት የለቅሶው ፍፃሜ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ በኋላ የሚከናወነውን ባህላዊ ስነ-ስርዓት የውይይቱ አባላት እንደሚከተለው በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡  ህፃኑ የሞተው ጀንበር ከመጥለቋ ቀደም ብሎ ከሆነ በአካባቢው ካሉ ወንዶች ጠንከር ያሉት እና ልምዱ ያላቸው ተለይተው ለቀብር ይሆናል ተብሎ የተመረጠውን ከሰፈሩ ወጣ ብሎ የሚገኘን ዛፍ ለመቦርቦር የሚያስችሉ እንደ ገጀራ፣ መጥረቢያ፣ ፋስ እና ገሶ የመሳሰሉ መሳሪያዎችን በመያዝ በፍጥነት እቦታው ደርሰው ሰው እና አውሬ በቀላሉ ሊደርስ ከማይችልበት ስፍራ ላይ በመሰላል በመውጣት ዛፉን የሳጥን ቅርፅ አስይዘው ይቦረቡራሉ፡፡ የሚመረጠው ዛፍ ቢያንስ የሁለት ሰው እቅፍ የሚሞላ፣ በንፋስ ይወድቃል ተብሎ የማይገመት እና በቀላሉ መቦርቦር የሚችል  "ከረሾ" ወይም ዋንዛ የሚባል ዛፍ ነው፡፡ በመሆኑም የመቃብሩን ስፍራ ሊያዘጋጁ ከመጡት ሰዎች ግማሹ እንጨቱን ሲቦረቡር ሌላው ደግሞ የተቦረቦረውን

በአግባቡ መክደን የሚችል እንጨት ጠርቦ የማዘጋጀት ስራ ላይ ይጠመዳሉ፡፡ ይህ የህፃናት አስክሬን የሚያርፍበት ቦታ በብሔረሰቡ "ዋኪኔ ቆጦ" (የሬሳ ማረፊያ) ይባላል፡፡ ከ1፡00 እስከ 1፡30 ሰዓት የሚፈጀው ስራ ወደመጠናቀቁ ሲቃረብ የማጣሪያውን ስራ ከሚሰሩ የተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ሌሎች ወደ ሰፈር ተመልሰው ሟቹን አጥበው በመገነዝ እና ጊቢውን በማፅዳት ላይ ለነበሩት ሰዎች የስራውን መጠናቀቅ ያስረዳሉ፡፡ ሟች ወንድ ከሆነ አባትየው ሴት ከሆነች ደግሞ እናትየው አጥበው ልምዱ ላላቸው ገናገሮች ይሰጣሉ፡፡ የግንዘት ስርዓቱም የሚከናወነው ሟችን እንግላል በማስተኛት በጋቢ ጠቅልሎ በአካባቢው ተዘወትሮ ለምግብነት ከሚውለው የቆጮ[9] ተክል ተረፈ ምርት በሚገኝ ቃጫ በማሰር ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በአካባቢው ከሚገኙ አዛውንቶች መካከል አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ተመርጠው ለሞተው ማዘን እንደማይገባ በማሳሰብ ፈጣሪ ሌላ ልጅ እንዲሰጣቸው መርቀው በአካባቢው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ካለፈች ሴት መካከል አንዷን በመምረጥ እንዳያፈስ ሆኖ በተዘጋጀ እርጥብ ቅጠል ውስጥ ተደርጎ ሽማግሌዎች ፊት የነበረን ውኃ በማንሳት የሟችን አባት እና እናት እጅ እንድታስታጥብ ይደረጋል፡፡ ይህ እንዲሆን መደረጉ የአስታጣቢዋ እድል እንዲደርሳቸው ሲሆን ውኃውም በእርጥብ ቅጠል እንዲሆን መመረጡ የእናት ማህፀን እንዲረጥብ፣ የአባትም የዘር ፍሬ እንዲያፈራ በመመኘት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ከተፈፀሙ በኋላ አስክሬኑ ከቤት ወጥቶ እንዲሄድ ይፈቀዳል፡፡ (የተ.ቡ.ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

#### 4.1.1.2. ጊዜ ቀብር ከዋኔ

ጠንከር ካሉ ሁለት መካከለኛ እንጨቶች እና በአካባቢው ከሚገኝ በቀላሉ ከማይበጠስ ሀረግ በተሰራ መሸከሚያ አስክሬኑን አራት ወንዶች ፊት እና ኋላ ሆነው በመሸከም ከጊቢው በመውጣት ላይ ሳሉ እናት እና ሌሎች ሴቶች ሰብሰብ ብለው እንደቀደመው ሁሉ በለሆሳስ እያለቀሱ ለመጨረሻ ጊዜ ሟችን ይሰናበታሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች እናትም ሆነች ሌሎች ሴቶች እንዲሁም ህፃናት ሬሳውን ተከትለው እንዲሄዱ የማይፈቀድላቸው በመሆኑ የጊቢውን አጥር ሳይሻገሩ እንደሚመለሱ፡፡ ይህም የሚሆነው እነዚህ አካላት እንደ ወንዶቹ ችግርን መጋፈጥ ሊከብዳቸው ይችላል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ የሟችን ቀብር በሚያዩበት ጊዜ አምርረው

[9]. "ቆጮ" የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ ሲሆን በሌሎች አካባቢዎች ላይ "እንሰት" ተብሎ ይጠራል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት የሚካሔድበት የህብረተሰብ ክፍል "ቆጮ" እያለ የሚጠራው በመሆኑ በህብረተሰቡ አጠራር መገልገልን ምርጫዬ አድርጌአለሁ፡፡

በማልቀስ ፈጣሪን አስቀይመው የሟች እናት ሌላ ልጅ እንዳትወልድ ፈጣሪ ይጨክንባት ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን መሆኑን አቶ አምባው (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) ያስረዳሉ፡፡

በጉዞ ወቅት ፀጥ ባለ ድባብ ውስጥ ሆነው አስከሬኑን በቅብብል እየተሸከሙ ዝግ ባለ እርምጃ ወደ ቀብር ስፍራው የሚጓዙ መሆኑን በመጥቀስ ቀሪውን ሂደት አቶ አዴሎ ሻጫቸው እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

> የቀብር ስፍራው እንደደረሱም አስከሬኑን በተጎዘጎዘ እርጥብ ቅጠል ላይ በማሳረፍ የታሰረበትን ሀረግ ፈተው ሁለት ሰዎች እቅፋቸው ውስጥ አድርገው ወደተቦረቦረው ዛፍ ውስጥ በአግባቡ አስገብተው ያስተኙታል፡፡ እርጥብ ቅጠል ላይ እንዲያርፍ የሚደረገው ነፍሱ በለምለሚ ገነት እንድትገባ ያለንን ምኞት እንዲገልፅ ነው፡፡ ከዚያም ቀደም ሲል የተዘጋጀውን ክዳን በአግባቡ በመክደን ዙሪያውን በሚስማር ከመቱት በኋላ ቀዳዳውን በሙሉ ቀልጦ በተዘጋጀ ሰም ይሸፍናሉ፡፡ በመጨረሻም አስከሬኑ ከተቀበረበት ከፍ ብሎ ዛፉን መስቀለኛ በመቦርቦር ጎላ ያለ የመስቀል ቅርፅ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ ይህ መሆኑ ብሔረሰቡ የክርስትና እምነት ተከታይ መሆኑን ለማመላከት እና ማንኛውም የብሔረሰቡ አባል ቀፎ ለመስቀል ወይም ለተለያየ ምክንያት ወደዚያ አካባቢ ቢመጣ በዚያ ዛፍ ላይ ህፃን መቀበሩን በመረዳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ለማሳሰብም ጭምር ነው፡፡ (ቃ. መ. 29/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ)

በዚህ መልክ ቀብሩ ከተፈፀመ በኋላ የሟች አባት እና ሽማግሌዎች ከፊት፣ ሌሎች ለቀስተኞች ከኋላ በመሆን ወደመጡበት ይመለሳሉ፡፡

#### 4.1.1.3. ድህረ ቀብር ክዋኔ

ወ/ሮ ዘውዲቱ እና አቶ አምባው እንደሚያስረዱት በድህረ ቀብር ክዋኔ ወቅት ትልቁን ድርሻ የሚይዘው እናትየውን አፅናንቶ ለቀጣይ ዓላማ ዝግጁ እንድትሆን ማስቻል ነው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድም ዋንኛው ኃላፊነት የሚጣለው በአካባቢው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ሌላ ልጅ መውለድ የቻሉ ሴቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች እንዴት ባለ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ሌላ ልጅ መውለድ እንደቻሉ በመንገር የሟች እናት ቀጣይ ልጅ ለመውለድ እራሷን ዝግጁ እንድታደርግ ያነሳሷታል፡፡  ሌላው ልጁ በሞተ በአራተኛ ቀኑ ሴቷን ለግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያዘጋጁበት "ውቶ" የተሰኘ ባህላዊ የጭፈራ ስርዓት አላቸው፡፡ ይህ የጭፈራ አይነት ምሽት ላይ

ሞቅ ተደርጎ በረንዳ ላይ በሚነድ እሳት ዙሪያ የሚካሔድ ሆኖ ጭፈራው ሲጀምር በቁጥር የሚመጣጠኑ ሴቶች እና ወንዶች ብቻ ለብቻ ክብ ሰርተው ይጨፍራሉ፡፡ ኋላ ላይ ጭፈራው እየተጋጋለ ሲመጣ ጥንዶች ተፈላልገው አንዴ እጅ ለእጅ በመያያዝ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሴቷ በወንድየው እቅፍ ውስጥ በመዋል በድምቀት የሚከወን ባህላዊ የጭፈራ ስርዓት ነው፡፡ ስርዓቱ አንድ ሴት ወልዳ ወሩን ሙሉ በእንክብካቤ ታርሳ ከአራስ ቤት ስትወጣም በተመሳሳይ መልኩ የሚካሔድ መሆኑንም ይገልፃሉ፡፡ (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ እና ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

### 4.1.2. ለአዋቂዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት

በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት በዕድሜ ገፋ ላሉ ሰዎች የሚደረግ የለቅሶ ስርዓት ልዩነት የሚኖረው ሟች ወይም የሟች ቤተሰቦች ባላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳላቸው ተቀባይነት እና ሟች የባህላዊ ስልጣን ባለቤት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ሟች በህይወት ዘመኑ ያከማቸው ሀብትና ንብረት ያለው ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ የዚያኑ ያህል በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ያልፋል፡፡ ነገር ግን የሟች የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ ከሆነ እምብዛም የደመቀ ለቅሶ እና ሰፋ ያለ ስርዓት ላይኖር ይችላል፡፡ በሌላ አንፃርም ሟች በህይወት ዘመኑ ከማህበረሰቡ ጋር የነበረው መስተጋብር ዝቅተኛ ከሆነ በዚያው መጠን የለቅሶ ስርዓቱ ሊደበዝዝ ይችላል፡፡

በቀደመው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው የሸካቾ ብሔረሰብ እንደአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ሁሉ የራሱ በሆነ ንጉስ የሚመራ ነበር፡፡ በዚህ የንግስና ስርዓት ውስጥ በተዋረድ ካሉ የባህላዊ ስልጣን ባለቤቶች መካከል አንዱ ቢሞት የለቅሶ ስርዓቱ "ከተራው" የህብረተሰብ ክፍል የለቅሶ ስርዓት የሚለይበት የራሱ የሆነ ገፅታ ያለው ቢሆንም ያን ያህል ጉልህ ነው ተብሎ የሚገለፅ ልዩነት አይስተዋልም፡፡ (ቃ.መ. አቶ አምባው ጮሪቶ 03/07/ 06 እና አቶ ኃይሌ ማድራሻ 04/07/06፣ ማሻ )

የሸካቾ ብሔረሰብ የአዋቂዎች የለቅሶ ስርዓት የጋራ የሆኑ ገፅታዎችን በስፋት በማንሳት ልዩነት የሚስተዋልባቸውን ነጥቦች በመጠቆም እንደሚከተለው ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ምን እንደሚመስል ለማሳየት ይሞከራል፡፡ ለአቀራረብ ይመች ዘንድም በቅድመ እና ጊዜ ሞት እንዲሁም በቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ቀብር ወቅት የሚታዩት ልዩ ልዩ ገፅታዎች ተዘርዝረው ይተነተናሉ፡፡

#### 4.1.2.1. ቅድመ ሞት ክዋኔ

በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት አንድ ሰው በፀና ከታመመ መታመሙን የሰሙ የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ወደ ታማሚው ቤት በመቅረብ "እግዜር ይምረው ዘንድ" መልካም ምኞታቸውን መግለፅ ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ስለሺ ጫሊቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> አንድ ሰው በጣም ታሞ ከቤት መውጣት ያቃተው መሆኑ ሲታወቅ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች በቡድንም ሆነ በተናጠል ወደ ሰውየው ቤት በመቅረብ ሰውየውን ያበረታቱታል፣ ፈጣሪ እንዲምረውም ይፀልዩለታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የታማሚው የቅርብ ዘመድ እና የጎሳው አባላት ለበሽተኛው ይስማማል ብለው ያሰቡትን ምግብ እና መጠጥ በመያዝ ተመላልሶ መጠየቅ በኛ ባህል እንደግዴታም የሚቆጠር ነው፡፡ (ቃ.መ. 28/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በሽተኛውን እየተመላለሱ ከሚጠይቁት ሰዎች መካከል ከዘመናዊው ህክምና በተጨማሪ ለህመሙ ይበጃል የሚሉት ባህላዊ መድኃኒት የሚያውቁ ከሆነ ወይም ከሚያውቅ ሰው በመጠየቅ አምጥተው በሽተኛው እንዲፈወስ የማድረጉም ጥረት በሰፊው የሚከናወን መሆኑንም የቀደሙት መረጃ አቀባዬ ይጠቅሳሉ፡፡

ህመምተኛው ያለበት ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን በእድሜ ከፍ ያሉ የታማሚው ዘመዶች እና የአካባቢው ሽማግሌዎች እንደተረዱ በዚህ ወቅት የሚፈፀመውን ሌላኛውን ተግባር አቶ አምባው ጮሪቶ "በሽተኛው እንደበቱ ከመዘጋቱ በፊት ሀብት እና ንብረቱ እንዴት እንዲሆንለት እንደሚፈልግ ለማወቅ በቤተሰቡ አባላት የጋራ ስምምነት ለተመረጡ ሦስት ሽማግሌዎች እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ ዛሬ ዛሬ ኑዛዜውን መፃፍ የሚችል አንድ ሰው ከሽማግሌዎቹ ጋር አብሮ እንዲሆን የሚደረግ ቢሆንም ቀደም ባለው ጊዜ ግን ሽማግሌዎቹ የሰሙትን በቃል እንዲያስተላልፉ ነበር የሚደረገው፡፡" (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም) በማለት ያብራራሉ፡፡

የኑዛዜው ተግባር ከተፈፀመ በኋላ ታማሚው ያለበት ሁኔታ ከቀድሞው የባሰ መሆኑ የበሽተኛውን ሁኔታ በንቃት በሚከታተሉት ሽማግሌዎች ሲረጋገጥ በአካባቢው ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ተሰባስበው ጓሮ ላይ በፍጥነት የሳር ክዳን ቤት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ የቤቱ ስራ በአካባቢው ባሉ ሰዎች ርብርብ ተሰርቶ እንዳለቀ ሽማግሌዎቹ ነፍስ ያወቁ ቤተሰቦቹን እንዳለ በማስጠራት

ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በየተራ አይኑን አይተው እንዲሰናበቱ እና በድሎኛል የሚሉት ነገር ካለም ይቅር እንዲሉት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ ባያደርጉም ሁሉም ስንብቱን በለቅሶ ነው የሚቋጩት፡፡ (ምልከታ ፲፣ ከ20 - 24/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ)

አቶ ኃይሌ መድራሻ ቤተሰቦቹ ታማሚውን ከተሰናበቱ በኋላ ስለሚፈፀሙ ነገሮች እንደሚከተለው በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡

> በእኛ ባህል መሰረት ሬሳ ከመኖሪያ ቤት ከወጣ ቤቱ ይረከሳል፣ በዚያ ቤት ውስጥ ሞት ይለምዳል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ቤተሰቦቹ ከተሰናበቱት በኋላ በሽተኛው ከቤት ወጥቶ በዚያው ጊቢ ውስጥ በሳር ክዳን ወደተሰራለት አዲስ ቤት እንዲገባ ይደረጋል፡፡ በሽተኛው እዚህ ቤት ከገባ በኋላ የመመገቢያ ዕቃም ሆነ ምግብ አዘጋጅቶ የሚያቀርቡ አካላት ተለይተው ከበሽተኛው ጋር እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለታማሚው ካላቸው መውደድ የተነሳ በራሳቸው ፍላጎት የሚመደቡ ሁለት በሙያቸው የተመሰከረላቸው ሴቶች እና ሁለት ጠንከር ያሉ ወንዶች እንዲሁም የግንዘት ስርዓቱን መፈፀም የሚችሉ ሁለት የታማሚው ጎሳ አባል የሆኑ አዛውንቶች ሲሆኑ ታማሚው ህይወቱ አልፋ ሬሳው ግብዓተ መሬቱ እስኪፈፀም ድረስ ከዚያ ቤት ወጥተው ወደ መኖሪያ ቤት እንዲገቡም ሆነ ሌሎች ዕቃዎችን እንዲነካኩ አይፈቀድላቸውም፡፡ ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ ግን እንደ ፀበል በሚቆጠር "ደሶ አጮ" በተሰኘ ውኃ በሽማግሌዎች ተረጭተው እንዲነፁ ተደርገው ከሰው ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በዚህ ወቅት ከሚከወኑ ሌሎች አበይት ጉዳዮች መካከል የሬሳ ሳጥን "ጎኖ" ዝግጅት አንዱ ነው፡፡ በሸካቾ ባህል መሰረት የሬሳ ሳጥን የሚዘጋጀው አራት ጣውላዎችን በሚስማር በማገናኘት ሳይሆን ለዚሁ ዓላማ ሲባል እያንዳንዱ አባወራ በቤተሰቦቹ ልክ በነፍስ ወከፍ በማሳው ውስጥ ተንከባክቦ ከሚያሳድገው የሾላ ወይም የዋንዛ ዛፍ ተቦርቡሮ የሚዘጋጅ ነው፡፡ እነዚህ የዛፍ አይነቶች የሚመረጡት ከሌሎቹ ይልቅ በቀላሉ ስለሚጠረቡ እና ብል በቀላሉ ሊያጠቃቸው የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ አንድ የብሔረሰቡ አባል የጤንነቱ ሁኔታ በእጅጉ አስጊ ደረጃ ላይ ከደረሰ በቤተሰቡ ወይም በአካባቢው ሰዎች አስተባባሪነት ባለሙያ ተፈልጎ በማሳው ካሉት ዛፎች መካከል አንዱን በመጣል ለሰውየው ቁመት የሚበቃውን ያህል ከዛፉ ቆርጦ በመለየት በባህላዊ ቀፎ ቅርፅ በአግባቡ ተጠርቦ ይዘጋጃል፡፡




ፎቶ 1. በዝግጅት ላይ ያለ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የሬሳ ሳጥን፤

እንጨቱን በዚህ መልክ በአግባቡ ክብ አድርገው ከጠረቡ በኋላ ከአናቱ በጥንቃቄ ለክዳን የሚሆን ነገር ጠርበው (በአሁኑ ወቅት በመጋዝ የሚዘጋጅ ቢሆንም ቀደም ሲል ግን በስለት መጥረቢያ ነው ክዳኑ ተቀፎ የሚነሳው) ያነሱና ውስጡን ቦርቡረው የቀፎ ቅርፅ በማስያዝ ዝግጁ ያደርጋሉ፡፡



ፎቶ 2. ዝግጅቱን የጨረሰ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የሬሳ ሳጥን፤

በዚህ መልክ የተዘጋጀው ሳጥን የበሽተኛው ነፍስ እስኪወጣ ድረስ ኩሽና ውስጥ እሳት ዳር እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ እሳት ዳር እንዲሆን የተፈለገው ትንሽ ደረቅ እንዲል ነው፡፡ ይህ አይነቱ

ሳጥን በብሔረሰቡ ዘንድ ጥርስ ካላበቀሉት ህፃናት ውጭ ላሉት ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች አገልግሎት ላይ የሚውል ነው፡፡ (የተ.ቡ. ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

#### 4.1.2.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ

የታማሚው ነፍስ ማለፏ ከጎን ባሉ የዕድሜ ባለፀጎች እንደተረጋገጠ ወዲያውኑ የሟችን ታላቅ ወንድ ልጅ በማስጠራት (ወንድ ልጅ የሌላቸው ከሆነ ከቤተሰቡ መካከል የቅርብ ዘመድ የሆነ ታላቅ ወንድ ሊሆን ይችላል) ስለ ሁኔታው አስረድተው አስከሬኑን እንዲያጥብ ያደርጉታል፡፡ ከዚያም ሽማግሌዎቹ ወዲያውኑ የግንዘቱን ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ አስከሬኑን ቀጥ አድርጎ በጀርባው በማስተኛት አይኑን እንዲሸፈን፣ ጥርሶቹ እንዲከደኑ፣ ከንፈሩ እንዲገጠም ካደረጉ በኋላ ሁለት እጆቹ ብልቱን እንዲሸፍኑ አድርገው የእግሮቹን አውራ ጣቶች እና ጉልበት አጣምረው በቃጫ[10] ያስራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ አድርገው ሬሳውን ከመከፈናቸው በፊት በዕድሜ ፀና ያሉ የሟች ቤተሰቦችን ወደ ሬሳ ቤቱ እንዲቀርቡ በማስደረግ ሬሳውን ወደ በረንዳ አውጥተው ሞቱን እንዲያረጋግጡ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ድምፅ ጎላ ብሎ እንዳይወጣ የሚከለከል ቢሆንም የሚኖረው ለቅሶ መሪር ነው፡፡ በመቀጠልም ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ትልቅ ጋቢ አስከሬኑን ከፍነው በሳጥን ውስጥ በማስገባት የክዳኑን ዙሪያ በሚስማር በመምታት ምንም አይነት ክፍተት እንዳይኖር ያደርጋሉ፡፡

ሬሳ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ሽማግሌዎች እና አስተናባሪዎች የሳጥኑን ክዳን ዙሪያ ሰም እያቀለጡ በአግባቡ የመሸፈን ስራ ሲሰሩ ከደጅ ያሉት ትልቅ በሬ አርደው ቆዳውን ለሬሳ ሳጥኑ መሸፈኛ እንዲሆን ያቀርባሉ፡፡ ሽማግሌዎችም ሳጥኑን በቀረበላቸው ትኩስ ቆዳ በመሸፈን ይጠፍራሉ፡፡ በመጨረሻም የተጠፈረበትን ዙሪያ ገባ ሰም አፍስሶ በመሸፈን በሬሳ ክፍል ውስጥ እሳት ዳር በእንጨት ፍርግርግ ተሰርቶ በተዘጋጀ የሬሳ ሳጥን ማስቀመጫ ላይ ሬሳውን በማኖር ጥሩ መዓዛ ያላቸው የጭስ እንጨቶች በብዛት እንዲጨሱ ይደረጋል፡፡ መልካም ጠረን አላቸው ተብለው ከሚመረጡት መካከል ጤናዳም፣ የነጭ ባህር ዛፍ ቅጠል፣ አሪቲ፣ ኮሰረት እና የወይራ እንጨት ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ጤናዳም እና የነጭ ባህር ዛፍ ቅጠል ሬሳውን ለማጠብም ይገለገሉባቸዋል፡፡ ይህ ተግባር ጥርስ ካላበቀሉ ህፃናት ውጭ ላሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ተግባራዊ እሚሆን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሟች ሴት ከሆነች የእጥበቱን ስራ የምታከናውነው

[10] . ቃጫ የሸካቾዎች ባህላዊ ምግብ ከሆነው ቆጮ ተረፈ ምርት የሚገኝ የተለያየ መጠን ያላቸውን ማሰሪያዎች ለመስራት የሚያገለግል ነው፡፡

የመጀመሪያዋ ሴት ልጅ ነች፤ ሟች ሴት ልጅ የሌላቸው ከሆነ የታላቅ ወንድ ልጅ ሚስት እጥበቱን እንድታከናውን ይደረጋል፡፡ (የተ.ቡ. ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

#### 4.1.2.3. ቅድመ ቀብር ክዋኔ

እንደ የተተኳሪ ቡድን ተወያዮቼ አገላለፅ በሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ወቅት ሰፊውን ድርሻ የሚይዙት ከቀብር በፊት የሚፈፀሙ ዝግጅቶች ናቸው፡፡ ይህ ዝግጅት ሟች አንዳች ማህበራዊ ስልጣን ወይም ኢኮኖሚያዊ አቅም ያለው ከሆነ ደግሞ ከሌላው ይልቅ ሰፋ ይላል፡፡ ከቀብር በፊት ከሚከናወኑ ዝግጅቶች መካከል የምግብ እና መጠጥ ዝግጅት፣ ለቅሶ ነጋሪዎችን ማሰናዳት፣ በሟች ማሳ መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት ማከናወን፣ ለእርድ የሚሆኑ ከብቶች ማዘጋጀት፣ የቀብር መሄጃውን ማፅዳት እና የቀብሩን ቦታና ቤት ማዘጋጀት፣ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ ማፅዳት እና ዳስ መስራት፣ አስከሬኑ ተሸፍኖ የሚሄድበት ሰረገላ ማዘጋጀት፣ በቀብሩ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ አልባሳትን እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፣. . .ወዘተ የሚሉት ዋንኛውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ (የተ.ቡ. ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

እነዚህ የቅድመ ቀብር ክንውኖች የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ቀብሩ ከመፈፀሙ በፊት ከተወሰኑ ቀናት ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ድረስ እንዲቆይ ሊያስገድዱ የሚችሉ እንደመሆናቸው መጠን ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው፡፡

**የምግብ እና መጠጥ ዝግጅት፡-** የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ የሚባለው ቆጮ ሲሆን ጠጅ ወይም ቦርዴ ደግሞ በብሔረሰቡ በግንባር ቀደምትነት የሚመረጡ ባህላዊ መጠጦች ናቸው፡፡ ቆጮ በብሔረሰቡ ዘንድ በበዓላት ቀን አሊያም ለየት ባሉ ዝግጅቶች ላይ ብቻ ለምግብነት የሚውል የምግብ አይነት ሳይሆን ሁሌም ከጠዋት እስከ ማታ ከሌሎች ማባያዎች ጋር ለምግብነት የሚውል ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን በከተሞች አልፎ አልፎም ለከተሞች አቅራቢያ በሆኑ የገጠር ክፍሎችም ዘንድ እንጀራም እንደ አማራጭ በማዕዱ ላይ ይቀርባል፡፡




ፎቶ 3. የቆጮ ተክል፣

ቆጮ ተተክሎ ለመድረስ ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚፈልግ የተክል አይነት ሲሆን ማንኛው የሸካቾ ብሔረሰብ በነፍስ ወከፍ ሰፋ አድርጎ በማሳ ውስጥ ከሚተክላቸው ተክሎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ አንድ ቆጮ ተፍቆ በጥሩ ሁኔታ ለምግብነት ለመድረስ ከ1 ወር እስከ 40 ቀን የሚፈጅ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በአንድ የለቅሶ ስርዓት ላይ በዋናነት የሚቀርብ የምግብ አይነት እንደመሆኑ መጠን በቀብሩ ዕለት ሊገኝ ይችላል ተብሎ እንደሚገመተው ሰው ቁጥር ልክ ቆጮን በብዛት እና በጥራት ለማዘጋጀት የሚያስችልን ቀን ከግምት ውስጥ አስገብቶ የቀብር ጊዜን መወሰን በብሔረሰቡ ዘንድ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ቆጮው የሚዘጋጀው ሞት በተከሰተበት አካባቢ ባሉት ሴቶች እና በሩቅም ባሉ የሟች ጎሳ አባል በሆኑ ሰዎች ቤትም ጭምር ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ለቆጮ ማባያነት የበሬ ወይም የበግ ስጋ፣ ጎመን እና አይብ ተመራጮች ናቸው፡፡




ፎቶ 4. ለለቀስተኞች በስሎ የተዘጋጀ ቆጮ፣

በቀብሩ ዕለት ከተለያዩ አካባቢዎች ለሚመጡ ለቀስተኞች ከቀብር በኋላ ከሚቀርቡ ባህላዊ መጠጦች መካከል ለዝግጅት ከወር በላይ የሚፈልገው ጠጅ (ጠጅ በሸክኛ "ቢቶ" የሚባል ሲሆን በዕውቅ ባለሙያ ከወር እስከ ሦስት ወር ድረስ እንዲቆይ ተደርጎ የሚዘጋጀው ግን "ቢታ ቢቶ" ይሰኛል፤ ከጠጅም ጠጅ እንደማለት) ዋንኛውን ስፍራ ይይዛል፡፡ በዋናነት ጠጅ የሚዘጋጀው ከማር እና ከጌሾ ሲሆን ዝግጅቱ የሚካሔደው በዋናነት በሟች ቤት ውስጥ ሆኖ በአካባቢው ያሉ በጠጅ መጥመቅ ስራቸው የተካኑ ሴቶች አስተባባሪነት ነው፡፡ ጠጁ ተጥሎ አንድ ወር ከቆየ በኋለ ዳግም በማርና በውኃ በመበጥበጥ ለሌሎች በርካታ ቀናት የሚቆይበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህ ሲሆን ጠጁ ከአስካሪነቱ ይልቅ ለሰውነት የሚሰጠው ጠቀሜታ ይጨምራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከጠጅ በተጨማሪ ከቀይ ጤፍ የሚዘጋጀው "ቦርዴ"ም ከቀብር በኋላ በአማራጭነት የሚቀርብ በመሆኑ በዚሁ ወቅት የሚዘጋጅ ነው፡፡

ሌላው በቀብር ዕለት ለምግብነት ለሚቀርበው ቆሎ እና ንፍሮ ዝግጅት የሚሆን በቆሎ እና ባቄላ፣ ቡና እና ለጨሞ ዝግጅት የሚሆን የቡና ቅጠል ማሰናዳት በቅድመ ቀብር ወቅት ከሚፈፀሙ የምግብ እና የመጠጥ ዝግጅቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡ (ቃ.መ. ወ/ሮ ዘውዲቱ አንገሎ፣ 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ እና ወ/ሮ በላይነሽ አርጀፎ፣ 26/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

***ለቅሶ ነጋሪዎችን ማሰናዳት፡-*** በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት የብሔረሰቡ አባል ሆኖ ለቅሶ አለመድረስ ከህብረተሰቡ ጋር ከሚያቃቅሩ ጉዳዮች መካከል በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

በመሆኑም ሞት በተከሰተበት አካባቢ ያሉት አዛውንቶች ከቤተሰቡ አባላት ጋር በመሰብሰብ የቀብሩን ቀን እና በቀብሩ ዕለት በዋናነት እንዲገኙ የሚፈልጓቸውን ሰዎች ዝርዝር በጋራ ተነጋግረው ይወስናሉ፡፡ ቀደም ባለው የብሔረሰቡ እምነት መሰረት የቀብር ቀን ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ ላይ እንዲውል አይደረግም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቀናት እህል ቢዘራባቸው እንኳ አያበቅሉም፤ ደረቅ ናቸው ተብሎ የሚታመን ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍ ያለ ድርሻ የሚሰጣቸው የህብረተሰቡ አካላት ሲሞቱ የብሔረሰቡ አባላት ወደሚኖሩባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በሙሉ መልዕክተኞችን በእግር፣ በፈረስ እና በመኪና በመላክ የቀብሩን ቀን እና ቦታ በአግባቡ ተናግረው እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን በአብዛኞቹ አካባቢዎች የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት በስፋት ያለ በመሆኑ ሁሉም ለሚያውቀው ደውሎ እንዲናገር በማድረግ ነው የመረጃ ልውውጡ የሚካሔደው፡፡ በመሆኑም ትራንስፖርት ባልተስፋፋበት ወቅት ከማሻ - አዲስ አበባ ድረስ በእግር ተጉዘው እንዲናገሩ ይደረግ የነበረው አድካሚ እና ጊዜ ፈጅ የነበረው አሰራር ተሻሽሏል፡፡

ለመልዕክተኛነት የሚመረጡት ሰዎች ጎልማሳ ሆነው የጤንነታቸው ሁኔታ "መልዕክቱን ሳያደርሱ ከመንገድ ሊቀሩ ይችላሉ" የሚል ስጋት ውስጥ የማይከቱ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚላኩበትን አካባቢ እና ሰው የሚያውቁ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ይህ ምርጫ የቤተሰቡ አባላት የሆኑ ጎልማሶችን አያካትትም፡፡ ምክንያቱም እነሱ በኃዘን ተጎድተዋል በሚል ነው፡፡ በዚህ መልክ ተመልምለው የተላኩት መልዕክተኞች ወደተላኩበት ሰው ቤት እንደደረሱ በአካባቢው ከሚገኙ ሰዎች ቤቱ በእርግጥ የተላኩበት ሰው መሆኑን፤ አለመቀየሩን በማጣራት በቀስታ ወደ ውስጥ ዘልቀው ሟቹ የሚስት ዘመድ ከሆነ ለባል፣ የባል ዘመድ ከሆነ ደግሞ ለሚስት ስለሁኔተው ቀድመው በማስረዳት ለሟች ወገን በማስተዛዘን እና በቀስታ በመንገር ይላቀሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ትንሽ ዕረፍት እንዳደረጉ የቀብሩን ቀን እና ቦታ በጥንቃቄ ነግረው ሌሎች በአካባቢው ለሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት ንገሩ መባላቸውን በማሳሰብ የሄዱበት መንገድ ሩቅ ከሆነ እንደሁኔታው አንድም ሆነ ሁለት ቀን አርፈው ይመለሳሉ፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ታልፎ መልዕክቱ ከደረሰው በኋላ ብዙም አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት በቀብሩ ዕለት በማይገኝ የብሔረሰቡ አባል ላይ የሚኖረው መገለል ከፍተኛ ነው፡፡ (ቃ.መ. አቶ መንገሻ አለሙ፣ 27/06/06 ዓ.ም ይና ቀበሌ እና አቶ ኃይሌ መድራሻ፣ 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

**በሟች ማሳ መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት ማከናወን፡-** የሰው ልጅ ታሞ አልጋ የሚይዝበት ብሎም የሚሞትበት ቀን በውል የማይታወቅ በመሆኑ አንድ ሰው በሚሞትበት ወቅት

በጅምር የሚቀሩ ስራዎች፣ ያልተፈፀሙ ዕቅዶች፣ ያልተከፈሉ ዕዳዎች ወይም ያልተመለሱ ብድሮች ይኖራሉ፡፡ የሸካቾ ብሔረሰብ በዋናነት የሚተዳደረው በግብርና ስራ ላይ እንደመሆኑ መጠን በአካባቢው የሚሰሩ ስራዎች ወቅትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጊዜው የእርሻ ሆኖ ሳለ በተለያዩ ምክንያቶች የሟች ማሳ ጦሙን ያደረ ከሆነ በአካባቢው የሚገኙ የጎሳው አባላት ተሰባስበው በመካከር የሟችን ማሳ መንጥረው፣ አርሰው፣ ጎልጉለው እና ዘርተው ከቀብር በፊት በማሰናዳት ሟች ወገን ያለው መሆኑን ማስመስከር የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሟችን ማሳዎች ማጠር፣ ቀፎ መስቀል እና ቆጮውን መኮትኮትም በእነዚሁ አካላት በተጓዳኝ ይፈፀማል፡፡

ከዚህ ጋር በተጓዳኝ በሌሎች አካላትም ጭምር የሚከወነው ሌላው ተግባር ለማገዶ የሚሆን እንጨት ማሰናዳት ነው፡፡ ሞት በአካባቢው መከሰቱን የሰሙ በአካባቢው የሚገኙ አባወራዎች በሙሉ ከቀብሩ ቀን ቀደም ብለው በነፍስ ወከፍ አንዳንድ እንጨት በመያዝ በሟች ቤት እያመጡ መከመር የኖረ ልምድ ነው፡፡ ከእዚህ በተጨማሪ ግን ማሳውን በማሰናዳት ላይ የሚገኙት አካላት በማሳው ውስጥ የሚገኙ ደረቅ ዛፎችን በመጣል በህብረት ፈልጠው በማሳ ያለው ስራ እስኪጠናቀቅ ወደ ሟች ቤት በማጓዝ የማገዶ እንጨት ችግርን ይቀርፋሉ፡፡ በሸካቾዎች ባህል ለወትሮውም ቢሆን የማገዶ እንጨት የማቅረብ ግዴታ የተጣለው በወንዱ ላይ መሆኑን አቶ አዴሎ ሻጫቸው (ቃ.መ. 29/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ) በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡

**ለእርድ የሚሆኑ ከብቶች ማዘጋጀት፡-** የቀብሩ ዕለት ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰባስበው የመጡት ለቀስተኞች የተሻለ ነገር ተመግበው እንዲሄዱ ማድረግ በሸካቾዎች ባህል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የሟች ቤተሰቦች፣ አማቾች እና የጎሳው አባላት በዋናነት ለዚህ የሚሆኑ ግብዓቶችን የማሟላት ማህበራዊ ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ በመሆኑም የሟችን ልጅ ያገቡ አቅማቸው የሚፈቅድ ከሆነ እያንዳንዳቸው አንዳንድ በሬ ወይም መሴና ከብት፣ የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑት ደግሞ ሙክት በግ፣ ቅርበት ያላቸው የሟች ጎሳ አባላት እና ጓደኞች ደግሞ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ከፍ ሲል ከተጠቀሱት አንዱን መርጠው በማቅረብ የሟች ቤተሰቦች ባዘጋጁት ላይ ተጨማሪ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰበሰቡት ከብቶች ቁጥራቸው ከ10 እስከ 20 አንዳንዴም ከዚህም ሊዘል ይችላል፡፡ የከብቶቹ እርድ የሚፈፀመው ከቀብሩ ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ አመሻሽ ላይ ሲሆን የሚታረደው የከብት ቁጥር የሚወሰነው ይመጣል ተብሎ በሚገመተው የሰው ቁጥር ልክ

ነው፡፡ (ቃ.መ.አቶ ስለሺ ጫሊቶ 28/06/06 ዓ.ም እና አቶ አምባው ጮሪቶ፣ 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

**የቀብር መሄጃውን ማፅዳት እና የቀብሩን ቦታና ቤት ማዘጋጀት፡-** የቀብር ቦታ በሸክኛ "ጌዳሜ ጣኦ" የሚባል ሲሆን ቀደም ባለው የሸካቾዎች ባህል መሰረት በሁለት የተለያዩ ስፍራዎች ላይ የቀብር ቦታ እንዲዘጋጅ ይመረጣል፡፡ አንደኛው በሟች መኖሪያ አካባቢ ባለ የግል ማሳ ውስጥ የሚሰናዳ ነው፡፡ ሟች በማሳው ውስጥ የሚቀበርበት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው በኑዛዜው ወቅት ሟች "በማሳዬ ውስጥ ቅበሩኝ" ያለ እንደሆነ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የሟች ቤተሰቦች በአቅራቢያችን ተቀብሮ መቃብሩን በየጊዜው እየጎበኘን መንከባከብ እንፈልጋለን የሚል ሀሳብ ያቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡

ሁለተኛው የቀብር ስፍራ ከአካባቢው ወጣ ብሎ በሚገኝ ኮረብታማ ስፍራ ላይ የአካባቢው ሰዎች በጋራ ያሰናዱት የቀብር ስፍራ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በእንዲህ ያለ ስፍራ የሚቀበሩት ነገስታት፣ የጎሳ መሪዎች፣ ቃልቻዎች እና በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ስም ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀብሩ ዕለት ሴቶች ለቀብር በተከለለው አጥቢያ ውስጥ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህ የሚሆነውም ቦታው ንፁኃን ያረፉበት የተቀደሰ ስፍራ ተደርጎ ስለሚታሰብ ምናልባት ቀናቸው ላይ የሆኑ ሴቶች ተቀላቅለው ገብተው ያረክሱታል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

እነዚህ የቀብር ስፍራዎች በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ ቀርተዋል ለማለት ባያስደፍርም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በየኃይማኖት ስፍራው ተከልሎ በሚገኘው የቀብር ቦታ መቅበርን ተቀዳሚ ምርጫው ያደርጋል፡፡ የሆነ ሆኖ ባህላዊውን የቀብር ስፍራ አዘገጃጀት ስንመለከት የቀብሩ ዕለት ሦስት ቀን ሲቀረው ወደ ቀብር ስፍራ መሄጃ መንገዱን ሰፋ አድርጎ መመንጠር ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡ ቀጥሎም ልምዱ ያላቸው ሰዎች ተለይተው ቀብሩ እዚህ ጋር ቢሆን የተሻለ ይሆናል የሚሉትን ቦታ በመምረጥ በአራት ማዕዘን ቅርፅ አራት ክንድ ጥልቀት ያለው ጉርጓድ ሰፋ አድርገው ይቆፍራሉ፡፡ ከዚያም የሬሳ ሳጥኑ የሚያርፍበትን ዙሪያ ገባ በሙሉ ድንጋይ በሸክላ አፈር እያጣበቁ (በአሁኑ ጊዜ በሲሚንቶ ነው የሚያጣብቁት) በጥንቃቄ ይደረድራሉ፡፡



ፎቶ 5. የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የመቃብር ጉድጓድ፣

በዚህ መልክ ድንጋዩን በአግባቡ ከደረደሩ በኋላ ሳጥኑ የሚያርፍበትን ዙሪያ በጨርቅ ይሸፍኑታል፡፡ የኢኮኖሚ አቅማቸው ከፍ ያለ ወይም አንድ አይነት ማህበራዊ ስልጣን ያላቸው ከሆኑ ደግሞ ጉድጓዱ ሙሉ በሙሉ የድንጋይ ካብ ይሰራለታል፡፡ በመጨረሻም በአካባቢው ከሚገኝ እንጨት ተጠቅመው የሳር ክዳን ቤት በላዩ ላይ ይሰሩበታል፡፡ (ቃ.መ. አዴሎ ሻሜቸው፣ 29/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ)

**የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ ማፅዳት እና ዳስ መስራት፡-** አብዛኛውን ጊዜ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ የማፅዳት ኃላፊነት የሚጣለው በወጣት ሴቶች እና ወንዶች ላይ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ዘውዲቱ አንገሎ ሲያስረዱ "ሴቶቹ የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ "ጊጠሮ" በሚባል በሁለት በኩል መያዣ ባለው የተቆለመመ ገጀራ መሰል ብረት በመታገዝ ሙልጭ አድርገው ሳርና ቆሻሻውን የማስወገድ ተግባራቸውን ሲወጡ ወንዶቹ ደግሞ ከሴቶቹ አቅም በላይ የሚሆነውን በገጀራ በመመንጠር እና በቤቱ ዙሪያ ያለውን አጥር የማጠናከር ድርሻቸውን በትብብር ያከናውናሉ፡፡" (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ) በማለት ነው፡፡

ሌላው በጎልማሶች የሚሰራው ተግባር የዳስ ስራ ነው፡፡ ዳሱ የሚጣለው በሟች መኖሪያ ቤት አራቱም አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትን ዋንኛ ምክንያት አቶ አምባው ጮሪቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጡትን ለቀስተኞች በየመጡበት አቅጣጫ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሲሆን በአራቱም ዳስ ውስጥ በሚመደቡት አስር አስር አስተባባሪዎች አማካኝነት "ማን መጥቷል ? ማንስ አልመጣም ?" የሚለውን በአግባቡ ለመለየትም ጭምር ነው፡፡ በእያንዳንዱ ዳስ ውስጥ በዋናነት የሚመደቡት 5 ወንድ እና 5 ሴት አስተናጋጆች ሲሆኑ ከሴቱም ከወንዱም አንዳንድ አስተባባሪ ይሰየማል፡፡ እነዚህ አካላት ከቀብሩ አንድ ቀን ቀደም ብለው በመሰባሰብ በያቅጣጫቸው ያሉ ቀበሌዎችን በአግባቡ መለየት፣ ማን ተቀብሎ ቦታ ያስይዝ፣ ማን ምግብ ያቅርብ፣ ማንስ መጠጥ ያሳልፍ፣ . . .ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ነው የሚያድሩት፡፡ በመሆኑም የእነዚህ አካላት ምርጫ በህብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈፀም ነው፡፡ (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

ለዳስ መስሪያ በዋናነት ከሚያስፈልጉት ግብዓቶች መካከል በርከት ያለ የቀርቀሀ እንጨት፣ የቆጮ ቅጠል እና ሀረግ (ቃጫ) ዋንኞቹ ናቸው፡፡





ፎቶ 6. ለለቀስተኞች ማረፊያ የሚሆን ባህላዊ ዳስ ዝግጅት፣

ሞት በተከሰተበት አካባቢ የሚገኙ የአካባቢው ሰዎች እና የቤተሰቡ አባላት ቀብሩ 5 ቀን ሲቀረው ጀምረው ያዘጋጁቸውን የዳስ መስሪያ ቁሳቁሶች ተጠቅመው በየአቅጣጫው በመከፋፈል ከቀብሩ ዕለት ሦስት ቀን ቀደም ብለው የዳሱን ስራ በህብረት ይሰራሉ፡፡ አካባቢው 13ቱንም ወር ሙሉ ዝናብ የማያጣው በመሆኑ በክዳንነት የሚያገለግለውን የቆጮ ቅጠል በርከት አድርጎ ማልበስ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በተለይም ሟች ንጉስ አሊያም የጎሳ መሪ ከሆነ በዕለቱ ከባድ ዝናብ

ይጥላል ተብሎ የሚታመን በመሆኑ በእነዚህ አካላት ለቅሶ ላይ የሚዘጋጁ ዳሶች ከወትሮው የተሻለ ጥንቃቄ ይደረግባቸዋል፡፡

በዚህ መልክ በሚዘጋጀው ዳስ ውስጥ የሟች አማቾች በመጡበት ቀበሌ አቅጣጫ በተሰራው ውስጥ የቀብሩ ዕለትም ሆነ ከዚያ በኋላ ባሉት የሀዘን ቀናት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ የአማቾቹ ቁጥር ከዳሱ ቁጥር የሚበልጥ ከሆነ ደግሞ እንደሁኔታው በጋራ እንዲቀመጡ የሚደረግ መሆኑን አቶ ኃይሌ መድራሻ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) ያስረዳሉ፡፡

**አስክሬን ታጅቦ የሚሄድበት ሰረገላ ማዘጋጀት፡-** ይህ ዝግጅት የሚከናወነው ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን ንጉስ የሞተ ዕለት ብቻ ነው፡፡ አገልግሎቱም የንጉሱን አስክሬን ከሌላው ለቀስተኛ ለየት አድርጎ በክብር እመቃብር ቦታው ድረስ ሸፍኖ ማድረስ ነው፡፡



ፎቶ 7. የሸካቾ ብሔረሰብ ነገስታት እና ስመ ጥር የጎሳ መሪዎች ሲሞቱ አስክሬን የሚታጀብበት ሰረገላ፣

የሰረገላውን አዘገጃጀት አቶ ስለሺ ጫሊቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

ሰረገላው የሚዘጋጀው በቀርቀሀ ሆኖ የቤት ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ነው፡፡ አንዱን ቀርቀሀ ከሌላኛው በሀረግ እና በቃጫ በአግባቡ ካሰሩ በኋላ ደማቅ ከለር ባላቸው ጨርቆች እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡ አስክሬኑ በሰረገላው ውስጥ ሆኖ የሚጓዝ ከመሆኑ አንፃር በሰረገላው ዝግጅት ወቅት ታሳቢ ከሚደረጉ ነገሮች መካከል አስክሬኑን በፍርርቅ ተሸክመው የሚጓዙ ከ20 የማያንሱ ሰዎችን በአግባቡ ሊይዝ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጀው ሰረገላ በአራቱም ማዕዘን ከውጭ ሆነው በመተጋገዝ እንዲይዙ

በተመረጡ ጠንከር ያሉ ሰዎች ትከሻ ላይ አርፎ በአዝግሞ እንዲጓዝ ይሆናል፡፡ ከውስጥ አስከሬኑን የተሸከሙት ሰዎች ከውጭ ባሉት ሰረገላ ተሸካሚዎች የእንቅስቃሴ ልክ አረማመዳቸውን በማስተካከል እየተጓዙ እቀብር ስፍራው ይደርሳሉ፡፡ (ቃ.መ. 28/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

#### 4.1.2.4. ጊዜ ቀብር ከዋኔ

በሸካቾ ብሔረሰብ ለቅሶ ማህበራዊ ትስስርን ማጠንከሪያ፣ የሟችን እና የሟች ወገኖችን ማንነት መግለጫ፣ የሀብት መጠን ማሳወቂያ፣ ወዳጅ እና ጠላት መለያ፣. . .ወዘተ ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ በተለይም በቀብሩ ዕለት የሚኖረው ዝግጅት ደመቅ ያለ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ከሟች ወይም ከሟች ቤተሰቦች ጋር እውቂያ ያለው እያንዳንዱ የብሔረሰቡ አባል የትኛውንም አማራጭ ተጠቅሞ በቀብሩ ዕለት የመገኘት ማህበራዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን አምኖ የተቀበለ በመሆኑ በቀብሩ ዕለት የሚገኘው ለቀስተኛ ቁጥር በእጅጉ የበዛ ነው፡፡ ይህ ሀቅ ይበልጡን የሚጎላው ደግሞ ሟች አንድ አይነት ባህላዊ የስልጣን ባለቤት ወይም ታዋቂ ግለሰብ የሆነ እንደሆነ ነው ሲሉ አቶ አምባው (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም) ያስረዳሉ፡፡

የቀብሩ ዕለት ጠዋት፤ ወፍ ከመንጫጫቱ አስቀድሞ በሟች ቤት አቅራቢያ በያቅጣጫው በሚገኙ ከረብታማ ቦታዎች ላይ በመሆን ጥሩንባ በተደጋጋሚ እንዲነፋ ይደረጋል፡፡ ይህን የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች እና ከተለያየ አካባቢ የተሰባሰቡት ለቀስተኞች ወዲያው ነቅተው ወደ ሟች ቤት ጉዟቸውን ያደርጋሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ከዚህን ሰዓት ጀምረው በዕለቱ መረር ያለ ለቅሶ እያደረጉ ከለቀስተኛው ፊት ይገኛሉ፡፡ የሚመጡትም ለቀስተኞች እንደቅርበታቸው ልክ ከሰፈር ጀምረው ከፍ ባለ ድምፅ ያለቅሳሉ፣ ደረታቸውን በሁለቱም እጆቻቸው አምርረው ይደቃሉ፣ እየዘለሉ ይወድቃሉ - ይነሳሉ፣ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፣. . .ወዘተ፡፡ በዚህ መልክ የተጀመረው ለቅሶ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ያለሚቋረጥ በደማቅ ሁኔታ ይቀጥላል፤ የመጣው ለቀስተኛ ሁሉ በከባድ የሀዘን ድባብ ውስጥ ሆነው ከሚያለቅሱት፣ እየወደቁ ከሚነሱት፣ ደረታቸውን በኃይል ከሚደቁት፣ ፊታቸውን ከሚቧጥጡት፣. . .የሟች ቤተዘመዶች ፊት ሲደርስ ከደጅ ጀምሮት የነበረውን ለቅሶ በማጠናከር የሚሆኑትን ሁሉ እየሆነ ሀዘናቸው ሀዘኑ፤ ጉዳታቸው ጉዳቱ መሆኑን ለማስመስከር ይጥራል፡፡

በዚህ ሁኔታ ተጀምሮ ያለማቋረጥ እስከ እኩለ ቀን ድረስ የቀጠለው ለቅሶ ይበልጥ የሚፋፋመው አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ጉዞ ሊጀምር ሲል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አብዛኛው የህብረተሰቡ

አባል መረር ያለ ለቅሶ ያለቅሳል፡፡ ሴት የሟች ቤተሰቦች (በተለይም የሟች እናት፣ ሚስት እና ሴት ልጆች) የመውደቅ የመነሳታቸው ሁኔታ ከሌላው ጊዜ ያይላል፡፡ የሟች ሚስት፣ እናት እና እህቶች በወቅቱ ከሚለብሱት ጥቁር ልብስ ላይ ጣል የሚያደርጉት ከቃጫ የተሰራ "ፋሶ" የተሰኘ ነጭ ካባ መሰል ባህላዊ የሀዘን መግለጫ ይለብሳሉ፡፡ (ምልከታ 2፣ ከ27/06/06 እስከ 02/07/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ)




ፎቶ 8. በሸካቾ ብሔረሰብ ሴት የሟች ቤተሰቦች የሚለብሱት ባህላዊ የሀዘን መግለጫ ልብስ - "ፋሶ"፣

በባህሉ መሰረት ሬሳው ከቤት ወጥቶ ጉዞ ሲጀምር የሚከናወኑ ልዩ ልዩ ስርዓቶችን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከት፡፡

**መውደቅ - መነሳት (ቤኖ)፡-** በሸካቾ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ላይ ዛሬም ድረስ በዋናነት ከሚፈፀሙት ባህላዊ ተግባራት መካከል ድምፅን ከፍ አድርጎ እያለቀሱ በተደጋጋሚ እየወደቁ መነሳት መሆኑን ወ/ሮ ዘውዲቱ አንገሎ እና አቶ ኃይሌ መድራሻ ጠቅሰው እንደሚከተለው በስፋት ያብራራሉ፡፡ ይህን ተግባር በዋናነት የሚፈፅሙት ሴት የሟች ቤተሰቦች እና የቅርብ ወዳጆች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሀዘኑ እጅግ የጎዳቸው ወንዶችም ወድቀው ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ሴቶቹ በሚወድቁ በሚነሱበት ሰዓት ደረታቸውን በእጅጉ እየደቁ፣ ፊታቸውን እየቧጠጡ እና ፀጉራቸውን እየነጩ ነው፡፡ ይህንን የሚያደርጉት በዋናነት በተፈጠረው ክፉ አጋጣሚ እጅጉን ማዘናቸውን ለመግለፅ እና ከእሱ/ ከእሷ ይልቅ እኔ ነኝ መሞት ያለብኝ የሚለውን ስሜት እንዲወክልላቸው

ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሀዘን ስሜታቸውን ለታዳሚው በማጋባት የወገናቸው ለቅሶ የደመቀ እንዲሆን የማድረግ ዓላማም አለው፡፡

መውደቅ መነሳቱ የሚከወነው ቦታ እየተመረጠ ሳይሆን ድንገት በተገኙበት ስፍራ ላይ ስለሚሆን በርካታ ሰዎች ከፍ ላለ ጉዳት የሚጋለጡባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ የሟች የቅርብ ዘመድ ሆነው ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት ካለች፣ ህመምተኞች ቢኖሩ፣ እርጅና የተጫጫናቸው ከሆኑ ወድቀው እራሳቸውን ለጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት ቀደም ተብሎ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሆነው በሚመደቡ ጠንከር ያሉ ሴቶች ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሴቶች እንዲጠብቋቸው የተመደቡባቸው አካላት የመውደቅ አዝማሚያ ሲያሳዩ ከኋላ ሆነው በፍጥነት ወገባቸውን በመያዝ ከአደጋ ሊታደጓቸው ይገባል፡፡ (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ እና ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

**ሙሾ (ያሶ)፡-** በሸካቾ ብሔረሰብ ከሴቶችም ሆነ ከወንዶች መካከል ተመርጠው ወዲያ ወዲህ እያሉ ሙሾ በመደርደር አልቅሰው የሚያስለቅሱ ሰዎች አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ በላይነሽ አርጀፎ "ሙሾ አውራጆች በዋናነት የሚመረጡት ከቤተሰብ አሊያም ከቅርብ ዘመድ መካከል ልምድ ያላቸው ተለይተው ነው፡፡ የሙሾ ደርዳሪዎች (በሸከኛ ለሴት "ያሰቺ"፣ ለወንድ ደግሞ "ያሰቾ" ይባላል) ምርጫ ከቤተሰብ አባላት መካከል እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ከሌላው ይልቅ የሀዘኑ ስሜት በዋናነት የጎዳቸው በመሆኑ የማስለቀስ አቅም ያለው ሙሾ መደርደር ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው" (ቃ.መ. 26/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ሙሾ አውራጆቹ አብዛኛውን ጊዜ ሙሾ የሚደረድሩባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አቶ አምባው ጮሪቶ ሲያብራሩ "ሙሾ የሚደረደረው የሟችን ደግነት፣ ጀግንነት፣ ለሰው አሳቢነት፣. . .ወዘተ በተመለከተ እና የሞትን ጨካኝነት፣ ሞት የማይቀር፤ የሚገልም ሆነ የሚያድን ፈጣሪ መሆኑን፣. . .ወዘተ በሚዳስሱ ጉዳዮች ዙሪያ ነው (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር የተወሰኑ የሙሾ ግጥሞችን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

## ፩. የሟችን ደግነት/ ለጋስነትን የተመለከቱ የሙሾ ግጥሞች

| በሽክኛ | የአማርኛ ትርጉሙ |
|---|---|
| 1. መጮ በጀታቼ | ፈረስ የማይከለክል |
| ገቶ በጀታቼ | የእርሻ በሬ እሚሰጥ |
| ጊጆ በጀታቼ | ለተቸገረ እሚያበድር |
| ሽዎ ቢን ማሄ | አፈር እሱን በላው |
| ተ ሽዎ መመኔ፡፡ | እኔ አፈሩን ልብላለት፡፡ |
| 2. ማጦ ኔቻ ዶኖ | ከደጅ የማያቆመው |
| ማቤ ዮህ ዶኖ | ሲበላ የማያባርረው |
| ቂቲ ታቂቲበን፡፡ | ለደጉ ወዳጄ እኔ ልሙትለት፡፡ |
| 3. ቢ ማጦ ሽፓኖ | ዳዳዋ የማይጎል |
| ቢ ኪሾ ቀጃኖ | እጁ የማይሰስት |
| አሞኔ ኖዬሮ | ምነው ፈጣሪያችን |
| ቢን አሎኔ ኖኒ ኔውጢቶ፡፡ | ደጓን ሴት ቀማኸን፡፡ |

የሽካቾ ብሔረሰብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ በዋናነት ምርጫው የሚያደርገው የጋማ ከብቶችን ነው፡፡ ስለሆነም የቸገረው ሲጠይቅ ፈረሱን የሚያውስ፣ የብሔረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው በጥምር ግብርና እንደመሆኑ መጠን ለእርሻ የሚያቀናጀው በሬ አጥቶ ሲጠይቅ ፊቱን ሳያጠቁር የሚሰጥ እና ለተቸገረ የሚያበድር ሰው ሲሞት በተራ ቁጥር 1 ላይ በቀረበው መልኩ ሙሾ በመደርደር ማልቀስ የተለመደ ተግባር መሆኑን አቶ መንገሻ አለሙ (ቃ.መ. 27/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ) ያስረዳሉ፡፡

በተራ ቁጥር 2 ላይ የተመለከተውን የሙሾ ግጥም አስመልክቶ ደግሞ አቶ አምባው ማን፣ እንዴት እና በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ሁኖ ሊደረድረው እንደሚችል እንደሚከተለው በዝርዝር ያብራራሉ፡፡

የመንጃ ጎሳ ከሽካቾ ብሔረሰብ በርካታ ጎሳዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ጎሳ ቀደም ባለው ጊዜ በብሔረሰቡ ዘንድ ከኃጢያቶችም ሁሉ የከፋ፣ የወንጀል ሁሉ ጥግ ተደርጎ የሚቆጠረውን የሰው ነፍስ የማጥፋት ተግባር ፈፅሟል ተብሎ በመታመኑ ከብሔረሰቡ ተገልሎ እንዲኖር ተፈርዶበታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ሲያገላቸው ይስተዋላል፡፡ ይሄንን ፍርድ በመቀበል መንጃዎች እራሳቸውም ተገልለው መኖርን ምርጫቸው ያደርጋሉ፤ በሌሎቹ የሸካቾ ጎሳዎች ቤት አይገቡም (ግቡ ቢባሉ እንኳ ፍቃደኛ አይሆኑም)፣ ምግብ በሰሀን ቢሰጣቸው ቅጠል ላይ እንዲገለበጥላቸው አድርገው እንጂ ሌሎቹ በሚመገቡበት ለመመገብ አይደፍሩም፣ ሌሎች ጋር ሲያወሩ አይናቸውን መሬት ላይ ተክለው ማውራትን ይመርጣሉ፣. . .ወዘተ፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ አላስችል ያላቸው የሌላው ጎሳ አባላት እነዚህን ሰዎች በማግባባት ከቤታቸው ገብተው አብረዋቸው እንዲበሉ እና እንዲጠጡ የሚያደርጓቸው፣ ሲቸገሩ የሚረዷቸው ሆነው ሳለ በሞት ሲነጠቋቸው መንጃዎቹ በለቅሷቸው ላይ ተገኝተው በመረረ ለቅሶ አጅበው በተራ ቁጥር 2 የተመለከተውን አይነት ሙሾ ይደረድሩላቸዋል፡፡ (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በተራ ቁጥር 3 ላይ የቀረበው የሙሾ ግጥም በይዘት ከቀደሙት ሁለቱ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ይህኛው የሚደረደረው በሴቶች የለቅሶ ስርዓት ላይ ነው፡፡

### ፪. ያለጊዜው ለሞተ ሰው የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች

| በሽከኛ | የአማርኛ ትርጉሙ |
|---|---|
| 1. ቂቶስ ቤዳኖ | ሞት የማይገባዎት |
| ቂቲዮኔ አካ | ለምን ይሞታሉ |
| ቂቶቴ ቤቶ፡፡ | ሞት የሚገባኝ እኔ እያለሁ፡፡ |
| 2. ባቄሎ አበቤ | ባቄላው አብቦ |

| | |
|---|---|
| ከሎ ከሾ ጌዴ | አተሩ ደርሶ |
| ማታኖ ሀመኔ | ሳትበላው ቀረህብኝ |
| ማታኖ ሀምበኔ፡፡ | ምነው ለኔ ባደረገው፡፡ |

አቶ አዴሎ ሻጫቸው እንደሚያስረዱት "የዕድሜ መግፋት ሳይሆን የሀጢያት መብዛት የሰውን መሞቻ ታቀርባለች የሚል ፅኑ እምነት ያለን በመሆኑ አንድ በደግነቱ የሚታወቅ ሰው የቱንም ያህል ዕድሜው ገፍቶ ቢሞት ከነደግነቱ መሞቱን ለመግለፅ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የቀረበውን እና መሰል ሙሾ በመደርደር ሀዘናችንን መግለፅ የለመድነው ተግባር ነው፡፡" (ቃ.መ. 29/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ) መሆኑን ነው፡፡ በተራ ቁጥር 2 ላይም የቀረበው የሙሾ ግጥም ያለጊዜው መቀጨቱን የሚያመለክት ነው፡፡

## ፫. የሞትን ጨካኝነት የሚገልፁ የሙሾ ግጥሞች

| በሸከኛ | የአማርኛ ትርጉሙ |
|---|---|
| 1. አቦ ቂቶን ተቤኤና | አወይ ሞትን ባየኋት |
| ሾኪና ኮዬና | በጦሬ በወጋኋት |
| ሾቾና ጬየና፡፡ | ባለንጋ በገረፍኳት፡፡ |
| 2. ተማራኖ ቂቶ፣ ተማሮ ውጢጋ | ያልተማረው ሞት፣ የተማረ ሲገል |
| ማ ሚሳኖ ቂቶ፣ ማሀኖ ውጢጋ | የማይጠግበው ሞት፣ ያልበላውን ሲገል |
| ቢ ፊርዶ ሊክ አሎ፣ ኮባ ከሾቪበት፡፡ | ለተዛባው ፍርዱ፣ ለማን አቤት ልበል፡፡ |

ከፍ ሲሉ የቀረቡት ሁለት የሙሾ ግጥሞች ከላይ ስንመለከታቸው በቀጥታ ግኡዙን ሞት የሚነቅፉ፣ የሚከሱ፣ የሚወቅሱ እንዲያም ሲል በሞት ላይ የሚፎክሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይሁን እንጂ ውስጣቸውን ስንመረምር ግጥሞቹ በስመሀዳሪ ዘይቤ የቀረቡ እንደሆኑ እንረዳለን፤ ሞትን ጠርቶ ሞትን ከሰው ልጅ ጋር ያስተሳሰረውን ፈጣሪን ማሰብ እንዲቻል ሆን ተብሎ በዞርታ የተበጀ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በመሆኑም ከላይ እንዳየነው እየተወቀሰም ሆነ እየተገሰፀ ያለው፣

እየተፎከረበትም ሆነ እየተሸለለበት የሚታየው በስሙ እየተጠራ ያለው ሞት ሳይሆን ሞትን ፈጠረ ተብሎ የሚታሰበው ፈጣሪ ላይ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

እንዲህ አይነት ሙሾዎችን ለመደርደር፤ ከፈጣሪ ጋር ለመጋፈጥ ከፍ ባለ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ መሆንን አሊያም በመራር ሀዘን ውስጥ መከተትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም የቀደሙት ግጥሞች የነቁት ከፍ ካለ የሀዘን ስሜት ውስጥ ነው እሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል፡፡

### ፬. ሞት የማይቀር፤ የሚገልም ሆነ የሚያድን ፈጣሪ መሆኑን የሚያወሱ የሙሾ ግጥሞች

| በሸክኛ | የአማርኛ ትርጉሙ |
|---|---|
| 1. ፈሊ ቤቶ የሪ | ይገላል ያድናል፣ |
| ውጢ ቤቶ የሪ | ይፈጥራል ያጠፋል |
| አሞስ ኖ ኤፒዮ | ይህ ምኑ አዲስ ሆኖ |
| አሞኔ አንዲሮ፡፡ | ሰው ሁሌም ያለቅሳል፡፡ |
| 2. አንዲሮ አሎኔ ቂቶ ኖቃቦኔ | ሞት የነበረና ያለ የሚኖር ነው |
| ኮስ ተገቲ ጋታ ቢን ታስ ቆለሄ፡፡ | የዛሬውን ብቻ ቢምርልኝ ምነው፡፡ |

ሞት የነበረ፣ ያለና የሚኖር መሆኑ ለሁሉም ግልፅ ቢሆንም የሰው ልጅ ሁሌም ሞት በማህበሩ ውስጥ ሲከሰት አምርሮ ከማልቀስ ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ይህ የሚሆነው፤ ዛሬ አልቅሶ ሙቱን የሚሰናበተው ነገ የሚለቀስለት መሆኑ ጠፍቶት ሳይሆን የሰው ልጅ ካለው ማህበራዊ መስተጋብር አኳያ መጉደልን የሚሻ ባለመሆኑ ነው፡፡ አስቀድመን ያየናቸው ሁለት የተለያዩ የሙሾ ግጥሞችም የሚያስረግጡልን ይህንኑ እውነት ነው፡፡

**ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን (ጎሞ)፡-** የ"ጎሞ"ን ምንነት አቶ ስለሺ ጫሊቶ ሲያስረዱ "በእኛ ብሔረሰብ ባህል መሰረት የሟች ወገኖች በመራር ሀዘን እራሳቸውን ለከፋ አደጋ አሳልፈው እንዳይሰጡ፣ ቀጣይ ህይወታቸው ሀዘን የበዛበት ሆኖ እንዳይቀር፣ ከሀዘን በተቃራኒ ደስታ መኖሩን ለማስገንዘብ፣. . .ወዘተ በቀብሩ ዕለት በስፋት የሚከወን ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን ነው፡፡" (ቃ.መ. 28/06/06 ዓ.ም፣ ማሻ) በማለት ነው፡፡

ጎሞ ፍፁም ተቃርኗዊ በሆነ መልኩ በለቅሶ ስርዓት ወቅት የሚከወን ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን ነው፡፡ ይህ ዘፈን እሚከወነው ለቀስተኞች ወንዱ በአንድ ወገን ሴቱም በሌላኛው ወገን ተቧድነው ክብ በመስራት የሟች ወገኖች ሊያፅናና የሚችል ዘፈን እየዘፈኑ ነው፡፡ የወንዶቹ ቡድን ጦር እና ጋሻ ይዞ፣ በከበሮ፣ በጡርንባ እና በክራር በመታገዝ ባህላዊ ዘፈኖቹን እየተቀኘ ደማቅ በሆነ አከዋወን ይወጣዋል፡፡



ፎቶ 9. የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የወንዶች የማፅናኛ ዘፈን አከዋወን፣

ሴቶቹም በፊናቸው ባህላዊ የሀዘን ልብስ ለብሰው በከበሮ እና በጭብጨባ ከታጀበው ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን ይታደማሉ፡፡



ፎቶ 10. የሸካቾ ብሔረሰብ የሴቶች ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን አከዋወን፣

በወንዱም ሆነ በሴቱ የሚደራጀው ቡድን በርካታ ሲሆን በአንድ ቡድን ውስጥ እንደሁኔታው አስርም ሆነ ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ተቧድነው ሰልታዊ በሆነ መልኩ በሚቃኘው ጭበጨባ እያተገዙ ወደ ላይ ዘለል ዘለል እያሉ ነው የሚጨፍሩት፡፡ አንዳንዴም ተቧዳኞቹ ወንዶች ከሆኑ በአንድ እጃቸው ጦር ይዘው በሌላኛው እጃቸው እርስ በእርስ በመያያዝ ወዲያ - ወዲህ፣ ላይ - ታች እያሉ ሲጨፍሩ ቆይተው ዘፈኑን ሲቋጩ አንድ ላይ በእግራቸው መሬቱን በከበሮ ስልት ረግጠው ሲያርፉ የታዳሚን ቀልብ ይማርካል፡፡ ሴቶቹ ደግሞ ከመያያዝ ይልቅ ክብ ሰርተው ደመቅ ባለ ጭብጨባ እና በከበሮ እየታገዙ በወንዶቹ ስልት ላይ ታች እያሉ ክብ እየሰሩ መጨፈርን ምርጫቸው ያደርጋሉ፡፡ (ምልከታ ፲፣ ከ20 - 24/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ)

በዚህ ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን ውስጥ እነማን እንደሚሳተፉ አቶ ኃይሌ መድራሻ እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

> ይህንን ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን እና ጭፈራ ከሟች ቤተሰቦች፣ እርጅና አብዘዝቶ ከተጫናቸው አዛውንቶች እና በደዌ ከተያዙ ሰዎች በስተቀር ሁሉም በሚችለው ልክ እንዲጨፍር ይጠበቃል፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገበትም ምክንያት ለቀስተኛው እዚያ የተገኘው ሀዘንተኞችን ለማፅናናት በመሆኑ በባህሉ መሰረት ሁሉን አቀፍ ማፅናኛ ተደርጎ በሚቆጠረው ስርዓት ላይ በመዝፈን፣ በማጨብጨብ፣ ከበሮ በመምታት፣ ክራር በመጫወት፣ ጥሩንባ በመንፋት፣ ጦር በመስበቅ፣. . .ወዘተ የሚጠበቅበትን ማህበራዊ ግዴታ ሊወጣ ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ያልፈለገ ቢኖር ግን አንድም ከሟች ወይም ከሟች ወገኖች ጋር ከፍ ያለ ቅያሜ ያለው ተደርጎ ይቆጠራል፤ በሌላ መልኩም ለቅሰውን ካልደረሱት አካላት እኩል ሊቆጠርም ይችላል፡፡ (ቃ.መ. 04/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በወንዶቹ የጎሞ ጭፈራ ወቅት ከተቻለ በየቡድኑ ካልተቻለ ግን የተገኘውን ያህል ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈኑን በክራር እየታጀቡ በአግባቡ ማውጣት የሚችሉ ባህላዊ ዘፋኞች አስቀድመው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ ዘፋኞች ከቀብሩ አስር ቀን ቀደም ተብሎ የሚነገራቸው በመሆኑ ከሁኔታው ጋር የሚስማሙ ልዩ ልዩ የማፅናኛ ዘፈኖችን አስቀድሞ በመፍጠር፣ በዕለቱ ድንገት ከሚፈጠሩ አንዳንድ ሁኔታዎች ጋር አያይዘው በመግጠም የተጣለባቸውን ሙያዊ ግዴታ ይወጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከታዳሚያኑ መካከል የሚቀርብላቸውንም ግጥም በክራር አስደግፈው ስሙም አድርገው የሚያቀርቡበት ሁኔታም አለ፡፡

የጎሞ ዘፈን እና ጭፈራው የሚጀምረው እኩለ ቀን ላይ አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ጉዞ ሲጅምር ታዳሚው ሁሉ ቀኑን ሙሉ ሲያለቅስ ከነበረው ይልቅ ከግማሽ ሰዓት በላይ አምርሮ ካለቀሰ በኋላ ነው፡፡ ለቅሶው በዚህ ሁኔታ መረር ብሎ መቀጠሉን ያስተዋሉት አዛውንቶች በየአልቃሾቹ መሀል እየዞሩ ያስቆሟቸዋል፡፡ ለቅሰው እንዳበቃ ወደ መቃብር ስፍራ በሚወስደው መንገድ ላይ አስቀድሞ ከተዘጋጀ ሜዳ ላይ ሲደርሱ የጎሞ ስርዓቱ ይጀምራል፡፡

የጎሞ ስርዓቱ የሚጀምረው ሟቹ ንጉስ፣ የጎሳ መሪ፣ አዳኝ፣ በተለያዩ ማህበራዊ መለኪያዎች ጀግና፣ ኑሮን በትግል አሸንፎ ሲኖር የነበረ፣. . .ወዘተ ከሆነ ጦር በቀኝ ጋሻ በግራ እጃቸው ይዘው ወዲያ ወዲህ እያሉ በመፎከር እና በመሸለል ሞትን በያዙት ባህላዊ መሳሪያ እያስፈራሩ ያሉ የሚመስሉ ሰዎች በሚከውኑት ትርዒት ነው፡፡



ፎቶ 12. የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን (ጎሞ) ስርዓት አጀማመር፣

በዚህ መልክ የሚጀመረውን የጎሞ ስርዓት ለቀስተኛው ሁሉ አንድ በአንድ ክብ ሰርቶ መታደም ይጀምራል፡፡ በከዋኔው ሂደት ታዳሚው ሞት የተወጋ ያህል ከለቅሶ መልስ የፈገገ ፊት እያሳየ በጭብጨባ ያደምቀዋል፡፡ ለከዋኝነት የሚመረጡት በአካባቢው በጀግንነታቸው የተመሰከረላቸው ሰዎች ስለሚሆኑ ታዳሚው እግረ መንገዱን ለከዋኞቹ የጦር አሰባበቅ እና አፎካከር ሂደትም ድጋፉን ያሳያል፡፡

በዚህ ወቅት በባህላዊ ጌጦች ያሸበረቁ ፈረሶችን የያዙ ሰዎች ወደ ትርዒቱ በመቀላለቀል ፈረሶቹን ወዲያና ወዲህ እያንጎማለሉ ለሟች ጀግንነት ተጨማሪ ምስክርነታቸውን በድርጊት ይገልፃሉ፡፡ በመቀጠልም ክራር የያዙት ባህላዊ ዘፋኞች ቅኝታቸውን ማሰማት ይጀምራሉ፡፡ በዚህን

ጊዜ ታዳሚው ወዲያውኑ መቧደን ስለሚጀምር ባህላዊ ዘፋኞቹ በየቡድኑ አንዳንድ እየተዘሩ ክዋኔውን ማድመቅ ይጀምራሉ፡፡ ሴቶችም ለብቻቸው ተቧድነው በከበሮ እና በጭብጨባ በመታገዝ ደመቅ አድርገው እየጨፈሩ የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊ ግዴታ መወጣት ይጀምራሉ፡፡ (ምልከታ 2፣ ከ27/06/06 ዓ.ም እስከ 02/07/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ)

ሟች ሴት ከሆነች ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የክዋኔ አይነቶች ጦር እና ጋሻ ይዘው የሚፎክሩት፣ ፈረስ አስጊጠው ላይ እና ታች የሚሉት ይቀርና በሴቶች ብቻ የሚከወን "ሽሬ የጦ" (ግማሽ አካሉ መሬት ውስጥ የተቀበረን ጋን በሰፌድ እየመቱ የመስበር ስርዓት) በተሰኘ ክዋኔ ይተካል፡፡ ይህን ተግባር የሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑ እና "ከእጇ በልቻለሁ፣ ጠጥቻለሁ !" የሚሉ ሴቶች ከብ ሰርተው ቀደም ተብሎ የኀሞ ስርዓቱ በሚከናወንበት ቦታ ላይ የተዘጋጀን ጋን ባህላዊ የማፅናኛ ዘፈን ግጥሙን እየደረደሩ ተራ በተራ በያዙት ሰፌድ ጫፉን እየመቱ የጋኑን አፍ ይሰብራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በዙሪያቸው የተሰበሰቡ ሴቶች ከፍ ባለ ድምፅ እና በከበሮ ታጅበው የማፅናኛ ዘፈኑን በድምቀት ይወጡታል፡፡ (ምልከታ 1፣ ከ20 - 24/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ)

ይህ "ሽሬ የጦ" የተሰኘው ተግባር ለምን እንደሚከወን ወ/ሮ ዘውዲቱ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> አንድ ሴት ትዳር መስርታ የራሷን ኑሮ መምራት ከጀመረች በኋላ ስትሞት ከእጇ የበሉ እና የጠጡ ሴቶች ሀዘናቸውን የሚገልፁት እሷ በህይወት ሳለች ትጠቀምበት የነበረውን አንድ የጠጅ/ የጠላ መጥመቂያ ጋን እየተቀባበሉ አፉን ሲሰብሩ ነው፡፡ ይህ የሚሆነውም 'ሟች ለተቸገረ የምታበላ፣ የምታጠጣ ደግ እና ሞያተኛ ነበረች፣ ዛሬ ግን አፈር በላት' የሚለውን ለማመልከት ሲሆን ከሌሎቹ ዕቃዎቿ ይልቅ ጋን የሚመረጠውም በአካባቢው ጠጅ በአግባቡ የመጣል ብቃት ከሙያዎች ሁሉ የሚሞገስ በመሆኑ ነው፡፡ (ቃ.መ. 25/06/06 ዓ.ም፣ አበሎ ቀበሌ)

በዚህ መልክ የተጀመረው ክዋኔ ለሁለት ሰዓት ያህል ያለሟቋረጥ ቀጥሎ በሽማግሌዎች በቃ ባይነት እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ልክ የኀሞ ስርዓቱ እንዳበቃ ጉዞ ወደ ቀብር ስፍራ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ሟች አንድ አይነት ማህበራዊ ስልጣን ያለው ከሆነ ቀብሩ የሚፈፀመው ለእነዚህ አካላት ታስቦ በተዘጋጀ አካባቢ ስለሚሆን ሴቶች ወደ መካነ መቃብሩ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡ አሁን አሁን ግን "ሀዘናችን በአግባቡ የሚቆርጥልን ሲቀበር ስናይ ነው" በሚል

ሴቶች ወደ ተከለከለው ስፍራ ባህላዊውን ደንብ ተላልፈው እየገቡ መሆናቸውን አቶ መንገሻ አለሙ (ቃ.መ. 27/06/06 ዓ.ም፣ ይና ቀበሌ) ይጠቅሳሉ፡፡

ልክ የቀብር ቦታው ሲደርሱ ቀደም ሲል አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ በነበረው ልክ አምርረው ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ የቀብር አፈፃፀም ሂደቱን በሚገባ የሚያውቁት አካላት አስከሬኑን ከመሸከሚያው አውርደው ወደ ተዘጋጀለት ጉርጓድ ውስጥ በጥንቃቄ የማስገባቱን ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከቀደሙት ጊዜያት በበለጠ መልኩ ከፍ ባለ ድምፅ እና በምሬት ማልቀሱ፣ መውደቅ - መነሳቱ፣ ደረት መድቃቱ - ፊት መቧጠጡ፣ . . .ወዘተ በስፋት ይከወናል፡፡ ከሟች ጎሳ አባላት መካከል በዕድሜ ገፋ ያሉት አዛውንት የመጀመሪያውን አፈር ወደ አስከሬኑ በመጨመር አፈር የማልበሱን ሂደት ያስጀምራሉ፡፡ ወንዶቹ በመተጋገዝ አፈር በመጨመር ጉርጓዱን ከሞሉት በኋላ በስተመጨረሻ በድንጋይ ጥቅጥቅ አድርገው በመድፈን ግብዓተ መሬቱን ይፈፅማሉ፡፡ (የተ.ቡ.ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

#### 4.1.2.5. ድህረ ቀብር ክዋኔ

የሸካቾ ብሔረሰብ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን እና ማህበራዊ ትስስሩን ከሚገልፅባቸው አጋጣዎች መካከል ልደት፣ ሰርግ እና ሞት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የለቅሶ ስርዓት በብሔረሰቡ ዘንድ ለእነዚህ ሁነቶች ደምቆ መታየት ዋንኛ አጋጣሚ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ የለቅሶ አጋጣሚ ላይ የሟችን ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ማህበራዊ መስተጋብር መሰረት አድርጎ ሰፋ ያለ ቅድመ ዝግጅት ሊደረግ የሚችልበት ከ 1 ወር እስከ 3 ወር የሚፈጅ ጊዜ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ ቀደም ሲል ዝግጅታቸውን አስመልክቶ በቅድመ ቀብር ጊዜ ክዋኔ ወቅት በዝርዝር የተመለከትናቸው ምግብ እና መጠጦች ለታዳሚው የሚቀርቡበት በዚሁ ከቀብር በኋላ ባሉት ጊዜያት ነው፡፡ የምግብ እና የመጠጥ ስርዓቱን በተመለከተ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አባላት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> እያንዳንዱ ለቀስተኛ የመጣበትን አቅጣጫ መሰረት አድርጎ በተዘጋጀለት ሰፋ ያለ ዳስ ውስጥ በአስተናባሪዎች አማካይነት እጅ እና ፊቱን እየታጠበ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ወዲያውኑ በእሳት ለብ ባለ የቆጮ ቅጠል የተሰራ ሰሀን መሰል ነገር ለእያንዳንዱ ይታደላል፡፡ ከዚያም በአስተናጋጆች አማካኝነት ገሚሱ ቆጮውን አስቀድሞ ሲያሲዝ ሌላዋ ወጥ ለእያንዳንዱ እያደረገች ታልፋለች፡፡ ተከታዩ አስተናጋጅ ደግሞ ከቀርቀሀ በተዘጋጀ "ዶሎ" በተሰኘ ባህላዊ መጠጫ ጠጅ/ ጠላ እየቀዳ ማደሉን ይያያዛል፡፡ በዚህ መልክ

የተጀመረውን የምግብ እና የመጠጥ ፕሮግራም የሟች ቤተሰቦች እና የአካባቢው ሽማግሌዎች ከተመደቡት አስተናጋጆች ጋር እየተሰባጠሩ በየዳሱ በመዞር አስተዛዛኞቻቸውን ብሉልኝ ጠጡልኝ ከማለት አይቦዝኑም፡፡

ሁሉም ሰው የሚበቃውን ያህል ከበላ እና ከጠጣ በኋላ ቡና ለሚፈልግ ቡና ለማይፈልግ ከቡና ቅጠል የሚዘጋጀው ጨሞ ከባቄላ ወይም ከበቆሎ ቆሎ ጋር እንዲቀርብለት ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም በሽማግሌዎች አስተባባሪነት ሁሉም "የሪ ቢ ከሾ ማሪቤ" (ፈጣሪ ነፍሱን ይማር) ብለው የፕሮግራሙ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ ከሩቅ የመጡት እና የቅርብ ዘመዶች እዚያው እንዲያድሩ ሲደረግ ሌሎች ግን ወደ ቤታቸው ሄደው በተመቻቸው ሰዓት እየመጡ ያስተዛዝናሉ፡፡ (የተ.ቡ.ው. 05/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

ከቀብር በኋላ ትኩረት ተሰጥቶት ስለሚፈፀመው ሌላኛው ተግባር አቶ አምባው ጮሪቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

በባህላችን በሌሎች ዘንድ 'ሰልስት' በሚል የሚከበረው ስርዓት በአራተኛው ቀን በደማቅ ሁኔታ ነው የሚከበረው፡፡ በዚህ ቀን ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤት እና ጓደኞች ወፍ ሳይንጫጫ ከያሉበት በሟች ቤት ተሰባስበው ወንዶች ጦር፣ ሴቶች ደግሞ የቆጮ መቁረጫ ቢላቸውን በመያዝ ወደ ቀብሩ ስፍራ ይጓዛሉ፡፡ እዚያ እንደደረሱም ሁሉም ከ30 ደቂቃ ላላነሰ ጊዜ በጣም አልቅሰው ሴቶች በያዙት ቢላዋ በአቅራቢያቸው ካለ ቆጮ ቅጠል እየቆራረጡ፣ ወንዶቹ ደግሞ በጦራቸው መሬት እየወጉ በጋራ `ደፒዮ - ዳፒዮ ኤሰቤ' (ከዚህ በኋላ ሞት እኛን መግደሉን ያቁም፣ ሞት በዚሁ ይብቃ !) በማለት ለቅሶዋቸውን ያሳርጋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሀዘንተኛው ሁሉ እጁን እና ፊቱን ታጥቦ በሟች ቤት የተዘጋጀውን ምግብ በመቅመስ ሀዘኑን ይፈፅማል፤ የነበረበትን ዳስ እና ለአስከሬን የተሰራውን ቤት በማፍረስ ሁሉም እራሱን ለስራ ያዘጋጃል፡፡ ይህ ስርዓት በእኛ ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ቀብሩ ቀን ሁሉ ከፍ ያለ ትኩረት የሚሰጠው በመሆኑ በተለያየ ምክንያት በቀብሩ ዕለት ያልተገኘ ሰው በዚህ ዕለት ደርሶ ሀዘኑን በመግለፁ በቀብሩ ዕለት ባለመድረሱ ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው ቅሬታ ይወገድለታል፡፡ አራተኛው ቀን የተመረጠውም እንደዛሬው መንገድ በየአካባቢው ከመስፋፋቱ በፊት የእኛ ህዝብ ሰፍሮ የሚገኝበት አካባቢ ጥቅጥቅ ያለ ደን የሚበዛበት እና ኮረብታማ በመሆኑ ሁሉም ለቀስተኛ በቀብሩ ዕለት ከያለበት ተሰባስቦ መገኘት ባይቻለው በዚህ ቀን ደርሶ ሳይመቸው እንዲ

ሆን ብሎ አለመሆኑ ከግምት ውስጥ እንዲገባለት የሚያደርግበትን እድል ለመፍጠር እና ሀዘኑ ሞት ከተፈጠረ በኋላ ከ1 እስከ 3 ወር ድረስ ሊቆይ የሚችል በመሆኑ ቀብሩ ከተፈፀመ ከአራተኛው ቀን በኋላ ሁሉም ወደቀድሞ ስራው መመለስ ይኖርበታል ብለው አባቶች በደነገጉት ደንብ መሰረት ነው፡፡ (ቃ.መ. 03/07/06 ዓ.ም፣ ማሻ)

በአራተኛው ቀን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ በሟች መቃብር ላይ ተገናኝተው ዘመድ አዝማዱ አልቅሶ ከመለያየቱ በፊት በመካነ መቃብሩ የነበራቸውን ቆይታ የሚፈፅሙት በመቃብሩ ላይ አስቀድመው ያዘጋጁትን የተለያዩ ዛፎች ችግኝ በመትከል እና አካባቢውን በማፅዳት ነው ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ስር ከሚገኙት 56 ያህል ብሔረሰቦች መካከል አንዱ በሆነው የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ አተኩሮ የተሰራ ነው፡፡ የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ የነበረው "የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜው ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት ማሳየትና መተንተን ነው፡፡" በመሆኑም ይህን ዓላማ እና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በሁለት ተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ፣ ስለ ብሔረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ ካላቸው የተለያዩ አካላት ጋር ቃለ-መጠይቅ እና የቡድን ውይይት በማካሔድ በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡

የተገኙት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል በአግባቡ ለማሳየት ይበጅ ዘንድ "ለህፃናት የሚደረግ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት"ን እና "ለአዋቂዎች የሚደረግ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት"ን በቅድመ ሞት እና ጊዜ ሞት እንዲሁም በቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብር እና ድህረ ቀብር በሚሉ እርከኖች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ቅድመ ሞት በሚለው እርከን ውስጥ ብሔረሰቡ አንድ ሰው ለሞት የተቃረበ መሆኑን ሲገምት የሚያከናውናቸውን ልዩ ልዩ ባህላዊ ተግባራት የሚመለከት ሲሆን በጊዜ ሞት ስር የቀረቡት ደግሞ አንድ ሰው ህይወቱ ስታልፍ የሚፈፀሙ ክንውኖችን የሚያሳይ ነው፡፡ በሸካቾ ብሔረሰብ ዘንድ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በየደረጃው የሚከናወኑ ባህላዊ ተግባራት ደግሞ በቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ሞት ክዋኔ ስር ተተንትነዋል፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ አጠቃላይ ሂደት ከአንድ ወር እስከ ሦስት ወር ድረስ ሊፈጅ እንደሚችል በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ይህ ጊዜ አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ ያሉትን የመታሰቢያ ቀናቶች የሚያካትት ሳይሆን ሟች በብሔረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ደረጃ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ባገናዘበ መልኩ ከቀብሩ በፊት ለሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ባህላዊ ስርዓቶች መከወኛ የሚሆን መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህ ወቅት ከሚፈፀሙ ባህላዊ ስርዓቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት በየአካባቢው ያሉ የብሔረሰቡ ተወላጆች በቀብሩ ዕለት ወገናቸውን ተገኝተው እንዲቀብሩ ለማስቻል፣ ለዝግጅት ከወር በላይ የሚፈልገውን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ

ለለቀስተኞች ለማዘጋጀት፣ በሟች ማሳ ውስጥ መፈፀም ያለባቸውን የእርሻ ስራዎች ለማከናወን፣. . .ወዘተ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በእርግጥ እድሜ፣ ፆታ እና ማህበራዊ ደረጃ በብሔረሰቡ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚፈጥሯቸው የተወሰኑ ልዩነቶች መኖራቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም ሟች የአካባቢው ንጉስ፣ የጎሳ መሪ ወይም ባለቃልቻ ከሆነ ከሌላው ህብረተሰብ ለቅሶ ይልቅ ሰፋ ባለ እና በደመቀ መልኩ እንደሚከወን ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህም በላይ ዋንኛው የልዩነት ምንጭ ሟች ወይም የሟች ቤተሰብ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንደ ብሔረሰቡ አባላት እምነት የአንድ ሰው የለቅሶ ስርዓት የሚደምቀው ከቀብሩ በፊት በሚሰናዱት ዝግጅቶች ልክ ነው፡፡ ከዝግጅቶቹ መካከል ደግሞ የሌሎች ቅድመ ዝግጅቶችን ስፋት እና ጥበት የመወሰን አቅም ያለው ለለቀስተኞች የሚሆንን ምግብ እና መጠጥ በስፋት ማዘጋጀት ነው፤ ለዚህ ዝግጅት ከሚያስፈልገው በርከት ያለ ቆጮ በተጨማሪ ለቆጮው ማባያ የሚሆን ስጋ ይመጣል ተብሎ በሚገመተው ሰው ልክ ታርዶ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ወይ ሟች አሊያም ቤተሰቦቹ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ከፍ ያለ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ አቅም ለለቅሶ ስርዓቱ ድምቀት ወይም መደብዘዝ ከፍ ያለ ሚና የሚጫወት መሆኑ ታውቋል፡፡

በብሔረሰቡ ባህል መሰረት አንድ ህፃን ጥርስ ከማብቀሉ በፊት የሚሞት ከሆነ የለቅሶ ስርዓቱ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በእጅጉ የሚለይ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሽካቾዎች ዘንድ አንድ ህፃን ከእናቱ እቅፍ ሳይወርድ በሞት የተነጠቀ እንደሆነ "ህፃኑ ኃጢያተኛ ስለሆነ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለመረጠው ነው የወሰደው፡፡" የሚል ፅኑ እምነት አለ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ህፃን አይለቀስም፣ ደረት አይደቃም፣ ፊት አይቧጠጥም፡፡ ይልቁንም ብዙም ሰው ሳይሰማ ጎረቤታሞች ብቻ ተሰባስበው እናት እርሟን ለማውጣት ያህል ብቻ ድምፅ ሳታሰማ አልቅሳ እንድትሰናበተው አድርገው የህፃኑን አስከሬን ዛፍ ቦርቡረው የሚቀብሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ የሚሆነው ልጁ መሬት ከተቀበረ እናት ዳግመኛ ልጅ አትወልድም ተብሎ የሚታሰብ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው በጥናቱ የተደረሰበት መሰረታዊ ነገር የሽካቾ ብሔረሰብ በቀብሩ ዕለት የሚፈፀመውን መሪር ሀዘን የሚያሳርገው "ጎሞ" በተባለ ባህላዊ ዘፈን እና ጭፈራ ነው፡፡ ይህ ጭፈራ የሟችን እና የቤተሰቦቹን መልካም ገፅታዎች የሚያወሱ፣ ሞት ለሁሉም የቀረበ ግዴታ መሆኑን የተመለከቱ፣ ሞት ዳግም የሟችን ቤተሰቦች እንዳይጎበኝ የሚመኙ፣. . .ወዘተ ግጥሞችን ለቀስተኞቹ እየደረደሩ በከበሮ፣ ክራር እና ጥሩንባ ታጅበው በመጨፈር የሟችን ቤተሰቦች ሀዘን

እንዳይጎዳቸው የማድረግ ዋንኛ ዓላማ ያለው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም "ሞት ሀዘን ሲበዛ ተደጋግሞ የሚመጣ በመሆኑ ሀዘኑ በቅቶን መደሰት ጀምረናል" የሚል መልዕክት እንዲያስተላልፍም ታስቦ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ አዋቂዎች ቀብር የሚፈፀመው በሁለት የተለያዩ አካባቢዎች ነው፡፡ አንደኛው በሟች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ የሟች ማሳ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች በጋራ ተስማምተው ኮረብታማ ስፍራ ላይ የሚያሰናዱት ነው፡፡ በሁለቱም መካነ መቃብሮች ቀብር በሚፈፀምበት ወቅት በርከት ያሉ ዛፎችን በመቃብሩ ዙሪያ መትከል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የህብረተሰቡ የአኗኗር ይትባህል በመሰረታዊነት ደንን የሚፈልግ ከመሆኑ ጋር በመዳመር የአለም የባህል እና ቅርስ ጥበቃ ተቋም (UNESCO) በ2005 ዓ.ም የሸካን ደን ከአለም ጥብቅ የደን ሀብቶች አንዱ አድርጎ እንዲመዘግበው ማስቻሉን ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

የሸካቾ ብሔረሰብ ማህበራዊ ትስስሩን ከሚያጠነክርባቸው እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ከሚገልጥባቸው ባህላዊ ክዋኔዎቹ መካከል "የለቅሶ ስርዓት" ቀዳሚውን ስፍራ እንደሚይዝ ታውቋል፡፡ ባህላዊው የለቅሶ ስርዓት የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ እሴቶች የሚገለጡበት፣ የሚፀኑበት እና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉበት ሁነኛ መድረክ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች

ሕይወት አበሩ፡፡ "የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2003 ዓ.ም፡፡

ማናዬ እንግዳወርቅ፡፡ "በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ንፅፅራዊ ጥናት፡፡" በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡

ምህረት ካሳ፡፡ "የሸከቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና አመጋገብ ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡

ሞገስ ሚካኤል፡፡ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሔድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡

ስለሺ አባተ፡፡ "የሸከቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡

ተሾመ ሙሉጌታ፡፡ "በቤንሻንጉል ጉምዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1998 ዓ.ም፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ “ መጽሃፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዘወገበ ቃላት ሀዲስ”፡፡ 1948 ዓ.ም፡፡

አማረ ሞላ፡፡ “የሸካቾ ብሄረሰብ ሃገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና፡፡” በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1999 ዓ.ም፡፡

አስቴር አንጀሎ፡፡ "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1997 ዓ.ም፡፡

አቡበከር ሀሰን፡፡ "የሺናሻ ብሔረሰብ የሐዘንና የተዝካር ስርዓት ክዋኔ፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1998 ዓ.ም፡፡

አባተ አሰፋ፡፡ "የአሚባራ ወረዳ አፋሮች የለቅሶ ስርዓት (አርካ) እና ምሳሌያዊ ንግግሮች ትንታኔ፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡

አየለ መሎሬ፡፡ "የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1986 ዓ.ም፡፡

አየሁሽ ቶማ፡፡ “የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ፡፡” ጥናት፡፡" በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡

ወርቁ ማንደፍሮ፡፡ "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1987 ዓ.ም፡፡

ወርቃየሁ አረጋ፡፡ "የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርዓት) እና የአዊ ዚንዚምኛ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1995 ዓ.ም፡፡

ውቤ ታደገ፡፡ "የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ጥናት፡፡" በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡

ዘላለም ፋንቱ፡፡ "የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" ጥናት፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ <u>የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፣ 1992፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ <u>የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋና ታሪክ ቅርስ ጥናት ተቋም፡፡ <u>የደቡብ ብሔር ችህዝቦች ፕሮፋይል</u>፡፡ ሀዋሳ፡፡ ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡

ጌታመሳይ ግዛው፡፡ "የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር፡፡" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡

ጌጡ ታደሰ፡፡ "ክዋኔ በጎንደር ከተማ ለቅሶ ስነ ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1986 ዓ.ም፡፡

ጥላሁን ኢቢዶ፡፡ "የጌዴኦ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት፡፡" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1982 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ <u>የሥነ - ቃል መምሪያ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡ 1991 ዓ.ም፡፡

Abudulla Abdurahman. "Harriri Funeral Customs." Ethnological Society Bulletin. Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 1. Addis Ababa, Addis Ababa University Press, 2002.

Andargachew Tesfaye. "The Funeral Customs of the Kottu of Harar." Ethnological Society Bulletin. Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa University Press, 2002.

Bauman, Richard, and Briggs L, Charles.Poetics and Performance as Critical Perspectives on Language and Social Life:Annual Review of Anthropology New York: Vassar College, 1990.

Bauman, Richard, ed. Folklore Cultural Performances and Popular Entertainment. New York: Oxford University Press, 1992.

Ben-Amos, Dan. "Context in Context "Western Folklore: Theorizing Folklore Toward New Perspectives on the Politics of Culture, 1993.

-------"Toward A Definition of Folklore in Context: Toward New Perspectives in Folklore." The Journal of American Folklore, 1971.

Brown, Inc Corinne. *Understanding others Cultures*. Prentice Hall Inc ; Gngliwood cliffs N.J, 1963.

Cohen, Milton. Death Ritual: Anthropological Perspectives. McGraw-Hill: Companies Inc, 1980.

Corinne, Brown. Understanding Other Cultures. The United States of America: Library of Congress press, 1963.

David, Gray E. Doing Research in the Real World. London, SAGE Publications Ltd, 2004.

Dorson, Richard M ed. Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Fassika Bellete. "The Death Customs Among the Amharas of Sawa." Ethnological Society Bulletin. Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa University Press, 2002.

Finnegan, Ruth. Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices. London And New York: Rutledge, 1992.

Kapchan, A Deborah. Performance. The Journal of American Folklore. New York: 1995: Vol. 108, No. 430.

Kenneths, Goldstein, and Henderson, Hamish. A Guide for Field Workers in Folklore. The American Folklore Society. Pensilvaniya,1964.

Kothari, C. R. Research Methodology: Methods & Techniques. 2nd ed. India, New International (P) Limited, Publishers. 2004.

Kottack, Phillip. Anthropology the Explanation and Human Diversity. McGraw-Hill: Companies Inc, 2002.

Nega Tessema. "The Death Customs in the Province of Tigre." Ethnological Society Bulletin. Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 5. Addis Ababa, Addis Ababa University Press, 2002.

Ralph, Linton. The Study of Man an Introduction. The United States of America: Division of Meredith Company, 1964.

Rappaport, roy a. “Ritual.”Folklore ,cultural performances ,and popular entertainment .Ed. Richard Bouman. New York: Oxford University

Schensul J, Jean and etal. Enhanced Ethnographic Methods. New York, Altamira Press, 1999.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan: Utah State University Press, 2005.

Small, Neil. "Death and Difference" in D. Field, J. Hockey and N. Small (eds.) Death, Gender and Ethnicity. London: Rutledge, 1997. pp. 209 - 226.

Untiedt, Kenneth L. Death Lore. University of North Texas Press, 2008.

## አባሪዎች

አባሪ 1. የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል፣

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ፆታ | የት/ት ደረጃ | ስራ | የመኖሪያ አካባቢ | የሰጡት መረጃ አይነት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አምባው ጮሪቶ | 54 | ወ | 12 + 4 | የመንግስት ሰራተኛ | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን እና ማህበረ ባህላዊ ዳራን በተመለከተ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 2 | » ስለሺ ጫሊቶ | 47 | ወ | 12 ኛ ክፍል | ነጋዴ | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔንና ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 3 | » ኃይሌ መድራሻ | 57 | ወ | 12 + 2 | የመንግስት ሰራተኛ | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን እና ማህበረ ባህላዊ ዳራን በተመለከተ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 4 | ወ/ሮ ዘውዲቱ አንገሎ | 68 | ሴ | 5ኛ ክፍል | አርሶ አደር | አበሎ ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 5 | » በላይነሽ አርጀሮ | 46 | ሴ | 8ኛ ክፍል | » » | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | |
| 6 | አቶ መንገሻ አለሙ | 73 | ወ | መሰረተ ት/ት | » » | ይና ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔንና ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | |
| 7 | » አዴሎ ሻጫቸው | 70 | ወ | » » | » » | ይና ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔንና ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | |
| 8 | » አበበ ዋጋቸው | 77 | ወ | » » | » » | አበሎ ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 9 | ወ/ሮ አዛለች አንጉሎ | 65 | ሴ | 6ኛ ክፍል | » » | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 10 | » አልማዝ ጋዎቶ | 61 | ሴ | 4ኛ ክፍል | የፅዳት ሰራተኛ | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | » ፋናዬ ኮታቸው | 42 | ሴ | 10ኛ ክፍል | የመንግስት ሰራተኛ | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 12 | አቶ መጂቶ ደሰኖ | 47 | ወ | 7ኛ ክፍል | አርሶ አደር | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 13 | » አዳሾ ሻዎኖ | 64 | ወ | 6ኛ ክፍል | » » | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 14 | » ጋረፎ መጫሎ | 78 | ወ | መሰተረ ት/ት | » » | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 15 | » ካፊሾ ዴግራሻ | 57 | ወ | 7ኛ ክፍል | » » | አበሎ ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔንና ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 16 | አቶ አስታውሰኝ በቃሉ | 32 | ወ | 12 + 4 | የመንግስት ሰራተኛ | ማሻ ከተማ | አካባቢያዊና ማህበራዊ ዳራን በተመለከተ | |
| 17 | ወ/ሮ መሰረት አንገሎ | 45 | ሴ | 8ኛ ክፍል | አርሶ አደር | ማሻ ከተማ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | |
| 18 | ወ/ሮ ፋናዬ ጨጊቶ | 62 | ሴ | 4ኛ ክፍል | አርሶ አደር | ይና ቀበሌ | የለቅሶ ክዋኔን በተመለከተ | የተ.ቡ.ው. አባል |
| 19 | አቶ አስፈፋው መጫሎ | 44 | ወ | 9ኛ ክፍል | አርሶ አደር | ይና ቀበሌ | ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | |
| 20 | አቶ ካሙቶ ዋሜቾ | 67 | ወ | 7ኛ ክፍል | አርሶ አደር | አበሎ ቀበሌ | ታሪካዊ ዳራን በተመለከተ | |

አባሪ 2፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ናሙና፣




ፎቶ 1፡- አጥኚው ከአቶ አምባው ጮሪቶ ጋር ቃለ-መጠይቅ ሲያካሂድ የሚያሳይ፣




ፎቶ 2፡- አጥኚው ከአቶ ኃይሌ መድራሻ ጋር - በቃለ-መጠይቅ ወቅት፣